

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት

# በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸሙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚውል መደበኛ የጨረታ ሰነድ

## (ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ)

የሚገዛው አገልግሎት:- *[የዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች አጠቃላይ መግለጫ ይግባ*]

የግዥ መለያ ቁጥር:- *[የግዥው መለያ ቁጥር ይግባ]*

የውል ዓይነት:- የማዕቀፍ ስምምነት

የፕሮጀክቱ ስም:- *[የፕሮጀክቱ ስምይግባ ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ*]

ጨረታ ሰነዱ የወጣበት ቀን:- *[ቀንይግባ]*

አዲስ አበባ ___ ወር ____ ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት

### መቅድም

ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ግዥ መፈፀም የሚችለው በመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1333/2016 እንዲሁም በገንዘብ ሚኒስቴር ግንቦት 2017 ዓ.ም. በወጣው የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያና ለዚሁ ዓላማ ተብሎ በተዘጋጀው በዚሁ መደበኛ የጨረታ ሰነድ መሠረት ይሆናል።

ይህ መደበኛ የጨረታ ሰነድ በመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን (ከዚህ ቡኋላ ''ባለሥልጣን " እየተባለ በሚጠራው) የተዘጋጀ ሲሆን ዓላማውም በዋነኛነት በመንግሥት ግዥ አገልግሎት (የማዕቀፍ ስምምነቱን ለማስተዳደር የተቋቋመ ማዕከላዊ አካል) እና እንደአግባብነቱ ሌሎችም የመንግስት መ/ቤቶች ተከታታይነት ያላቸው ፍላጎቶቻቸውን፤ የጋራ የሆኑና ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ትላልቅ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አጠቃሎ በመግዛት ከጥራት የሚገኘውን ጥቅም ሳይጓደል ከዋጋ የሚገኘውንም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም (economy of scale) ግምት ውስጥ ያስገባ ነው።

የማዕቀፍ ስምምነት ማለት ከአቅራቢዎች ጋር የሚደረግ ስምምነት ሲሆን የመንግስት አካላት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለመግዛት ሲፈልጉ ሊከተሉዋቸው የሚገቡ ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች፣ እንዲሁም የግዥ ትዕዛዝ አሰጣጥ ስርዓቶችን ያመለክታል። የማዕቀፍ ስምምነቱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የመንግስት መ/ቤቶች ዕቃዎች ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች ከአቅራቢዎች መግዛት ሲፈልጉ ለእያንዳንዱ ግዥ አዲስ የግዥ ሂደት መጀመር አያስፈልጋቸውም።

እንደዚህ አይነቱ የማዕቀፍ ስምምነት በቀጣይነት ለሚፈፀሙ የአስገዳጅነት ባህሪይ ላላቸው የተናጠል ውሎች የሚያገለግል ነው። በዚሁ የማዕቀፍ ስምምነት መሰረት ውሎች የሚመሰረቱት ይህንን የማዕቀፍ ስምምነት መሰረት በማድረግ በመ/ቤቶቹ እና በአቅራቢዎች መካከል የተናጠል ውል ሲፈጸም ነው።

በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት ውስጥ የተመለከቱት ሰነስርዓቶችና ልምዶች የዳበሩት በርካታ አለም አቀፋዊ ልምዶችን መሠረት በማድረግ ሲሆን ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ አንፃር በሙሉም ሆነ በከፊል በመንግሥት ገንዘብ በሚፈፀሙ ግዥዎች ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

ተጨማሪ መረጃ ሲያስፈልግ በሚከተለው አድራሻ መጠየቅ ይቻላል።
የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን
ስልክ ቁ. 251-111-248614/15
ፋክስ ቁ. 251-111-248611
ዌብሳይት http://www.ppa.gov.et

## የጨረታ ሰነድ

ማውጫ

**ምዕራፍ 1፡ የጨረታ ሥነ-ሥርዓት**......I

ክፍል 1: የተጫራቾች መመሪያ......I

ክፍል 2፡ የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ......II

ክፍል 3፡ የጨረታዎች የግምገማ ዘዴና መስፈርቶች......III

ክፍል 4፡ የጨረታ ቅፆች......IV

ክፍል 5፡ በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ ሀገሮች (ብቁ ሀገሮች)......V

**ምዕራፍ 2: የፍላጐቶች መግለጫ......VI**

ክፍል 6: የፍላጐቶች መግለጫ......VI

**ምዕራፍ 3: ውል......VII**

ክፍል 7: አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች......VII

ክፍል 8፡ ልዩ የውል ሁኔታዎች......VIII

ክፍል 9፡ የውል ቅፆች......IX

# ምዕራፍ 1

# የጨረታ ሥነ-ሥርዓት

## ክፍል 1: የተጫራቾች መመሪያ

ማውጫ


ሀ. ጠቅላላ.....1

1. መግቢያ.....1
2. የገንዘብ ምንጭ.....3
3. አጭበርባሪነት፣ ሙስናና አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት.....3
4.ተቀባይነት ያላቸው ተጫራቾች.....5
5. ተቀባይነት ያላቸው ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች.....7

**ለ. የጨረታ ሰነድ ይዘት.....8**

6. የጨረታ ሰነድ.....8
7. በጨረታ ሰነዱ ላይ የሚሰጥ የፅሑፍ ማብራሪያ.....9
8. በጨረታ ሰነዶች ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ.....10
9. የቅድመ-ጨረታ ስብሰባ (ኮንፈረንስ).....10

**ሐ. የጨረታ አዘገጃጀት.....11**

10. በጨረታ የመሳተፍ ወጪ.....11
11. የጨረታ ቋንቋ.....11
12. የጨረታ ዋጋዎችና ቅናሾች.....12
13. የጨረታ ዋጋ የሚቀርብባቸው የገንዘብ አይነቶች.....14
14. የተጫራቾች ሙያዊ ብቃትና አቅም.....14
15. የተጫራቾች የፋይናንስ አቅም.....14
16. የተጫራች ቴክኒካል ብቃት፣ ክህሎትና ልምድ.....14
17. የቴክኒክ ብቃት ማስረጃ ሰነዶች.....16
18. የናሙናዎች አቀራረብ.....16
19. የሽሙር ማህበር ወይም ጊዜያዊ ጥምረት.....17
20. አማራጭ ጨረታዎች.....17
21. ጨረታዎች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜ.....18
22. የጨረታ ዋስትና.....19
23. ከመጫረቻ ሰነድ ጋር መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች.....20
24. የጨረታ ቅፆችና አቀራረብ.....22

**መ. የጨረታ አቀራረብና አከፋፈት.....22**

25. የጨረታ ሰነድ አስተሻሸግና ምልክት አደራረግ.....22
26. የጨረታ ማቅረቢያ ቀነ-ገደብ.....23
27. ዘግይተው የቀረቡ ጨረታዎች.....23
28. ጨረታዎችን መሰረዝ፣ መተካትና ማሻሻል.....24

29. የጨረታ አከፋፈት......24

**ሠ. ጨረታዎችን መገምገምና ማወዳደር......25**

30. ምስጢራዊነት......25
31. የማብራሪያ ጥያቄ አቀራረብ......26
32. ተቀባይነት ያላቸው ጨረታዎች......26
33. አለመጣጣምና ግድፈቶች......27
34. አጠራጣሪ የጨረታ ዋጋዎችና የስሌት ስህተቶች......27
35. ልዩ አስተያየት......28
36. የመጀመሪያ ደረጃ የጨረታዎች ግምገማ......29
37. ከህጋዊነት፣ ሙያ፣ የቴክኒክ ብቃትና የፋይናንሺያል አንፃር የጨረታዎች አወሳሰን መስፈርቶች......30
38. ጨረታዎችን ስለመገምገም......32
39. ጨረታዎችን ስለማወዳደር......34
40. ድህረ-ብቃት ግምገማ......34
41. ጨረታን ስለመቀበል ወይም ውድቅ ስለማድረግ......34
42. ድጋሚ ጨረታ ስለማውጣት......34

**ረ. ውል ስለመፈፀም......35**

43. አሸናፊ ተጫራችን መምረጫ መስፈርቶች......35
44. ከውል በፊት የግዥ መጠን ስለመለወጥ......35
45. የጨረታ ውጤትና አሸናፊ ተጫራችን ስለማሳወቅ......35
46. ውል አፈራረም......36
47. የውል ማስከበሪያ ዋስትና......37

## ክፍል 1፡ የተጫራቾች መመሪያ

### ሀ. ጠቅላላ

**1. መግቢያ**

1.1 በጨረታው ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ የተጠቀሰው የግዥ ፈፃሚ አካል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የግዥ ሕጐች መሠረት የዚሁ ጨረታ ተዋዋይ አካል ነው። ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ መንግሥታዊ አካላት የሚቀርቡትን የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥዎችን የማዕቀፍ ስምምነቶች ለመፈፀም ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶታል። ስለሆነም ይህ የግዥ ሂደት በሥራ ላይ ባለው የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና አፈፃፀም መመሪያ፣ እንዲሁም በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ በተመለከተው የግዥ ዘዴ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል።

1.2 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ይህንን የጨረታ ሰነድ በማውጣት የማዕቀፍ ስምምነት በማድረግ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ለማቅረብ ፍላጐት ያላቸው ተወዳዳሪዎችን ይጋብዛል። የዕቃዎችና አገልግሎቶች አጠቃላይ ሁኔታ በጨረታው ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥና በዚሁ የጨረታ ሰነድ ክፍል 6 ላይ ተመልክቷል።

1.3 የዚህ የጨረታ ሰነድ የግዥ መለያ የሎት (lot) ብዛት በጨረታው ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ ተመልክቷል። ለእያንዳንዱ ሎት (lot) ጨረታ እንዲቀርብ በሚጠየቅበት ጊዜ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸውን ለአንድ ሎት (lot)፣ ለበርካታ ለቶች (lots) ወይም ለሁሉም ሎቶች (lots) ማቅረብ ይችላሉ። እያንዳንዱ ሎት (lot) የራሱ የሆነ ውል የሚኖረው ሲሆን በአንድ ሎት (lot) ውስጥ የተጠቀሰው የአቅርቦት መጠን መከፋፈል ግን አይቻልም። ተጫራቾች እንደምርጫቸው ለሁሉም ሎቶች (lots) ወይም ለእያንዳንዱ ሎት (lot) ውስጥ ለተጠቀሰው ቁጥር መጫረት ይችላሉ።

1.4 እያንዳንዱ ተጫራች በግሉ ወይም ከሌላ አጋር ጋር በመሆን በጥምረት ወይም በሽርክና ወይም በእሽሙር ማህበር የመጫረቻ ሰነዱን ማቅረብ ይችላል። ሆኖም በተፈቀደ አማራጭ ጨረታ መልክ ወይም በንዑስ ውል ስምምነት ካልሆነ በስተቀር ከአንድ በላይ የመጫረቻ ሰነድ ማቅረብ ከውድድር ውጭ ያስደርጋል።

1.5 የመንግሥት መ/ቤቶች የዕቃዎችና አገልግሎቶች የፍላጐት እቅድን መሠረት በማድረግ የግዥ መጠንና ሂደት በሚገለፅበት በክፍል 6 ላይ በተመለከተው ዝርዝር መሠረት የሚፈፀም ይሆናል። ይሁን እንጂ በክፍል 6 የሚመለከተው ፍላጐት ግምታዊ በመሆኑ ምክንያት ስለትክክለኛነቱ የግዢ ፈፃሚው መ/ቤት ኃላፊነት አይወስድም።

1.6 የማዕቀፍ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሌሎች መንግሥታዊ አካላትን በመወከል የማዕቀፍ ስምምነት ውል በመፈጸም የአቅራቢዎችን ምደባ ያሳውቃል፡፡ የመንግስት መ/ቤቶችም የማዕቀፍ ውል ስምምነቱን መሠረት በማድረግ የተናጠል ውል ስምምነት ከአቅራቢዎችን ጋር ይፈጽማሉ፡፡

1.7 በዚሁ የማዕቀፍ ስምምነት ሊታቀፉ የሚችሉ በሙሉም ሆነ በከፊል በፌዴራል መንግሥት በጀት የሚተዳደሩ የመንግሥት መ/ቤቶች፣ ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች በመባል የሚጠሩት ናቸው፡፡

1.8 ይህ የማዕቀፍ ስምምነት የሚፈፀመው በጨረታው ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ስምምነቱ ሥራ ላይ ከሚውልበት ቀን ጀምሮ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ የስምምነቱ ጊዜና ሌሎች በማዕቀፍ ስምምነቱ የተመለከቱት ጊዜያቶች የሚታሰቡት ተከታታይ ቀናቶችን በመቁጠር ይሆናል፡፡

1.9 የማዕቀፍ ግዥ ፈፃሚው አካል ይህንን የማዕቀፍ ስምምነትና የጨረታ ግምገማ ውጤቱን በማየት በጨረታው ሂደት ከተሳተፉት መካከል ከአንድ በላይ ለሆኑ ተጫራቾች በጨረታ ውጤታቸው ቅደም ተከተል መሠረት የጨረታ አሸናፊነት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ከሌሎች ተጫራቾች ጋር የጨረታ ውል የሚፈረመው የተመረጠውን አቅራቢ ዋጋ መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

1.10 ክፍል 1 የተጫራቾች መመሪያ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸውን ምን ምን ሁኔታዎችን አሟልተው በምን መንገድ ማቅረብ እንዳለባቸው ለመጠቀም ዓላማ የተዘጋጀ እንጂ የማዕቀፍ ስምምነቱ አካል አይደለም፡፡

1.11 የማዕቀፍ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ይህንን የጨረታ ሰነድ በማውጣቱ ምክንያት በማንኛውም ሁኔታ የማዕቀፍ ስምምነት እንዲፈጽም አይገደድም፡፡

1.12 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በኤልክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት ባወጣው ጨረታ የቀረቡለትን የመጫረቻ ሰነዶችን በባለቤትነት የመያዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ በመሆኑም ዘግይተው የደረሱ ጨረታዎች ካልሆኑ በስተቀር ተጫራቾች ያቀረቡት የመጫረቻ ሰነድ እንዲመለስላቸው የመጠየቅ መብት አይኖራቸውም፡፡

1.13 አንድ ተጫራች የመጫረቻ ሠነድ በሚያቀርብበት ጊዜ በጨረታ ሰነዱ የተመለከቱትን የግዥ ሥነ-ሥርዓቶችና ሁኔታዎች ያለምንም ገደብ እንደተቀበለ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም ተጫራቾች

የመጫረቻ ሠነድ ከማቅረባቸው በፊት በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የተመለከቱትን መመሪያዎች፣ ቅፆች፣ የስምምነት ሁኔታዎችና የፍላጐት ዝርዝሮች በጥንቃቄ ሊመረምሩዋቸው ይገባል፡፡ በጨረታ ሰነዱ ላይ የተጠየቁት መረጃዎችና ሰነዶች ተሟልተው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ካልቀረቡ ጨረታው ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል፡፡ በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለፁ ሁኔታዎች አሟልቶ አለማቅረብ ያለምንም ተጨማሪ የማጣራት ሥራ ከጨረታ ውድድር ውጭ ለመሆን ምክንያት ይሆናል፡፡

1.14 በግዥ ፈፃሚው መ/ቤትና በተጫራቾች መካከል የሚኖረው ግንኙነት የመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን ብቻ የተከተለ ይሆናል፡፡ በዚህ የጨረታ ሰነድ መሠረት ኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ሲባል በኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን በመጠቀም የተላከ መልእክት ነው፡፡

## 2. የገንዘብ ምንጭ

2.1 የመንግስት መ/ቤቶች ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር የተናጠል ውል ስምምነት ሲፈጽሙ በማዕቀፍ ስምምነቱ፣ በጨረታው ዝርዝር መረጃ ጠንረኸና በክፍል 6 የተመለከቱትን የዕቃዎችና አገልግሎቶች ፍላጐቶች ለመግዛትና የግዥ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚውል የፀደቀ (የተፈቀደ) በጀት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጠው የመንግስት የኤልክትሮኒክ ሥርዓትን በመጠቀም ይሆናል፡፡ በሲስተሙ የሚሰጠው የግዥ ትዕዛዝ በማዕቀፍ ስምምነቱ የተመለከቱት የውል ቃሎችና ሁኔታዎች በትዕዛዝ ተቀባዩ ወገን ተቀባይነት እንዳገኙ ይቆጠራል፡፡

2.2 ክፍያ የሚፈፀመው የተናጠል ውል በሚገባው የመንግስት መ/ቤት ሲሆን፣ አቅራቢው ክፍያውን የሚያገኘው ከግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ጋር በገባው የተናጠል ውል መሠረት ዕቃዎችና አገልግሎቶችን የማቅረብ ግዴታውን ሲወጣ ይሆናል፡፡

## 3. አጭበርባሪነት፣ሙስናና አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት

3.1 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት (ከሁን በኋላ "መንግሥት" እየተባለ የሚጠራው) በመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን (ከሁን በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ በሚጠራው) የሚወከል ሲሆን፤ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶች እና ተጫራቾች በግዥ ሂደትና በውሎች አፈፃፀም ወቅት የሥነ-ምግባር ደንቦችን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያከብሩ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በዚሁ ፖሊሲ መሠረት መንግሥት፦

(ሀ) ከላይ በአንቀጽ 3 ላይ ለተመለከተው አፈፃፀም ሲባል ለሚከተሉት ቃላት ቀጥሎ የተመለከተውን ፍች ይሰጣል።

“የሙስና ድርጊት” ማለት የአንድን በመንግሥት የግዥ አፈጻጸም ሂደት ወይም በውል አፈጻጸም ወቅት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተሳታፊ የሆነን የመ/ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም የግዥ ክፍል የሥራ ኃላፊ ወይም የአጽዳቂና ጊዜያዊ ገምጋሚ ኮሚቴ አባላት ወይም የግዥ ባለሙያ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለማባበል (ለማግለል) በማሰብ ማንኛውም ዋጋ ያለው ነገር መስጠት፣ ወይም ለመስጠት ማግባባት ማለት ነው።

ii) “የማጭበርበር ድርጊት” ማለት ያልተገባን የገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ግዴታን ላለመወጣት በማሰብ የግዥ ሂደቱንና የውል አፈፃፀሙን በሚጐዳ መልኩ ሀቁን በመለወጥና አዛብቶ በማቅረብ ሆን ተብሎ የሚፈፀም ድርጊት ነው።

“የመመሳጠር ድርጊት” ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ተጫራቾች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እያወቀም ሆነ ሳያውቀው በመመሳጠር ውድድር አልባና ተገቢ ያልሆነ ዋጋን መፍጠር ማለት ነው።

“የማስገደድ ድርጊት” ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሰዎችን አካልና ንብረት በመጉዳትና ለመጉዳት በማስፈራራት በግዥ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ወይም የውል አፈፃፀም ማዛባት ማለት ነው።

“የመግታት (የማደናቀፍ) ድርጊት” ማለት፣

መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን ሆን ተብሎ በማጥፋት፣ በምርመራ ሂደት የሚሳተፉ አካላትን በማስፈራራትና ጉዳት በማድረስ የምርመራ ሂደቶችን መግታት ወይም ማደናቀፍ ሲሆን፣ የዚህ መደበኛ የጨረታ ሰነድ አካል የሆነው የተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 3.5 ላይ የተመለከቱትን የቁጥጥርና የኦዲት ሥራዎች ማደናቀፍ ወይም መግታትን ያካትታል።

(ለ) በአሸናፊነት የተመረጡ ተጫራቾች በራሳቸው ወይም በተወካያቸው አማካኝነት የሙስናና የማጭበርበር፣ የማሴር፣ የማስገደድና የመግታት/ማደናቀፍ ድርጊት በጨረታው ሂደት ወቅት ከፈፀሙ ከጨረታው ይሰረዛሉ።

(ሐ) ተጫራቾች በማንኛውም የጨረታ ሂደት ጊዜ ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በሙስና፣ በማጭበርበር፣ በመመሳጠር፣ በማስገደድና በማደናቀፍ ተግባር ተካፋይ መሆናቸው ከተረጋገጠ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ በመንግሥት ግዥ ተካፋይ እንዳይሆኑ ይታገዳሉ።

የታገዱ ተጫራቾች ወይም አቅራቢዎች ዝርዝር በመንግስት የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ፖርታል ላይ ይገለጻል፡፡

3.2 ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3.1 ላይ ከተጠቀሰው ጋር በተያያዘ የግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ ወይም ተጫራቹ ወይም የተጫራቹ ተወካይ በግዥው ሂደት ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በሙስና ወይም በማጭበርበር ወይም በመሳሰሉት ድርጊቶች መሳተፋቸው ከተረጋገጠ/ከታወቀ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የማዕቀፍ ስምምነቱን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

3.3 የጨረታውን ውጤት ባልተገባ ሁኔታ ለማስቀየር በማሰብ በግዥ ሂደቱ ላይ ተሳታፊ ለሆኑ የመ/ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ማማለያ የሰጠ ወይም ለመስጠት ጥያቄ ያቀረበ ተጫራች ከጨረታው እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡ በሌሎች የመንግሥት ግዥዎችም እንዳይሳተፍ ይደረጋል፡፡ ያስያዘው የጨረታ ዋስትናም ይወረሳል፡፡

3.4 ተጫራቾች በሙስናና በማጭበርበር ጉዳይ ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች መቀበላቸውን በጨረታው ማቅረቢያ ሠንጠረዥ ማመልከት ይኖርባቸዋል፡፡

3.5 ከስምምነቱ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የአቅራቢዎች የሂሳብ መዝገቦችና ሰነዶች የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት በሚመድቧቸው ኦዲተሮች እንዲመረመሩና ኦዲት እንዲደረጉ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

3.6 በመንግሥት የግዥ አዋጅና መመሪያ መሠረት አንድ ተጫራች ከጨረታ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የግዥ ፈፃሚው አካል አዋጁንና መመሪያውን የጣሰ ከመሰለውና ቅር ከተሰኘ አፈፃፀሙ እንደገና እንዲታይለት ወይም እንዲጣራለት ለግዥ ፈፃሚ አካል የበላይ ሀላፊ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ተጫራቹ ቅሬታ ያስከተለበትን ድርጊት ባወቀ ወይም ማወቅ ይገባ ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት የበላይ ሀላፊ አቤቱታውን በኤልክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ተጫራቹ በተሰጠው ውሳኔ ካልረካ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለቦርድ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ በሁለቱም ወገኖች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**4.** ***ተቀባይነት ያላቸው ተጫራቾች***

4.1 አንድ ተጫራች የተፈጥሮ ሰው፣ የግል ድርጅት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት፣ (በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.5 መሠረት) ወይም በማንኛውም ዓይነት በጥምረት ወይም

በሽርክና ወይም በእሽሙር ማህበር ስምምነት ውስጥ ያለ ወይም አዲስ ስምምነት ለመፍጠር ይፋዊ ዕቅድ ያለው ሊሆን ይችላል፡፡

(ሀ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር በጥምረት ወይም በሽርክና ወይም በእሽሙር ማህበር የታቀፉ የጥምረቱ አባላት በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

(ለ) በጥምረት ወይም በሽርክና ወይም በእሽሙር ማህበር የሚሳተፉ ተጫራቾች እነሱን ወክሎ በጨረታ ሂደት ጊዜና በውል አፈፃፀም ወቅት ሊሰራላቸው የሚችል ተወካይ መምረጥ ይኖርባቸዋል፡፡

4.2 የአገር ውስጥ ተጫራች ማለት የተጫራቹ ወይም የአክሲዮን ባለድርሻ ባለቤቶች ዜግነት ከግምት ሳይገባ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ከተቋቋመ እና የንግድ እንቅስቃሴ ካለው፣ የንግድ ምዝገባ፣ የታክስ መለያ ቁጥር እና የንግድ ፈቃድ ያለው ተጫራች ከሆነ የጨረታው ተሳታፊ ይሆናል፡፡

4.3 ማንኛውም ተጫራች የጥቅም ግጭት ሊኖረው አይገባም፡፡ በጥቅም ግጭት ውስጥ መኖራቸው የተደረሰባቸው ተጫራቾች ሁሉ ውድቅ ይደረጋሉ፡፡ አንድ ተጫራች በዚሁ የጨረታ ሂደት ውስጥ ከአንድ ወይም ከሌሎች አካላት ጋር የጥቅም ግጭት አለው ተብሎ የሚወሰደው፦

(ሀ) አሁን ወይም ከዚህ ቀደም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጨረታ ለሚገዙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሰነድ ዝግጅት ወይም በማማከር አገልግሎት ከተሳተፉ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ካለው ወይም ከአጋሮቹ አንዱ በመሆን በስራው ተሳታፊ ከነበረ፣ ወይም

(ለ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሦስተኛ አካል ጋር ባለው ግንኙነት ምክንያት መረጃዎችን በመስጠት በሌሎች ተጫራቾች በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የግዥ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር የጨረታውን ሂደት ሊያዛባ የሚችል ከሆነ፣

(ሐ) በጨረታ ሂደት ወቅት ከአንድ በላይ የመጫረቻ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ፣

መ/ ሁለትና ከዛ በለይ የሆኑ ተጫራቾች ለአንድ የጨረታ ዓላማ አንድ ተወካይ ያላቸው ከሆነና፤

ሠ/ አንድ ተጫራች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ከሚያደርግ የመንግስት መ/ቤቱ ሰራተኛ ጋር የስራ ወይም የቤተሰብ ግንኙነት ያለው ከሆነ፣

4.4 አንድ ተጫራች በጨረታ ማስረከቢያ ቀነ-ገደብ ወይም ከዚያ በኋላም ቢሆን በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 3.1(ሐ) መሠረት ዕገዳ የተጣለበት ከሆነ ይህንን ጨረታ ለመካፈል ብቁ አይሆንም፡፡

4.5 በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ስር የሚተዳደሩ እስካልሆኑ ድረስ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው በፋይናንስ ራሳቸውን ችለው የሚተዳደሩና በንግድ ሕግ መሠረት ተቋቁመው የሚሰሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለመጫረት ብቁ ናቸው፡፡

4.6 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ተጫራቾች ከዚህ በታች የተመለከቱትን የብቁነት ማረጋገጫዎች ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

(ሀ) ዕዳ መክፈል ያላቃታቸው፣ ያልከሰሩ፣ በመፍረስ ላይ ያልሆኑ፤ የንግድ ስራቸው ያልተገደበባቸው መሆናቸውን፣
(ለ) የሚከተሉትን ጨምሮ የተጫራቹን ህጋዊነት የሚያሳዩ ማስረጃዎች፤

ተጫራቹ የተሰማራበትን የስራ ዘርፍ የሚያሳይ የታደሰ የንግድ ፈቃድ
የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርቲፊኬት
በመንግሥት የግብር ሕግ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያሳይ ሰርቲፊኬት
አግባብነት ያለው የሙያ ብቃት ሰርቲፊኬት (በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ከተጠየቀ ብቻ)

4.7 በመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ በመንግስት የኤልክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት በአቅራቢነት መመዝገብ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡

4.8 ተጫራቾች በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተጠቀሰው መሠረት ህጋዊነታቸው ተቀባይነት ያለው መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ለግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

4.9 ተጫራቹ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር በመንግስት ግዥ ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም በግል ወይም በሽርክና፣ በጥምረት ወይም በእሽሙር ማህበር የሚሳተፍ ተጫራች የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ያላቸውን ሰዎች የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

4.10 በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 4.8 አፈፃፀም አላማ የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይገለፃል፤

ሀ/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቢያንስ አስር በመቶ [10%] የሚሆነውን የድርጅቱ አክሲዮኖች ወይም የመምረጥ መብቶችን በባለቤትነት የያዘ ወይም የተቆጣጠረ እንደሆነ፤
ለ/ በሌሎች መንገዶች በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድር ወይም የሚቆጣጠር ከሆነ፣

ሐ/ በባለቤትነት የተመዘገበም ሆነ ያልተመዘገበ ሆኖ ድርጅቱ ላይ የመጨረሻ እና ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ከሆነ፣

4.11 በተጫራቹ የሚቀርበው የተጠቃሚ ባለቤትነት መብትን የሚገልጹ መረጃዎች ሀሰተኛ ያልተሟሉና ትክክለኛነት የሚጎላቸው መሆናቸው በመንግስት መ/ቤቶች ከተረጋገጠ፣ የቀረበውን የመጫረቻ ሰነድ በቅድሚያ ውድቅ በማድረግ በተጫራቹ ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርቡ ይችላል።

**5.** ***ተቀባይነት ያላቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች***

5.1 በክፍል 5 ስለ ብቁ ሀገሮች (በጨረታው መሳተፍ ስለሚችሉ ሀገሮች) በተገለፀው መሠረት የሚቀርቡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ምንጭ ከብቁ ሀገሮች መሆን ይኖርበታል።

5.2 ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ሲባል "ዕቃዎች" ማለት በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሳሪያ፣ ሸቀጥ፣ ለገበያ የተዘጋጀ ሶፍትዌር እና እንስሳ ነው፤ <<አገልግሎት>> ማለት ከግንባታ ዘርፍ ሥራ እና ከምክር አገልግሎት ውጪ የሆነ ማንኛውም አገልግሎት ሲሆን፣ የኪራይ፣ የትራንስፖርት፣ የህትመት፣ የጥገና፣ የጥበቃ፣ የጽዳት፣ የኃይል አቅርቦት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የውሃ አቅርቦት እና የመሳሰሉት አገልግሎቶችን ይጨምራል።

5.3 "የመነሻ ሀገር" የሚለው ቃል ዕቃዎቹ በቁፋሮ የወጡበት፣ ያደጉበት፣ የለሙበት፣ የተመረቱበት፣ የተፈበረኩበት ወይም የተዘጋጁበት ወይም የተገጣጠሙበት፤ የተሰሩበት፤ በንግድ ዕውቅና የተሰጠውና በመሠረታዊ በህርይ ከውጪ ከመጡት አካላቶች የሚለይ ዕቃ የተሠራበት ሀገር ማለት ነው።

5.4 ዕቃዎቹን የሚያመርት፣ የሚገጣጥም፣ የሚያከፋፍል ወይም የሚሸጥ ድርጅት ዜግነት የዕቃዎቹን መነሻ ሀገር ሊወስን አይችልም።

5.5 በተጫራቾች መመሪያ መሠረት የዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ ብቃት ለማረጋገጥ ተጫራቾች በክፍል 4 በተመለከተው የጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ቅፅ ላይ የመነሻ ሀገር መግለጫ በመሙላት ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

5.6 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የተጠየቀ ከሆነ ተጫራቾቹ በክፍል 4 የተመለከተውን የጨረታ ቅፅ በመጠቀም የሚያቀርባቸው ዕቃዎች እና/ወይም አገልግሎቶች የአምራች ድርጅት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

**ለ. የጨረታ ሰነድ ይዘት**

**6. *የጨረታ ሰነድ***

6.1 ይህ የጨረታ ሰነድ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ክፍሎች የሚያጠቃልልና በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 8 ከተመለከቱት ተጨማሪ ጽሑፎች ጋር በጥምረት መነበብ ያለባቸውን የጨረታ ሰነድ ምዕራፎች 1፣ 2 እና 3 ያካትታል።

ምዕራፍ 1:- የጨረታ ሥነ-ሥርዓት

ክፍል 1 - የተጫራቾች መመሪያ

ክፍል 2 - የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ

ክፍል 3 - የጨረታዎች ግምገማ ዘዴና መስፈርቶች

ክፍል 4 - የጨረታ ቅፆች

ክፍል 5 - በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ ሀገሮች (ብቁ ሀገሮች)

ምዕራፍ 2:- የፍላጐቶች መግለጫ

ክፍል 6 - የፍላጐቶች መግለጫ

ምዕራፍ 3:- ውል

ክፍል 7 - አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች

ክፍል 8 - ልዩ የውል ሁኔታዎች

ክፍል 9 - የውል ቅፆች

6.2 የጨረታ ማስታወቂያ የጨረታው ሰነድ አካል አይደለም። በጨረታ ማስታወቂያውና በጨረታ ሰነዱ የተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 6.1 መካከል ልዩነት ቢኖር በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለፀው የበላይነት ይኖረዋል።

6.3 ተጫራቾች የጨረታ ሰነዶችን እንደአስፈላጊነቱ በጨረታ ሠነድ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ በሚጠየቀው መሠረት ክፍያ በመፈጸም ከመንግስት የኤልክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ማግኘት ይችላሉ።

6.4 ተጫራቾች በጨረታ ሰነዶቹ ውስጥ የተመለከቱትን ሁሉንም ማሳሰቢያዎች፣ ቅፆች፣ ቃላቶችንና መዘርዝሮችን ይመረምራሉ ተብሎ ይጠበቃል። አንድ ተጫራች በጨረታ ሰነዱ

የተጠየቁትን መረጃዎችና ሰነዶች አሟልቶ ካላቀረበ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከጨረታው እንዲወጣ ሊያደርገው ይችላል።

**7. *በጨረታ ሰነዱ ላይ የሚሰጥ ማብራሪያ***

7.1 በጨረታ ሰነዶቹ ላይ ማብራሪያ የሚፈልግ ተጫራች የመንግስት የኤልክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን ተጠቅሞ የሚፈልገውን ማብራሪያ በሲስተሙ መጠየቅ አለበት።

የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከጨረታ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን ውስብስብ ለሆነ 10 ቀን ውስብስብ ላልሆነ ግዥ ደግሞ 5 ቀናት በፊት ለደረሱት የማብራሪያ ጥያቄዎች በሙሉ በሲስተሙ ምላሽ ይሰጣል። የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በማብራሪያው ውጤት መሠረት የጨረታ ሰነዶቹን የሚያሻሽል ከሆነም ይህንኑ የሚያደርገው በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 8 እና ንዑስ አንቀጽ 26.2 የተመለከተውን ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ ነው።

7.2 በጨረታ ሂደትም ሆነ በጨረታ ግምገማ ወቅት ተቀባይነት የሚኖረው በመንግስትየኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት አማካኝነት የተሰጠ የማብራሪያ ጥያቄ መልስ ብቻ ነው። በሌላ አኳኋን ማለትም በቃል፣ በፅሑፍ፣ ወይም በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሠራተኛ ወይም በሌላ ተወካይ ወይም በሌላ ሦስተኛ አካል የተሰጡ መልሶች ወይም ማብራሪያዎች በግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት የተሰጡ ማብራሪያዎች ተደርገው አይቆጠሩም።

**8. *በጨረታ ሰነዶች ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ***

8.1 ግዥ ፈፃሚው አካል በራሱ ተነሳሽነት ወይም በተጫራቾች ጠያቂነት ምክንያት የጨረታ ሰነድን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጨረታ ማስረከቢያ ቀነ-ገደብ ከማለቁ በፊት የጨረታ ሰነዶቹን ሊያሻሽላቸው ይችላል።

8.2 ማንኛውም በግዥ ፈፃሚው አካል የተደረገ ማሻሻያ የጨረታ ሰነዱ አካል ሆኖ በጨረታው ለመሳተፍ በመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ለተመዘገቡ ተጫራቾች ያሳውቃሉ።

8.3 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጨረታ ሰነዱ ላይ በተደረገው ማሻሻያ ምክንያት ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን ለማዘጋጀትና ለማስረከብ በቂ ጊዜ አይኖራቸውም ብሎ ሲያምን በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 8.1 መሠረት የጨረታ ማቅረቢያ ቀነ-ገደብን ሊያራዝም ይችላል።

**9. *የቅድመ-ጨረታ ስብሰባ (ኮንፈረንስ)***

9.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነበት በጨረታው ለመሳተፍ በመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ከተመዘገቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ጋር የቅድመ ጨረታ የውይይት መድረክ በመንግስት የኤልክትሮኒክ ግዥ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡ ስብሰባው የሚካሄደው በጨረታ ሰነዶቹ ይዘት ላይ ለመወያየት፣ ማብራሪያ ለመስጠትና ሊሻሻሉ የሚገባቸው ሁኔታዎች ካሉም ለማየት ነው፡፡

9.2 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ቅድመ-ጨረታ ስብሰባ ለማዘጋጀት ሲያስብ በቅድሚያ ለተጫራቾች ስብሰባው የሚካሄድበትን ቀንና ሰዓት በጨረታ ሠነዱ የተጫራቾች ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

9.3 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተጫራቾች ያሉዋቸውን ጥያቄዎችና ማብራሪያዎች በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተመለከተው ቀንና ሰዓት መሠረት በሲስተም እንዲያቀርቡ ይጋብዛል፡፡

9.4 የቅድመ ጨረታው ውይይት በቃለ-ጉባኤ ይያዛል፡፡ ተጫራቾች በውይይቱ ውስጥ የተነሱትን ማብራሪያዎች በጨረታ ማቅረቢያቸው ማካተት ይችሉ ዘንድ ቃለ ጉባኤው የጨረታ ሰነዱን ለገዙ ሁሉ በሲስተም ይላክላቸዋል፡፡

### ሐ. የጨረታ ሠነድ አዘገጃጀት

**10.** ***በጨረታ የመሳተፍ ወጪ***

10.1 ተጫራቾች ከጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ማዘጋጀና ማስረከቢያ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን በሙሉ እራሳቸው ይችላሉ፡፡ የጨረታው ሁኔታም ሆነ ውጤት ምንም ይሁን ምን የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለነዚሁ ወጪዎች ተጠያቂ አይሆንም፡፡

**11.** ***የጨረታ ቋንቋ***

11.1 ጨረታውም ሆነ በተጫራቾችና በግዥ ፈፃሚ መ/ቤት መካከል የሚደረጉ ሁሉም የፅሑፍ ልውውጦች በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተጠቀሰው ቋንቋ መሠረት መሆን አለበት፡፡

11.2 በሌላ ቋንቋ የተዘጋጁ የመጫረቻ ሠነዶችና ደጋፊ ሰነዶች ሕጋዊና ብቃት ባለው ባለሙያ መተርጎም ይኖርባቸዋል፡፡ የትርጉሙ ኮፒ ከዋናው ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

11.3 ልዩነቱ ጥቃቅን ነው ብሎ ካላመነ በስተቀር በዋናው የመጫረቻ ሰነድና በተተረጐመው የመጫረቻ ሰነድ መካከል ልዩነት መኖሩ ሲታወቅ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የመጫረቻ ሰነዱን ውድቅ ያደርገዋል፡፡

**12.** *የጨረታ ዋጋዎችና ቅናሾች*

12.1 ተጫራቾች የሚያቀርቡአቸው ዋጋዎችና ቅናሾች በጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ ክፍል 4 በተመለከተው የጨረታ ቅፅ መሠረት መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

12.2 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የዋጋ ቅናሽ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

12.3 በክፍል 6 ላይ የተመለከቱት የአቅርቦት ፍላጐቶች በዝርዝር ሊቀመጡና ለእያንዳንዳቸው ዋጋ ሊቀርብላቸው ይገባል፡፡ የአቅርቦት ፍላጐቶች ተዘርዝረው ዋጋ ያልተሰጣቸው ከሆነ የነዚሁ ፍላጐቶች ዋጋ በሌሎች ፍላጐቶች ውስጥ እንደተካተተ ይቆጠራል፡፡ በዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ የአቅርቦት ፍላጐቶች የዋጋ አሰጣጥን በተመለከተ በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 33.2 መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

12.4 በጨረታ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ ላይ ተሞልቶ የሚቀርበው ጠቅላላ ዋጋ ማናቸውም ታክስ ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሆኖም በጨረታ ሠነድ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር በሁኔታዎች ላይ የተመሰረቱ ቅናሾች የጠቅላላ ዋጋው አካል ይሆናል፡፡

12.5 ተጫራቹ ያቀረባቸውን ቅናሾችና የአተገባበራቸውን ዘዴ በጨረታ ማስረከቢያው ሠንጠረዥ ውስጥ መጥቀስ ይኖርበታል፡፡

12.6 አለም አቀፍ የንግድ ቃሎች (የኢንኮተርም) እና ሌሎች ተመሳሳይ ቃሎች አረዳድ በተጫራቾች መመሪያና በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ዓለም አቀፍ የንግድ ም/ቤት በሚያሳትመው ወቅታዊ የኢንኮተርም ደንብ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

12.7 በዚህ አንቀጽ በተገለጸው መሠረት ለዕቃዎችና አገልግሎቶች የዋጋ ሠንጠረዥ ላይ የሚቀርበው ዋጋ በጥቅል ሳይሆን በዝርዝር መሆን አለበት፡፡ ይህም የሚሆነው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጨረታዎችን ለማወዳደር እንዲያመቸው ብቻ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ከዚህ በታች በተገለፁት ሁኔታዎች መሠረት ውል ለመዋዋል የሚያግደው አይሆንም፡፡

(ሀ) ለዕቃዎች

የቀረጥ፣ የሽያጭና ሌሎች የታክስ ክፍያዎችን ሳይጨምር ኢ.ኤክስ. ደብሊው (EXW) የተከፈለ ወይም የሚከፈል ዋጋ፣

ዕቃዎቹን በማምረት ወይም በመገጣጠም ሂደት የተከፈሉ ወይም ሊከፈሉ የሚገባቸው ሁሉንም የኢትዮጵያ ጉምሩክ ግዴታዎች፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሌሎች የታክስ ክፍያዎች፣

(ለ) ለአገልግሎቶች

የተያያዥ አገልግሎቶች ዋጋን፣

ከተያያዥ አገልግሎቱ ጋር በተያያዘ የተከፈሉ ወይም መከፈል ያለባቸው የኢትዮጵያ ጉምሩክ ግዴታዎች፣ የሽያጭና ሌሎች የታክስ ክፍያዎችን፣

12.8 ወቅታዊ የዋጋ መረጃ እንደቅደምተከተላቸው የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት፣ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የዋጋ መረጃ እንደሌለ ማረጋገጫ በሚሰጥበት ጊዜ እንደሁኔታው ከታወቀ አምራች፣ ይህም ካልሆነ ከመሥሪያቤቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መነሻ ባለስልጣኑ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በማዕከል በሚከናወን የገበያ ዋጋ ጥናት በሚገኝ የገበያ ዋጋ መረጃ መሰረት ለአቅራቢው የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

12.9 አጠቃላይ የውል ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተውን የዋጋ ማስተካከያ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላም ቢሆን የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል፡፡

12. 10 ቋሚ ዋጋን መሠረት አድርጎ የቀረበ ጨረታ ውድቅ አይደረግም፡፡ ነገር ግን ምንም ዓይነት የዋጋ ማሻሻያ አይደረግለትም፡፡

12.11 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ንዑስ አንቀጽ 1.3 ላይ በተመለከተው መሠረት ጨረታዎች በሎት (lot) ወይም በፓኬጅ (package) ደረጃ መቅረብ ይችላሉ፡፡ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ካልተገለፀ በስተቀር የሚቀርቡት ዋጋዎች በእያንዳንዱ ሎት (lot) ግዥ ውስጥ ከተዘረዘሩት የአቅርቦት ፍላጐቶችና መጠን ጋር ሙሉ በሙሉ (መቶ በመቶ) መጣጣም ይኖርባቸዋል፡፡ የዋጋ ቅናሽ የሚቀርበው በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 12.4 በተመለከተው መሠረት ሲሆን በጨረታ መክፈቻ ወቅት ለማሳወቅ በሚያስችል መልኩ በግልጽ መፃፍ ይኖርባቸዋል፡፡

12.12. ተጫራቹ ከሚያቀርቡት ዋጋ በተጨማሪ የእቃውን የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና (Life-Cost Analysis) መሠረት ያደረገ የሕይወት ዘመን ወጪ ዝርዝር በመለየት ማቅረብ አለበት፡፡

**13.** ***ዋጋ የሚቀርብባቸው የገንዘብ አይነቶች***

13.1 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ካልተገለፀ በስተቀር ተጫራቹ ዕቃዎቹንና አገልግሎቱን የሚያቀርበው ከሀገር ውስጥ ከሆነ ዋጋ ማቅረብ ያለበት በኢትዮጵያ ብር ነው፡፡

**14.** ***የተጫራቾች ሙያዊ ብቃትና አቅም***

14.1 የተጫራቾችን ሙያዊ ብቃትና አቅም ለማረጋገጥ እንዲቻል በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ በተመለከተውና በክፍል 4 የጨረታ ቅፆች ላይ ባለው የተጫራቾች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መሙያ ቅፅ ላይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሙላት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

**15.** ***የተጫራቾች የፋይናንስ አቅም***

15.1 ተጫራቹ ይህን የማዕቀፍ ስምምነት ለማከናወን በቂ የሆነ የፋይናንስ አቅም ያለው መሆኑን በሚያሳይ መልኩ የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በሚያዘው መሠረት በክፍል 4 የተመለከተውን የተጫራቾች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሞልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

15.2 ከላይ በንዑስ አንቀጽ 15.1 በተገለጸው መሠረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰነዶች አብረው መቅረብ አለባቸው፡፡

(ሀ) በኦዲተር የተረጋገጠ የፋይናንስ ማረጋገጫ
(ለ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የተመለከቱ ሌሎች ሰነዶች

**16.** ***የተጫራች ቴክኒካል ብቃት፣ ክህሎትና ልምድ***

16.1 ተጫራቹ የኩባንያውን አደረጃጀትና አጠቃላይ ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በክፍል 6 የተመለከቱትን የፍላጐቶች ዝርዝር በተገቢው ሁኔታ ለመፈፀም የሚያስችል ልምድና ችሎታ በተመሳሳይ ስራ መስክ ላይ ያለው መሆኑን በግልፅ ማሳየት ይኖርበታል፡፡ ተጫራቹ አሁን በእጁ ከሚገኙ ሌሎች ፕሮጀክቶች ጋር በማጣጣም በዚሁ ጨረታ ሰነድ ውስጥ የተመለከቱትን ሥራዎች እንዴት ለማስኬድ እንዳሰበና በምን ዓይነት ሁኔታ መሥራት እንደሚችል የሚያሳይ ዕቅድ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

16.2 መረጃው በክፍል 4 በሚገኘው የተጫራቾች አግባብነት ማረጋገጫ ቅፅ ላይ ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

16.3 ተጫራቹ ከዚህ በፊት ላከናወናቸው ተመሳሳይ ሥራዎች/አገልግሎቶች ከአሠሪው አካል የመልካም ሥራ ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡ ማስረጃው የተሰጡትን ኮንትራቶች በአግባቡ ማከናወኑን፣ እንዲሁም የኮንትራቱን መጠንና ዓይነት የሚያሳይ እና የማስረጃውን ትክክለኛነት ሊያረጋግጡ የሚችሉ ሰዎችን ስም፣ የሥራ ኃላፊነት፣ አድራሻ፣ ኢሜይልና ስልክ ቁጥር ጭምር ያካተተ መሆን አለበት፡፡ ማስረጃውን የሚሰጠው አካል የአሠሪው ፕሮጀክት አስተዳዳሪ ወይም በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ያለና የተጫራቹን ሥራ በውል የሚያውቅ መሆን ይኖርበታል፡፡ የግዥ ፈፃሚው አካል በጨረታ ግምገማ ወቅት እንደአስፈላጊነቱ ማስረጃ የሰጡትን አካላት ሊያነጋግር ይችላል፡፡

16.4 የሚቀርቡት የመልካም ሥራ ማስረጃዎች የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለባቸው፡፡

(ሀ) ኮንትራቱን የፈረሙት አካላት ስምና የተፈረመበት ቦታ
(ለ) የኮንትራቱን ዓይነት
(ሐ) የኮንትራቱን መጠን
(መ) ኮንትራቱ የተከናወነበትን ጊዜና ቦታ
(ሠ) ኮንትራቱ በአጥጋቢ ሁኔታ ስለመከናወኑ

16.5 አንድ ተጫራች ከአሠሪው አካል የመልካም ሥራ አፈፃፀም ማስረጃ ባያቀርብም እንኳ ሥራውን በአጥጋቢ ሁኔታ ማከናወኑን ከገለፀና የመልካም ሥራ አፈፃፀም ማስረጃ እንዲሰጠው ለአሰሪው አካል ጥያቄ ያቀረበበትን ማስረጃ ካቀረበ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል፡፡

16.6 ተጫራቹ ወይም ተጫራቾቹ ያቀረቡት በሽርክና (በጋራ ማህበር) ከሆነ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መረጃዎች በሙሉ ለሁሉም የማህበሩ አካላት መገለፅ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጨረታው የእያንዳንዱ ማህበር አባል የይሁንታ ድጋፍ ማስረጃ መካተት ይኖርበታል፡፡

16.7 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በሌላ ሁኔታ ካልተጠቀሰ በስተቀር የግዥ ፈፃሚው አካል የተጫራቹን ወቅታዊ የቴክኒክ ብቃትና አቅም ይህን የማዕቀፍ ስምምነት ለመፈፀም የሚያስችል መሆኑን በአካል ጭምር በመገኘት ሊያጣራ ይችላል፡፡

## 17. *የቴክኒክ ብቃት ማስረጃ ሰነዶች*

17.1 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ተጫራቹ የሚቀርቡት ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች ከጨረታ ሰነዶች ጋር መጣጣማቸውን ለማረጋገጥ በፍላጐት መግለጫ ክፍል 6 ውስጥ የተገለፁትን የማስረጃ ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡፡

17.2 የማስረጃ ሰነዶች አይነት የሚቀርበው በፅሑፍ፣ በስዕል ወይም በመረጃ መልክ ሆኖ ዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ መሠረታዊ የቴክኒክ የአሠራር ባህሪዎቹን ዝርዝር መግለጫ የያዙ መሆን ይኖርባቸዋል። እነዚህ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በፍላጐት መግለጫው ላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ፍላጐቶች የሚያሟሉ መሆናቸውን ማሳየት ያስፈልጋል። የማያሟሉ ከሆነም የልዩነት ነጥቦቹ በትክክል መገለፅ ይኖርባቸዋል።

17.3 የግዥ ፈፃሚው አካል በፍላጐት መግለጫው ውስጥ የሚያስቀምጣቸው የባለሙያዎች ደረጃ፣ የሥራ ሂደቶች፣ ዕቃዎችና መሣሪያዎች እንዲሁም የምልክት ስሞች ወይም ካታሎጎች (Catalogues) ገላጮች እንጂ ገዳቢ መሆን የለባቸውም። ተጫራቾች በግዥ ፈፃሚው አካል ተቀባይነት እስካላገኘ ድረስ በፍላጐት መግለጫው ውስጥ የተጠቀሱትን በአቻነት የሚመጥኑ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የጥራት ደረጃዎች፣ ስሞችና የካታሎግ ቁጥሮች በአማራጭ ማቅረብ ይችላሉ።

**18.** *የናሙናዎች አቀራረብ*

18.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በዚህ የጨረታ ሰነድ መሠረት የሚቀርቡ ዕቃዎች ናሙና እንዲመረት ወይም ከእያንዳንዱ ምርት ወይም ከሁሉም ናሙና እንዲቀርብለት የመጠየቅ መብት አለው። ተጫራቹ የተጠየቁትን ናሙናዎች ማቅረብ ካልቻለ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከጨረታ ውድድር ሊያስወጣው ይችላል። ተጫራቹ የሚያቀርባቸው ናሙናዎች ከሚቀርቡት ዕቃዎች ጋር ተመሳሳይ ወይም የበለጠ የጥራት ደረጃ ያላቸው መሆኑን ዋስትና መስጠት አለበት። በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የተጠየቁት ናሙናዎች ከክፍያ ነፃና በወቅቱ መቅረብ አለባቸው።

18.2 በንኡስ አንቀጽ 18.1 የተገለጸው ቢኖርም ተጫራቾች የተሟላ ናሙና በአካል ማቅረብ የማይችሉ ከሆነ እና የማይችሉበትንም ምክንያት የመንግስት መ/ቤቱ ሲቀበለው ስለናሙናው ያላቸውን መረጃ ማቅረብ እንዲችሉ ሊፈቅድ ይችላል።

18.3 ግዥ ፈፃሚው አካል የሚቀርቡት ዕቃዎች ናሙና እንዲመረት ወይም እንዲቀርብለት ተጫራቾችን የሚጠይቀው የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ሲሆን ናሙናዎቹ መቅረብ ያለባቸው መቼና የት ቦታ እንደሆነ፣ እንዲሁም በግልፅ መታየት ያለባቸው መቼ እንደሆነ ያሳውቃል።

18.4 ግዥ ፈፃሚው አካል ናሙናዎቹን በጥንቃቄ መያዝና መመርመር አለበት። ነገር ግን በናሙናው የተፈጥሮ ሁኔታ ምክንያት ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ለአቅራቢው ካሣ ለመክፈል አይገደድም። ያልጠፉ ወይም ያልተበላሹ ናሙናዎች ግን ጨረታውን ላላሸነፉ ተጫራቾች

መመለስ አለባቸው። ጨረታውን ያላሸነፉ ተጫራቾች ያቀረቧቸው ናሙናዎች በ 6 ወር ጊዜ ውስጥ እንዲመለሱላቸው ካልጠየቁ በግዥ ፈፃሚው አካል ይወረሳሉ፣ ይወሰዳሉ።

18.5 በንዑስ አንቀጽ 18.4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጫራቾች የቀረቡ ናሙናዎች ከፍተኛ ጋር ከተያያዙ ምክንያቶች ውጭ በአያያዝ እና አጠቃቀም ጉድለት ቢበላሽ፣ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ተጠያቂነት ይኖርበታል።

18.6 በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር በአሸናፊ ተጫራች የቀረቡት ናሙናዎች የግዥ ሂደቱ እስኪያልቅ ድረስ ላይመለሱ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው ናሙናዎቹ ከቀረቡት ዕቃዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማጣራት ይቻል ዘንድ ነው።

**19.** ***<u>የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበር</u>***

19.1 ተጫራቹ **የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበር** ከሆነ እንደ አንድ ተጫራች ተደርጎ ይቆጠራል። እነዚህ ማህበራት ከመካከላቸው እንደ መሪ ሆኖ የሚሰራ አንድ ሰው ይወክላሉ። **የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበር** የተወከለው/ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ውል ይፈርማል። ሆኖም የማህበሩ አባላት የጋራና የተናጠል ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል። ጨረታ ከቀረበ በኋላ ያለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ዕውቅና **የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበሩን** ጥምረት መቀየር አይቻልም።

19.2 ውሉን ለመፈራረም **የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበሩ** የተወከለ ሰው መወከሉን የሚያረጋግጥ ሕጋዊ ሰነድ ለግዥ ፈፃሚው አካል ማቅረብ ይኖርበታል። ሕጋዊ ሰነዱ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠና **የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበሩ_** ስም መፈረም የሚያስችል መሆን ይኖርበታል። እያንዳንዱ የማህበሩ አባልም የግዥ ፈፃሚውን አካል በሚያረካ ሁኔታ አስፈላጊ የሆኑት የሕግ፣ የቴክኒክና የፋይናንስ ፍላጐቶች መሟላታቸውንና አገልግሎቱን በአግባቡ ለመስጠት የሚያስችሉ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባቸዋል።

**20.** *አማራጭ ጨረታዎች*

20.1 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር አማራጭ ጨረታዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

20.2 አማራጭ ጨረታ እንዲቀርብ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የተፈቀደ ከሆነም ግዥ ፈፃሚው አካል አሸናፊው ተጫራች ከመለየቱ በፊት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማረጋገጥ ይኖርበታል።

(ሀ) የቀረበው የመጫረቻ ሰነድ የግዥ ፈፃሚው አካል ያወጣውን የጨረታ ሰነድ መሠረት ያደረገ መሆኑን፣

(ለ) የቀረቡት አማራጭ ጨረታዎች የግዥ ፈፃሚው አካል ያወጣውን የጨረታ ሰነድ መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን፣

(ሐ) የቀረቡት አማራጭ ጨረታዎች ከዋናው ጨረታ ጋር ሲገናዘቡ ሊያስገኙ የሚችሉት ኢኮኖሚያዊና ቴክኒካዊ ጠቀሜታ በሚያሳምን ሁኔታ መቅረቡን፣

(መ) የቀረቡት አማራጭ ጨረታዎች ለግምገማ የሚረዳ ዝርዝር መግለጫ (የቁጥር ስሌቶች፣ የቴክኒክ ዝርዝር መግለጫዎች፣ የዋጋ ዝርዝሮች፣ የአሠራር ዘዴዎችና ሌሎች ተዛማጅ መግለጫዎች) ማካተታቸውን።

20.3 ግዥ ፈፃሚው አካል የዘጋጀውን የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የሚያሟላና ዝቅተኛ ዋጋ የሰጠው ተጫራች ያቀረበው የቴክኒክ አማራጭ ብቻ ግምት ውስጥ ይገባል።

20.4 የግዥ ፈፃሚው አካል አማራጭ ጨረታዎችን የሚገመግመው በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥና በክፍል 3 በተመለከቱት የግምገማ ዘዴዎችና መስፈርቶች መሠረት ይሆናል።

20.5 በግዥ ፈፃሚው አካል ያልፈቀዱ አማራጭ ጨረታዎች ውድቅ ይሆናሉ።

## 21. ጨረታዎች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜ

21.1 ጨረታዎች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከወሰነው የጨረታ ማስረከቢያ ቀነ-ገደብ በኋላ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሰው ጊዜ ፀንተው ይቆያሉ። ለአጭር ጊዜ ብቻ ፀንተው የሚቆዩ ጨረታዎችን የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ብቁ እንዳልሆኑ ቆጥሮ ሊሰርዛቸው ይችላል።

21.2 በልዩ ሁኔታዎች ምክንያት ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተጫራቾች የጨረታዎቻቸውን ፀንቶ መቆያ ጊዜ እንዲያራዝሙ ሊጠይቅ ይችላል። ጥያቄውና መልሱ የመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን በመጠቀም የሚፈፀም ይሆናል።

21.3 ተጫራቹ የማራዘም ጥያቄውን ባይቀበለው ጨረታው ውድቅ የሆናል። ሆኖም ያስያዘው የጨረታ ዋስትና ሊወረስበት አይችልም።

21.4 ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማራዘም የተስማሙ ተጫራቾች ያራዘሙበትን ጊዜ በመጥቀስ ስምምነታቸውን በሲስተም ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናም በተመሳሳይ ሁኔታ መራዘም ይኖርበታል ወይም አዲስ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

21.5 ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማራዘም ያልተስማማ ተጫራች የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ጥያቄ ለመፈፀም አምቢተኛ እንደሆነ ተቆጥሮ ያቀረበው የመጫረቻ ሠነድ ውድቅ እንዲሆንና ከውድድሩ እንዲወጣ ይደረጋል።

## 22. *የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና*

22.1 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ተጫራቾች በጨረታ ዘርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የተገለፀውን የገንዘብ ዓይነት መጠን የሚያሟላ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

22.2 የጨረታው ዋስትና በተጫራቹ ምርጫ ከሚከተሉት ዓይነቶች አንዱ ሊሆን ይችላል።

(ሀ) በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና፣

(ለ) በማይሻር ሌተር ኦፍ ክሬዲት የቀረበ ዋስትና፣

(ሐ) በታወቀ ባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ

ሁሉም ዓይነት የዋስትና ሰነዶች ከታወቀ ምንጭ መሆን አለባቸው። የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናው በጨረታ ቅፆች ክፍል 4 ውስጥ የተካተተውን ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ተመሳሳይ የዋስትና ቅጽ በመጠቀም ይቀርባል። በየትኛውም መልኩ ቅፁ የተጫራቹን ሙሉ ስም ማካተት መቻል አለበት። የጨረታ ዋስትናው ጨረታው ፀንቶ ከሚቆይበት ጊዜ በኋላ ለተጨማሪ 28 ቀናት ፀንቶ መቆየት ይኖርበታል።

22.3 በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት በጨረታ ማስከበሪያ ምትክ ማህበራቱን ካደራጃቸው የመንግስት ተቋም የሚሰጥ የጨረታ ማስከበሪያ የድጋፍ ደብዳቤ ሊያቀርቡ ይችላሉ። በዚህ መልኩ የሚቀርበው የድጋፍ ደብዳቤ ዋስትና የተሰጠበትን የገንዘብ መጠን በመጥቀስ ማህበራቱን ባደራጃቸው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የተፈረመ መሆን አለበት። በተጨማሪም በግዥ አፈጻጸም መመሪያ ላይ ባለው መተማመኛ ቅጽ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው።

22.4 በሽርክና፣ በጥምረት ወይም በአሽሙር ማህበርየሚቀርብ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በጋራ ማህበሩ መሪ ወይም በጋራ ማህበሩ ስም ወይም በሁሉም የማህበሩ አባላት ስም መዘጋጀት ይኖርበታል። በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 22.7 መሠረት ከጨረታ ዋስትና ጋር በተያያዘ ምክንያት ዕገዳ ቢጣል በሁሉም የማህበሩ አባላት ላይ ተፈፃሚ የሆናል።

22.5 በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 22.1 መሠረት ተጠይቆ ከሆነ ተቀባይነት ባለው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተደግፎ ያልቀረበ ጨረታ ግዥ ፈፃሚው አካል ውድቅ ሊያደርገው ይችላል።

22.6 የጨረታው አሸናፊ በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 47 መሠረት የውል ማስከበሪያ ዋስትና እንዳቀረበ የተሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ወዲያውኑ ተመላሽ ይደረግላቸዋል።

22.7 የአሸናፊው ተጫራች ጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተጫራቹ ውሉን እንደፈረመና ተፈላጊውን የውል ማስከበሪያ ዋስትና እንዳቀረበ ወዲያውኑ ተመላሽ ይደረግለታል።

22.8 የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ሊወረስ የሚችለው፦

(ሀ) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 21.2 ውስጥ በተመለከተው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ተጫራቹ በጨረታ ማቅረቢያ ሰነድ ውስጥ በተጠቀሰውና ጨረታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ከጨረታው ከወጣ፣ ወይም

(ለ) አሸናፊው ተጫራች ቀጥለው የተመለከቱትን ሳይፈፅም ሲቀር፦

በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 45 መሠረት ውል መፈረም፣

በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 47 መሠረት የውል ማስከበሪያ ማስከበሪያ ዋስትና ማቅረብ፣

(ሐ) በግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ተጫራቹ በመ/ቤቱ የተደረገውን የሂሳብ ስሌት ስህተት ማስተካከያ ለመቀበለል ፈቃደኛ ካልሆነ፣

23. ከመጫረቻ ሰነድ ጋር መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች

23.1 ሁሉም የሚቀርቡት የመጫረቻ ሰነዶች በክፍል 4 የጨረታ ቅፆች መሠረት ሆነው በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የተጠቀሱትን ፍላጐቶችና ከዚህ በታች የተመለከቱትን የተጫራቾችን ብቁነት የሚያረጋግጡ ሠነዶችን ማሟላት ይኖርባቸዋል።

ሀ) በሚመለከተው አካል የተሰጠ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ሰርቲፊኬት

ለ) በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ ወቅታዊ የታክስ ክፍያ ሰርቲፊኬት

ሐ) የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድና የንግድ ምዝገባ ሰርቲፊኬት እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ አግባብነት ያለው የሙያ ብቃት ሰርቲፊኬት

መ) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 24.2 በተመለከተው መሠረት በኩባንያው ወይም በጋራ ማህበሩ ወይም በጊዜያዊ ማህበሩ የተመረጠው ሰው ስምና ጥምረቱን ወክሎ መፈረም የሚችል መሆኑን የሚያስረዳ በሚመለከተው አካል የተሰጠ ሕጋዊ ውክልና፣

ሠ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ንዑስ አንቀጽ 15.2 መሠረት የተጫራቹን የፋይናንስ አቅም የሚያሳይ ሰነድ፣

ረ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ንዑስ አንቀጽ 16.3 በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ተጫራቹ ቢያንስ አሁን ከተወዳደረበት የውል ዋጋ ጋር የሚመጣጠን ሥራ በአግባቡ የሠራ መሆኑን የሚያስረዳ ከዚህ በፊት ከሠራባቸው አካላት የተሰጠ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ሰርቲፊኬት፣

ሰ) በክፍል 6 በተመለከተው የፍላጐት መግለጫ፣ የቴክኒክ አቅርቦትና መግለጫ ሠንጠረዥ በዝርዝር መቅረብ አለበት። ዝርዝር መግለጫው ቢያንስ ለታቀደው ግዥ የተጠየቀውን አነስተኛ የቴክኒክ ፍላጐት ማሟላት መቻል አለበት። ቀጥለው የተመለከቱት ወሳኝ ሰነዶችም አብረው ይቀርባሉ።

I. በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 17 መሰረት የቴክኒክ መግለጫ ጽሑፍ (በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ከተጠየቀ)፣

II. በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጸ 25 መሰረት በድርጅቱ የቀረበ ዋስትና (Warranty)፣

(ሸ) ተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 5.6 መሰረት ምርቱ የአምራች ኩባንያው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ፣

(ቀ) በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 22 መሠረት የጨረታ ዋስትና፣

(በ) በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 20 መሠረት አማራጭ ጨረታዎች (የተፈቀደ ሲሆን ብቻ) ፣

(ተ) በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 35 መሰረት የልዩ አስተያየት ገደብ ተጠቃሚ የሚሆኑ የሀገር ውስጥ ተጨራቾች ለዚሁ የሚረዱ አስፈላጊ መረጃዎችን ሁሉ ማቅረብ አለባቸው።

(ቸ) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.1 መሠረት ጨረታው የቀረበው **የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የአሽሙር ማህበር**) ሲሆን የመረጃ ቅፅ፣ የጋራ ማህበሩ የተቋቋመበት ስምምነት ወይም ደብዳቤ ወይም ረቂቅ ስምምነት፣

(ነ) በክፍል 4 የተመለከቱትን የጨረታ ቅፆች መሠረት በማድረግ ዕቃዎቹን ወይም አገልግሎቶቹን ለማቅረብ የቀረበ የዋጋ ዝርዝር፣

(ኘ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ መሠረት ሌሎች ተጫራቾች ማቅረብ ያለባቸው ሰነዶችና መረጃዎች፡፡

**24.** *የጨረታ ቅፆችና አቀራረብ*

24.1 ተጫራቹ በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 23 ውስጥ የተገለጹትን በማካተት የመጫረቻ ሠነዳቸውን የመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን ተጠቅመው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

24.2 የመጫረቻ ሠነዱ ድርጅቱን በመወከል ለማዘጋጀት ስልጣን በተሰጠው አካል መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

**25.** *የጨረታ ማቅረቢያ ቀነ-ገደብ*

25.1. የመጫረቻ ሰነዶች በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ የተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ከማለፉ በፊት በመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት መቅረብ አለበት፡፡

25.2 ግዥ ፈፃሚው አካል በራሱ ኃላፊነትና ተነሳሽነት በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 8 መሠረት የጨረታ ሰነዶችን በማሻሻል የጨረታ ማቅረቢያ ቀነ-ገደብን ማራዘም ይችላል፡፡ ይህም በሆነበት ጊዜ የግዥ ፈፃሚው አካል እና ቀደም ሲል በነበረው የጊዜ ገደብ መሠረት የነበሩ ተጫራቾች መብቶችና ግዴታዎች በተሻሻለው ሰነድ መሠረት ይሆናል፡፡

**26.** *ጨረታዎችን መሰረዝ፣ መተካትና ማሻሻል*

26.1 ተጫራቹ የጨረታ መክፈቻ ቀነ ገደብ ከመጠናቀቁ በፊት የመጫረቻ ሠነዱን ማሻሻል ወይም ከጨረታው መውጣት ይችላል፡፡

**27.** *የጨረታ አከፋፈት*

27.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጨረታውን የሚከፍተው በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት መሠረት የኤልክትሮኒክ ሥርዓት ይሆናል፡፡

27.2 በተጫራቾች የቀረቡ ሠነዶች ተከፍተው የተጫራቾቹ ስም፣ የጨረታ ዋጋዎች፣ ቅናሾችም (ካሉ) እና ተለዋጭ የዋጋ ሀሳቦች (ካሉ)፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ማቅረብ አስፈላጊ ከሆነ እንዲሁም ሌሎች ግዥ ፈፃሚው አካል አግባብነት አላቸው የሚላቸው ዝርዝሮች የጨረታ አከፋፈት ሂደቱን በሲስተም ለሚከታተሉ ተጫራቾች ወይም ተወካዮች እና ሌሎች ሂደቱን እንዲከታተሉ ለተጋበዙ አካላት ይነበል፡፡ በጨረታ መክፈቻው ላይ የተነበቡ ቅናሾችና አማራጭ የዋጋ ሀሳቦች ብቻ ለግምገማ ዕውቅና ያገኛሉ፡፡

27.3 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጨረታ መክፈቻውን ሂደት በቃለ-ጉባዔ ይመዘግባል፡፡ ቃለ-ጉባዔው የተጫራቹን ስም፣ የጨረታ ዋጋውን ከተቻለ በየጥቅሉ (ካለ) ፣ ማንኛቸውንም ቅናሾችና አማራጭ የዋጋ ሀሳቦች፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና መኖርና ያለመኖር ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

27.5 ማንኛውም በጨረታ መክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ወቅት ያልተከፈተና ያልተነበበ የጨረታ ሰነድ ለቀጣይ ግምገማ ሊቀርብ አይችልም፡፡

### ሠ. ጨረታዎችን መገምገምና ማወዳደር

**28.** *ምስጢራዊነት*

28.1 የጨረታው ውድድር አሸናፊ በይፋ ለሁሉም ተጫራቾች እስካልተገለጸ ድረስ የጨረታ ምርመራን፣ ግምገማን፣ ምዘናን፣ ድህረ-ብቁነትና የጨረታ አሸናፊነት ሀሳብን የሚመለከት መረጃ ለተጫራቾችም ሆነ ሌሎች ጉዳዩ ለማይመለከታቸው ግለሰቦች ማሳወቅ የተከለከለ ነው፡፡

28.2 በጨረታ ምርመራ፣ ግምገማ፣ ምዘናና ድህረ-ብቃት ወይም ውል አሰጣጥ ወቅት የግዥ ፈፃሚውን ውሳኔ ለማስቀየር ተጫራቹ የሚያደርገው ማናቸውም ጥረት ከጨረታ ለመሠረዝ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

28.3 የተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 28.2 ቢኖርም ከጨረታው መከፈት እስከ ውል መፈራረም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ማንኛውም ተጫራች ከጨረታው ሂደት ጋር በተያያዘ በማንኛውም ጉዳይ ላይ የግዥ ፈፃሚውን ማግኘት ሲፈልግ የሚፈልገውን ነገር የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ማቅረብ አለበት፡፡

**29.** *የማብራሪያ ጥያቄ አቀራረብ*

29.1 ግዥ ፈፃሚው ከጨረታ ምርመራ፣ ግምገማ፣ ምዘናና ድህረ ብቃት ሂደት ጋር በተያያዘ ግልፅ ባልሆኑት ጉዳዮች ዙሪያ ተጫራቾች ማብራሪያ እንዲሰጡት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ለቀረበው

ጥያቄ በተጫራቹ የተሰጠው ምላሽ ወይም ማብራሪያ ተገቢ ሆኖ ካልተገኘ ግምት ውስጥ አይገባም። የማብራሪያ ጥያቄውና መልሱም የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም መሆን አለበት። በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 34 መሠረት የሒሳብ ስሌትንና ሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮችን አስመልክቶ ብቻ የቀረበ ማብራሪያ ካልሆነ በስተቀር በቀረበው ዋጋ ወይም በጨረታው ላይ መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ማብራሪያ ወይም ለውጥ ተቀባይነት አይኖረውም።

29.2 ተጫራቹ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለቀረበለት የማብራሪያ ጥያቄ ወቅታቂ ምላሽ ካልሰጠ የተጫራቹ የመጫረቻ ሠነድ ውድቅ ሊደረግበት ይችላል።

## **30.** *ተቀባይነት ያላቸው የመጫረቻ ሠነዶች*

30.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተጫራቹ ያቀረበውን የመጫረቻ ሃሳብ ብቁነት የሚወስነው ለተጫራቾች የተሰጠውን የጨረታ ሰነድ ይዘት መሠረት በማድረግ ነው።

30.2 ብቃት ያለው የመጫረቻ ሠነድ ማለት ከሁሉም የውል ቃሎችና ሁኔታዎች፤ ከተጠየቀው ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ (ስፔስፊኬሽን) እና የመገምገሚያ መስፈርት ጋር የሚጣጣምና ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለበት ነው። ጉልህ ልዩነት፣ አለማሟላት ወይም ግድፈት የሚወሰነው፦

(ሀ) ጨረታው ተቀባይነት ቢያገኝ፤

በውሉ ውስጥ የተጠቀሱ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ወሰን፣ ጥራት ወይም አፈፃፀም ላይ የጎላ ልዩነት ይፈጥራል ተብሎ ሲታሰብና፣

በውሉ ውስጥ የተጠቀሱ የግዥ ፈፃሚውን መብቶች ወይም የተጫራቹን ግዴታዎች የማዛባት እና ከጨረታ ሰነዶች ጋር ያለመጣጣም ሁኔታ ሲፈጠር፤ ወይም

(ለ) ጨረታው ተቀባይነት ያገኘው በጨረታው ግምገማ ወቅት የታዩ መሰረታዊ ግድፈቶች እንዲስተካከሉ ተደርጎ ከሆነ ከሌሎች ተጫራቾች መብት ጋር በተያያዘ ሚዛናዊነትን የማፋለስ ውጤት ያስከትላል ተብሎ ሲገመት ነው።

30.3 አንድ የመጫረቻ ሠነድ በጨረታ ሰነድ ላይ የተጠቀሱና ወሳኝ የሆኑ የፍላጎት መግለጫዎችን የማያሟላ ከሆነ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውድቅ ያደርገዋል። ውድቅ ከተደረገ በኋላ ተጫራቹ ያላሟላቸውን መሰረታዊ ግድፈቶች እንዲያሟላ በማድረግ ብቁ ሊያደርገው አይችልም።

30.4 ብቁ ያልሆኑ የመጫረቻ ሠነዶች ብቁ ያልሆኑበት በቂ ምክንያቶች በግምገማ ሪፖርት ውስጥ በግልፅ መመልከት ይኖርበታል፡፡

30.5 የጨረታው ሰነድ የሚጠይቃቸው ፍላጐቶች አሟልቶ የተገኘው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆን የቀረበው የመጫቻ ሠነድ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጥያቄዎች መሠረታዊ መልስ የሚሰጥ እስከሆነና የቀረበው ዋጋም ካለው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ያነሰ ወይም ተመጣጣኝ ሆኖ ከተገኘ እንዲሁም የተዘጋጀው የጨረታ ሠነድ የሌሎች ተጫራቾችን የመወዳደር መብት የማይገድብ መሆኑ ከተረጋገጠ ከተጫራቹ ጋር ውል ሊፈጸም ይችላል፡፡

**31.** *አለመጣጣምና ግድፈቶች*

31.1 የመጫረቻ ሠነዱ በመሠረቱ አጥጋቢ ከሆነ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መሠረታዊ ያልሆኑ ያለመጣጣሞችን ወይም ግድፈቶችን ሊያልፋቸው ይችላል፡፡

31.2 የመጫረቻ ሠነዱ አጥጋቢ ከሆነ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መሠረታዊ ያልሆኑ አለመጣጣሞችን ወይንም ግድፈቶችን ለማስተካከል ተጫራቹን ተፈላጊ መረጃ ወይም ሰነድ በሚፈለገው ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል፡፡ ሆኖም የሚደረገው ማስተካከያ ከጨረታው ዋጋ ጋር መያያዝ የለበትም፡፡ ተጫራቹ በተጠየቀው መሠረት ተስማምቶ አስተካክሎ ካላቀረበ ከጨረታው ሊሠረዝ ይችላል፡፡

31.3 የመጫረቻ ሠነዱ አጥጋቢ ከሆነ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መሠረታዊ ያልሆኑ አለመጣጣሞችንና ግድፈቶችን ሊያስተካክል ይችላል፡፡ ተዘለው ወይም በሌላ ያልተሟላ አቀራረብ ምክንያት ዋጋ ያልተሰጠባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለውድድር ዓላማ ሲባል ብቻ ለተጠቀሱት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በጨረታ ወቅት የቀረበ ከፍተኛ ዋጋ ተወስዶ ማስተካከያ እንዲሰላላቸው ይደረጋል፡፡

**32.** *አጠራጣሪ የጨረታ ዋጋዎችና የሂሳብ ስሌት ስሀተቶች*

32.1 የመጫረቻ ሠነዱ በመሠረቱ አጥጋቢ መሆኑ ከታወቀ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሂሳብ ስሌት ስህተቶችን በሚከተሉት መሠረት ያስተካክላል፡፡

(ሀ) በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አስተያየት የዴሲማል ነጥብ አቀማመጥ ስህተት ካልሆነ በስተቀር በነጠላ ዋጋውና በተፈላጊው በመጠን ተባዝቶ በሚገኘው ጠቅላላ ዋጋ መካከል ልዩነት ከመጣ የነጠላ ዋጋው የበላይነት ይኖረዋል፡፡ ጠቅላላ ዋጋ በአንፃሩ ይስተካከላል፡፡ በግዥ ፈፃሚው አስተያየት መሠረት በነጠላ

ዋጋ ውስጥ የዴሲማል ነጥቦች አቀማመጥ ተዛብቷል ብሎ ካመነ ጠቅላላ ዋጋው የበላይነት ያገኛና የአንዱ ዋጋ በዚያው መጠን ይስተካከላል።

(ለ) የንዑሳን ድምሮች ወይም ቅናሾች ተዛማጅ በሆነው ጠቅላላ ድምር ላይ ስህተት ካለ ንዑሳን ድምሮች እንዳሉ ተወስደው ጠቅላላው ድምር በዚያው መሠረት ይስተካከላል።

(ሐ) በቁጥሮችና በቃላት መካከል ልዩነት ከታየ በፊደል የተገለፀው ቁጥር ይወሰዳል። በፊደል የተገለፀው ቁጥር ከሂሳቡ ስህተት ጋር የተየያዘ ከሆነ ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" ላይ በተገለፀው መሠረት በቁጥር የተገለፀው የበላይነት ይኖረዋል።

34.2 በተደረገው የሂሳብ ስህተት ስሌት ተጫራቹ ካቀረበው የመጫረቻ ዋጋ ከ 10% (አስር በመቶ) በላይ ከሆነ ተጫራቹ ከውድድር ውጭ ይደረጋል።

34.3 በንዑስ አንቀጽ 34.2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የተገኘው የሂሳብ ስህተት ሥሌት ከ 10% በታች ከሆነ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተገኙትን የሂሳብ ስሌት ስህተቶች በማረም ወዲያውኑ ለተጫራቹ የኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ያሳውቃል። ተጫራቹ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ጠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት እርማቱን መቀበል አለመቀበሉን ከተጠየቀበት ቀን ጀምሮ በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል። ሆኖም ተጫራቹ በሒሳብ ስህተት ስሌት ማስተካከያው የማይስማማ ከሆነ የጨረታ ማስከበሪያ ተወርሶ ከጨረታው እንዲወጣ ይደረጋል።

**33.** *ልዩ አስተያየት*

33.1 ልዩ አስተያየት የሚደረገው በኢትዮጵያ ውስጥ ለተመረቱ ዕቃዎች፣ ከምክር ወጪ ለሆኑ አገልግሎቶች፣ በማምረት ስራ ላይ ለተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት፣ ለአካል ጉዳተኞች እና የነጋዴ ሴቶች ማህበራት እንዲሁም ለቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች ይሆናል።

33.2 በሀገር ውስጥ ለተመረቱ ዕቃዎች ልዩ አስተያየት ተግባራዊ የሚሆነው የዋጋዎች ውድድርና ግምገማ በሚደረግበት ጊዜ የወጭ ምርት በሆኑት ዕቃዎች ላይ የተፈቀደውን የልዩ አስተያየት ምጣኔ በመጨመር ሲሆን፣ የሚደረገው የተጨማሪ እሴት እና የልዩ አስተያየት ምጣኔ እንደሚከተለው ይሆናል።

| የተጨማሪ እሴት ምጣኔ | የሚሰጥ ልዩ አስተያየት መጠን |
|---|---|
| ከ 20%- 35% | 10% |
| 36%- 50% | 11% |
| 51% -65% | 12% |
| 66%- 80% | 13.5% |

81% - 100% 15%

33.3 በንዑስ አንቀጽ 35.2 በተመለከተው መሠረት ልዩ አስተያየት ተግባራዊ የሚሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ እሴት ተጨምሮባቸው የተሰሩ ለመሆናቸው በተመሰከረለት ኦዲተር ሲረጋገጥ ነው።

33.4 በዚህ አንቀጽ መሰረት የልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ለመሆን የሚቀርበው የታከለ እሴት የተጋነነ፣ የተጭበረበረ ወይም የሀሰት መረጃዎችን ያቀረበ ተጫራች ተጠያቂ ይሆናል።

33.5 ለዚህ ንዑስ አንቀጽ 35.2 ዓላማ ሲባል በኢትዮጵያ የታከለው እሴት የሚሰላው ከጠቅላላ ወጪ ላይ ከውጭ አገር ለሚመጡ ጥሬ ዕቃዎች እና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሁም ከውጭ አገር ለተገኘ አገልግሎት የተደረገ ወጪ ተቀንሶ የሚቀረው ወጪ ሲሆን፣ በምርት ላይ የሚከፈሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን አይጨምርም።

33.6 አግባብነት ባለው አዋጅ የተቋቋሙ እና በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ከሀገር ውስጥ ተጫራቾች ጋር በሚወዳደሩበት ጊዜ የ 3% ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል።

33.7 በማምረት ሥራ ለተሰማሩ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ከሀገር ውስጥ ተጫራቾች ጋር በሚወዳደሩበት ጊዜ የ 3% ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል።

33.8 በማምረት ሥራ ላይ ለተሰማሩ የነጋዴ ሴቶች ማህበራት ከሀገር ውስጥ ተጫራቾች ጋር በሚወዳደሩበት ጊዜ የ 3% ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል።

33.9 የቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶችን ለማቅረብ ከሀገር ውስጥ ተጫራቾች ጋር በሚወዳደሩበት ጊዜ የ 5% ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል።

**34.** ***የመጀመሪያ ደረጃ የጨረታዎች ግምገማ***

34.1 የግዥ ፈፃሚው አካል በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 23 በተመለከተው መሠረት የተጠየቁት ሁሉም ሰነዶች መቅረባቸውንና የቀረቡት ሰነዶችም የተሟሉ መሆናቸውን ለመወሰን ሰነዶቹን መመርመር አለበት።

34.2 ጨረታው ከተከፈተበት እስከ ኮንትራት ስምምነት ፊርማ ድረስ ባለው ጊዜ ማንኛውም ተጫራች ከቀረበው የመጫረቻ ሰነድ ጋር በተያያዘ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ማድረግ የለበትም። በምርመራና በግምገማ ሂደት ወቅት፤ የተጫራቾች አንፃራዊ ደረጃ በሚወጣበት ወቅትና የጨረታው አሸናፊ በሚወሰንበት ሂደት ውስጥ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ላይ ጫና የሚፈጥር ማንኛውም ተጫራች የመጫረቻ ሠነዱ ውድቅ ይደረግበታል።

34.3 የግዥ ፈፃሚው አካል የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲኖሩ ጨረታው ብቁ አይደለም በማለት ሊወስን ይችላል፡፡

(ሀ) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 24.2 መሠረት ጨረታውን በሲስተም እንዲያዘጋጅ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተወከለው ሰው በኩባንያው ወይም በጋራ ማህበሩ ወይም በጊዜያዊ ማህበሩ ስም ለመፈረም የተወከለበት ህጋዊ የጽሑፍ ሰነድ ሳይቀርብ ሲቀር፣

(ለ) ጨረታው በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 11.1 በተመለከተው ቋንቋ ያልቀረበ ከሆነ፣

(ሐ) የቴክኒክ እና የዋጋ መጫረቻ ሠነድ በአንድ ላይ የሚቀርብ ከሆነ ተጫራቹ በሲስተሙ በተቀመጠው ቅጽ መሠረት የዋጋ ዝርዝር ማቅረብ ካልቻለ፣

(መ) ተጫራቹ የህጋዊ አግባብነት ማረጋገጫ ሠነዶችን ካልቀረበ፣

(ሠ) ተጫራቹ የፍላጐት ዝርዝር መግለጫ፣ የቴክኒክ ሀሳብና የአግባብነት መግለጫ ሠንጠረዥሞልቶ ካላቀረበ፣

(ረ) ተጫራቹ የተፈረመና ቀን ያለበት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ካላቀረበ፣

(ሰ) የቀረበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 22 መሠረት ካልሆነ፡፡

## 35. *ከሀጋዊነት፣ ሙያ፣ የቴክኒክ ብቃትና የፋይናንሺያል አንፃር የጨረታዎች አወሳሰን መስፈርቶች*

35.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተጠየቁትን ወሳኝ ሰነዶች ተሟልተው መቅረባቸውን ካረጋገጠ በኋላ የጨረታው ህጋዊነት፣ ፕሮፌሽናል፣ ቴክኒካልና ፋይናንሻል ተቀባይነት ይመረምራል፣ በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተቀመጡት መስፈርቶች አንፃር ብቁና ብቁ ያልሆኑትን ይለያል፡፡

35.2 ሕጋዊ ተቀባይነት

የግዥ ፈፃሚው አካል በሚከተሉት ምክንያቶች የጨረታን ብቁ አለመሆን ሊወስን ይችላል፡፡

(ሀ) ተጫራቹ ከዜግነት አወሳሰን ጋር በተያያዘ በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.2 ላይ የተገለፀውን ካላሟላ፣

(ለ) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.3 መሠረት ከተጫራቹ ጋር የጥቅም ግጭት መኖሩ ሲታወቅ፣

(ሐ) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.6 (ለ) (i) መሠረት ተጫራቹ ከሥራው ጋር አግባብነት ያለው የታደሰ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ ሳይችል ሲቀር፣

(መ) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.7 መሠረት ተጫራቹ በመንግሥት ግዥና ንብረት የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት ላይ በአቅራቢነት ያልተመዘገበ ሲሆን፣

(ሠ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥና በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.6 (ለ) (ii) መሠረት የሀገር ውስጥ ተጫራች ሆኖ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት/ ሰርቲፊኬት/ ማቅረብ ሳይችል ሲቀር፣

(ረ) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.6 (ለ) (iii) መሠረት የሀገር ውስጥ ተጫራች ሆኖ ታክስ የከፈለበትን ሰርቲፊኬት ከሚመለከተው አካል ማቅረብ ሳይችል ሲቀር፣

(ሰ) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.4 መሠረት ከዚህ በፊት ከነበሩ የውል ግዴታዎች ጋር በተያያዘ ምክንያት በመንግሥት ግዥ እንዳይሳተፍ በመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የታገደ ተጫራች ከሆነ፣

(ሸ) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.1 መሠረት ጨረታው የቀረበው ከጋራ ማህበር ከሆነና ተጫራቹ የጋራ ማህበሩን የመረጃ ቅፅ፣ ማህበሩ የተቋቋመበትን ስምምነት ወይም ደብዳቤ ማቅረብ ካልቻለ፣

## 35.3 ፕሮፌሽናል ተቀባይነት

የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚከተሉት ምክንያቶች የጨረታውን ብቁ አለመሆን ሊወስን ይችላል።

(ሀ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ንዑስ አንቀጽ 4.6 (ለ) (iv) ተጠይቆ ከሆነና ተጫራቹ ተዛማጅነት ያለው የፕሮፌሽናል ሥራ ማስረጃ ማቅረብ ካልቻለ፣

(ለ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ንዑስ አንቀፅ 14.1 መሠረት የተጫራቹን ፕሮፌሽናል አቅም ለማረጋገጥ የተጠየቀውን የአግባብነትና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረብ ካልቻለ፣

## 35.4 ቴክኒካዊ ተቀባይነት

የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚከተሉት ምክንያቶች የጨረታውን ብቁ አለመሆን ሊወስን ይችላል።

(ሀ) ተጫራቹ የጨረታ ማቅረቢያ ቅፅ በሚፈቅደው መሠረት ዕቃውን የሚያቀርበው ወይም አገልግሎቱን የሚሰጠው ከየት እንደሆነ ሳይገልጽ ሲቀር፣

(ለ) ተጫራቹ የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በሚጠይቀው መሠረት ከዚህ በፊት በአጥጋቢ ሁኔታ ያከናወናቸውን ዋና ዋና የውል አፈጻጸም መረጃ በቁጥርና በጊዜ ለይቶ በተጫራቾች አግባብነት ማረጋገጫ ቅፅ ሳያቀርብ ሲቀር፣

(ሐ) ተጫራቹ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ንዑስ አንቀጽ 16.3 መሠረት ከዚህ በፊት ከሰራላቸው አካላት የውል አፈጻጸም በአጥጋቢ ሁኔታ ማከናወኑን የሚያረጋግጥ በጊዜና በበጀት ለይቶ ሳያቀርብ ሲቀር፣

(መ) በክፍል 6 በተመለከተው መሠረት ተጫራቹ የተሟላ የፍላጐት መግለጫ፣ የቴክኒክ ሀሳብና የአግባብነት መግለጫን በተዘጋጀው ቅፅ መሠረት ሳያቀርብ ሲቀር፣ እንደዚሁም የሚከተሉትን ወሳኝ ማስረጃዎች ካላቀረበ፣

- (i) በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 17 መሰረት የቴክኒክ መግለጫ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ፣
- (ii) በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 25 በድርጅቱ የተሰጠ ዋስተና (Warranty)፣
- (iii) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 5.6 መሰረት እንዳስፈላጊነቱ በአምራቹ የተሰጠ የአቅራቢነት የስልጣን ደብዳቤ፣

## 35.5 የፋይናንስ ተቀባይነት

የግዥ ፈፃሚው አካል በሚከተሉት ምክንያቶች ጨረታውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል።

(ሀ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ንዑስ አንቀጽ 15.2 (ሀ) እና በክፍል 3 የግምገማ ዘዴዎችና መስፈርቶች በተመለከተው መሠረት ተጫራቹ በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ የፋይናንስ ማረጋገጫ ሳያቀርብ ሲቀር፣

(ለ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ንዑስ አንቀጽ 15.2 (ለ) መሠረት ተጫራቹ የፋይናንስ አቅሙን የሚያሳዩ እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች ማረጋገጫ ሰነዶች ሳያቀርብ ሲቀር፣

(ሐ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ተጫራቹ የሚያቀርበው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሃሳብ መጠን በክፍል 3 የግምገማ ዘዴዎችና መስፈርቶች በተገለፀው መሠረት ከዓመታዊ አማካይ የፋይናንስ ገቢው (turnover) መብለጥ የለበትም።

(መ) በተጫራቹ የሚቀርበው ዓመታዊ አማካይ የሽያጭ መጠን (turnover) በጨረታ ሠነድ ላይ ከተጠየቀው ካነሰ፣

(ሠ) ተጫራቹ ያቀረበው የጨረታ ዋጋ በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 12 በተገለጸው ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ መሠረት ካልሆነ፣

(ረ) ተጫራቹ ለመጫረት ያቀረበው የመጫረቻ ገንዘብ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥና በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 13 ካልሆነ፣

## 36. *ጨረታዎችን ስለመገምገም*

36.1 የግዥ ፈፃሚው አካል ለዝርዝር ግምገማ ብቁ የሆኑ የመጫረቻ ሰነዶችን ብቻ ይገመግማል።

36.2 በተጫራቾች ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር ተጫራቾች ዋጋ መሙላት ያለባቸው በኢትዮጵያ ብር ብቻ ይሆናል።

36.3 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አካል ጨረታውን የሚገመግመው በዚህ አንቀጽና በክፍል 3 የግምገማና የብቃት መስፈርቶች መሠረት ነው። ሌላ ማንኛውንም የግምገማ ዘዴና መስፈርት መጠቀም አይፈቀድም።

36.4 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጨረታ ሲገመግም የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ ያስገባል።

(ሀ) የጨረታ ዋጋ፣

(ለ) በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 34 መሠረት የሒሳብ ስሌት ስህተቶች ማረሚያ (ማስተካከያ) ፣

(ሐ) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 12.4 መሠረት በቀረበው የዋጋ ቅናሽ ሀሳብ መሠረት የሚደረግን የዋጋ ማስተካከያ፣

(መ) በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 33 መሠረት አለመጣጣሞችና ግድፈቶች ማስተካከያ፣

(ሠ) በግምገማና ብቃት መስፈርቶች ክፍል 3 ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት ሁሉንም የግምገማ ነጥቦች መተግበር፣

(ረ) በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 35 መሠረት የልዩ አስተያየት ገደብን ተግባራዊ ማድረግ፣

36.5 በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 12 ከተጠቀሰው የጨረታ ዋጋ በተጨማሪ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሌሎች ነጥቦችን ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡ እነዚህ ነጥቦች የአገልግሎቱ ባህርይ፣ አፈፃፀም፣ ቃላቶችና ሁኔታዎች ጋር ሊያያዙ ይችላሉ፡፡ ለግምገማ ጥቅም ላይ የሚውሉት ነጥቦችና የአተገባበር ዘዴዎች በግምገማና ብቃት መስፈርት ክፍል 3 ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡

36.6 ይህ የጨረታ ሰነድ ተጫራቾች ዋጋቸውን በሎት እንዲያቀርቡ፤ እንዲሁም ለአንድ ተጫራች የሎት (lot) ውል መስጠት የሚፈቅድ ሲሆን፤ ዝርዝር አፈፃፀሙም በጨረታ ማቅረቢያ ቅፅ ላይ የተመለከተውን ቅናሽ አካቶ አሸናፊውን ድርጅት ለመወሰን ስራ ላይ የሚውለው የመወዳደሪያ መስፈርት እና የግምገማ ዘዴ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ እና በጨረታ ሰነዱ ክፍል 3 ላይ በተገለፀው መሰረት ይሆናል፡፡

**37.** ***ጨረታዎችን ስለማወዳደር***

37.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጨረታ ሰነዱ ክፍል 3 ላይ የተገለፀውን የማወዳደሪያና የግምገማ መስፈርት በመጠቀም መሰረታዊ ወይም ዝቅተኛ የማወዳደሪያ መስፈርቶችን ካሟሉት መካከል በአሸናፊነት መመረጥ የሚገባውን ተጫራች ይወስናል፡፡

**38.** ***ድህረ-ብቃት ግምገማ***

38.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጨረታ ሰነዶቹ መመዘኛዎች መሠረት አሸናፊ የሆነውን ተጫራች ወቅታዊ ብቃት ለማረጋገጥ የድህረ-ብቃት ግምገማ ያከናውናል፡፡

38.2 የድህረ ብቃት ግምገማው የሚያተኩረው አሸናፊው ተጫራች በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 37 መሠረት ካቀረባቸው የማስረጃ ሰነዶች ጋር በተያያዘ ይሆናል፡፡

38.3 በድህረ-ብቃት ግምገማ ወቅት አሸናፊው ተጫራች በ 15 ቀናት ውስጥ ተጨባጭ ሰነዶች ማቅረብ ካልቻለ ወይም ያቀረባቸው ሰነዶች የተሳሳቱ ሆነው ከተገኙ ጨረታው ውድቅ ይደረጋል፡፡ በዚህ ጊዜ የግዥ ፈፃሚው አካል በሁለተኛ ደረጃ ዝቅተኛ ዋጋ ወደ አቀረበው ተጫራች በማለፍ ብቃቱን ለማረጋገጥ በተመሳሳይ ሁኔታበተጫራቹ ላይ አስፈላጊውን የድህረ-ብቃት ግምገማ ያከናውናል፡፡

**39.** ***ጨረታን ስለመቀበል ወይም ውድቅ ስለማድረግ***

39.1 በአዋጁ የተገለጸው ቅድመ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማንኛውንም ጨረታ የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት አለው፡፡ እንዲሁም ውል ከመፈረሙ በፊት ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሂ የመሰረዝና ውድቅ የማድረግ መብት አለው፡፡

**40.** *ድጋሚ ጨረታ ስለማውጣት*

40.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚከተሉት ምክንያቶች ጨረታውን ሰርዞ እንደገና እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡

(ሀ) የጨረታው ውጤት አጥጋቢ ሳይሆን ሲቀር ማለትም በጥራትና በዋጋ አዋጭ ሳይሆን ሲቀር፣
(ለ) የቀረበው የጨረታ ዋጋ ከወቅታዊ የገበያ ዋጋ አንጻር ከ 10% (አስር በመቶ) የበለጠ ሲሆን፣
(ሐ) በጨረታው ሰነድ ውስጥ የተገለፁት ህጐችና ሥነ-ሥርዓቶች ከግዥ አዋጁና መመሪያው ጋር የማይጣጣሙ ሲሆን፣ በዚሁ ምክንያት ተጫራቾችን የማይስብ ሆኖ ሲገኝ ወይም የጨረታ ሰነዱ ተሸሽሎ በድጋሚ ጨረታው ቢወጣ የተጫራቾችን ቁጥር ከፍ ሊያደርግ ይችላል ተብሎ ሲታመንበት፣
(መ) በሌሎች አስገዳጅ ሁኔታዎች ይህንን የማዕቀፍ ስምምነት ማከናወን ሳይቻል ሲቀር፡፡

**ረ. ውል ስለመፈፀም**

**41.** *አሸናፊ ተጫራችን መምረጫ መስፈርቶች*

41.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከቱትን መሰረታዊ መስፈርቶች በአጥጋቢ ሁኔታ ካሟሉት መካከል የተሻለ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች የጨረታ አሸናፊ አድርጎ በመምረጥ ይህንኑ ለአሸናፊው ተጫራች ያሳውቃል፡፡

41.2 በጨረታ ሰነዱ ላይ የተጠየቀው የሎት (lot) ውል ከሆነ በዚሁ መሠረት ለእያንዳንዱ የሎት (lot) የአሸናፊነት ማስታወቀያ ይሰጣል፡፡ ይህም ሆኖ ግን የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የቀረቡትን ቅናሾችና አጠቃላይ ሁኔታዎችን አይቶ የሚሻለውን ሊመርጥ ይችላል፡፡

41.3 አንድ ተጫራች ያሸነፈው ከአንድ በላይ የሎት (lot) ከሆነ ሁሉም በአንድ የውል ስምምነት ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡

**42.** *ከውል በፊት የግዥ መጠን ስለመለወጥ*

42.1 የጨረታ አሸናፊነት ማሳወቂያ በሚሰጥበት ጊዜ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የግዥውን መጠን በፍላጐት መግለጫ ክፍል 6 ውስጥ መጀመሪያ ከተጠቀሰው የመጨመር ወይም የመቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዡ ውስጥ የተመለከተውን የመቶኛ ምጣኔ ተጠብቆ በነጠላ ዋጋዎች ላይ ምንም ለውጥ ሳይደረግ ወይም ሌሎች የጨረታ ዋስትና ሁኔታዎች ላይ ለውጥ ሳይደረግ ነው፡፡

**43.** *የጨረታ ውጤትና አሸናፊ ተጫራችን ስለማሳወቅ*

43.1 ግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማለቁ በፊት የጨረታው ግምገማ ውጤት ለሁሉም ተጫራቾች የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ሥርዐትን በመጠቀም ያሳውቃቸዋል፡፡

43.2 የጨረታ ውጤት ማሳወቂያው ያልተመረጡ ተጫራቾች ያልተመረጡበትን ምክንያት፣ እንዲሁም የተመረጠውን ተጫራች ማንነት ማካተት ይኖርበታል፡፡

43.3 ለአሸናፊው ተጫራች የሚላከው የአሸናፊነት ማሳወቂያ በተጫራቹና በግዥ ፈፃሚው አካል የተፈፀመ ውል መኖሩን አያመለክትም፡፡ በግዥ ፈፃሚው አካልና በአሸናፊው ተጫራች መካከል ውል ተመስርቷል የሚባለው ለግዥው አፈፃፀም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ሁኔታዎች በውል ውስጥ ተካተው ውሉ ሲፈረም ብቻ ነው፡፡

43.4 ለአሸናፊው ተጫራች የሚላከው ማሳወቂያ የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት ይኖርበታል፡፡

(ሀ) የግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታውን መቀበሉን፣
(ለ) ጠቅላላ የውል ዋጋውን፣
(ሐ) የዕቃዎችን ዝርዝርና የነጠላ ዋጋውን፣
(መ) ተጫራቹ ሊያቀርበው የሚገባው የውል ማስከበሪያ ዋስትና መጠንና የመጨረሻ ማስረከቢያ ቀን፣

**44.** *ውል አፈራረም*

44.1 የጨረታ አሸናፊነት ማሳወቂያ ከተላከ በኋላ የግዥ ፈፃሚው አካል ወዲያውኑ ለአሸናፊው ተጫራች የማዕቀፍ ስምምነት ረቂቅ የውል ሰነድ ይልክለታል፡፡

44.2 አሸናፊው ተጫራች ስምምነቱን በተቀበለ በአሥራ አምስት (15) ቀናት ጊዜ ውስጥ ፈርሞና ቀን ጽፎበት ለግዥ ፈፃሚው አካል ይመልሳል፡፡

44.3 የግዥ ፈፃሚው አካል የጨረታ ውጤቱን ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ ካሉት ሰባት ቀናት በፊት ወይም በጨረታው ሂደት ላይ የቀረበ ቅሬታ ካለ ለቀረበው ቅሬታ ምላሽ ሳይሰጥ ውል መፈረም የለበትም፡፡

44.4 በሚከተሉት ሁኔታዎች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከአንድ በላይ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር የማዕቀፍ ስምምነት ሊገባ ይችላል፡፡

(ሀ) በማዕቀፍ ስምምነቱ መሠረት የሚቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት ከተጫራቾች አቅም በላይ ሆናል ተብሎ ስለሚገመት፣

(ለ) በገበያ ላይ ያሉት አቅራቢዎች ቁጥርና አቅም ከሚፈለገው አቅርቦት ጋር ያለውን ተመጣጣኝነት ግምት ውስጥ በማስገባት ከአንድ በላይ ለሆኑ አቅራቢዎች በመስጠት ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ፣

(ሐ) የገበያ ዋጋዎች በከፍተኛ ሁኔታ ከፍና ዝቅ የሚሉበት ሁኔታ በመኖሩ ምክንያት ዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥውን በአስቸኳይ በአሸናፊው ተጫራች ዋጋ መግዛት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ።

44.5 ከላይ በንዑስ አንቀጽ 44.4 በተመለከተው መሠረት የግዥ ፈፃሚው አካል ከአሸናፊው ተጫራች በተጨማሪነት ለማዕቀፍ ስምምነት የሚጋበዙና የሚሳተፉ ተጫራቾችን ቁጥር ይወስናል።

(ሀ) ስምምነቱ የሚፈረመው አሸናፊው ተጫራች ባቀረበው ዋጋ ዕቃዎቹንና አገልግሎቶቹን ለማቅረብ ፈቃደኛ ከሆነ ተጫራች ጋር ነው።

(ለ) ስምምነቱን በተመለከተ ለአሸናፊው ተጫራች ቅድሚያ እንዲሰጥ ይደረጋል።

(ሐ) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 44.4 በተመለከተው መሠረት ከአንድ በላይ ተጫራቾች በማዕቀፍ ስምምነቱ እንዲሳተፉ በሚደረግበት ወቅት የማዕቀፍ ስምምነቱ ቢያንስ አምስት አቅራቢዎችን ያካተተ መሆን ያለበት ሲሆን ለጨረታው ዋና አሸናፊ የሚሰጠው ድርሻ ከጠቅላላው የውሉ መጠን 50% (ሃምሳ በመቶ) ማነስ የለበትም። ቀሪው 50%(ሃምሳ በመቶ) በአሸናፊው ተጫራች ዋጋ ለማቅረብ ከተስማሙትና እንደቅደምተከተላቸው ለተመረጡ አቅራቢዎች የሚከፋፈል ሲሆን ዝቅተኛው ድርሻ ከውሉ ጠቅላላ መጠን ከ 5% (አምስት በመቶ)ማነስ የለበትም።

መ/ በንኡስ አንቀጽ 44..5 (ሐ) የተገለጸው ቢኖርም በአሸናፊው ተጫራች ዋጋ ለማቅረብ የተስማሙ ተጫራቾች ቁጥር ከአምስት በታች ከሆነ ለአንደኛው አሸናፊ የሚሰጠው ድርሻ ከውሉ ጠቅላላ መጠን ቢያንስ 60% (ስልሳ በመቶ) ሲሆን ቀሪው ድርሻ ለተቀሩት አቅራቢዎች እንደ የደረጃቸው ይከፋፈላል። ሆኖም ዝቅተኛው ድርሻ ከውሉ ጠቅላላ መጠን ከ 5% (አምስት በመቶ) ማነስ የለበትም።

44.6 በንኡስ አንቀጽ 44.5 (ሀ) እና (መ) የተገነጸው ቢኖርም በአሸናፊው ተጫራች ዋጋ ለማቅረብ የተስማሙ ተጫራቾች የማይገኙ ከሆነ፣ የአሸናፊው ተጫራች ስምምነትን በመጠበቅ አሸናፊው ተጫራች ጠቅላላ የግዥፍላጎቱን በሙሉ ማቅረብ ይችላል።

44.7 በዚህ አንቀጽ መሠረት በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተወዳዳሪ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ተወዳድሮ ባሸነፈበት ዋጋ እንዲያቀርብ መደረግ ይኖርበታል።

## 45. *የውል ማስከበሪያ ዋስትና*

45.1 አሸናፊው ተጫራች ስምምነቱን በፈረመ በአሥራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች መሠረት በውል ቅፆች ክፍል 9 ውስጥ የተመለከተውን የውል ማስከበሪያ ዋስትና ያቀርባል።

45.2 የማዕቀፍ ስምምነት የፈረመ አቅራቢ ድርጅት የማዕቀፍ ስምምነት ለሚገባው መ/ቤት የጠቅላላ ዋጋውን 3% የውል ማስከበሪያ ማስያዝ ያለባቸው ሲሆን ከግዥ ፈጻሚ መ/ቤቶች ጋር ዝርዝር ውል በሚገቡበት ጊዜ ደግሞ የውሉን መጠን 10% የውል ማስከበረያ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

45.3 አሸናፊው ተጫራች ከላይ የተጠቀሰውን የአፈፃፀም ዋስትና ማቅረብ ያለመቻል ወይም ውሉን መፈረም ያለመቻል ውል መስጠቱን ለመሰረዝና የጨረታ ዋስትናውን ለመውረስ በቂ ምክንያቶች ይሆናሉ፡፡

45.4 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በጨረታ ዋስትና፣ በውል ማስከበሪያ ዋስትናና በቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ምትክ ኢንተርፕራይዞቹን ለማደራጀትና ለመምራት ሥልጣን ከተሰጠው መ/ቤት የዋስትና በአደራጁ መ/ቤት የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የገንዘብ መጠን ተጠቅሶ የተጻፈ ደብዳቤ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

45.5 አሸናፊው ተጫራች ስምምነቱን ሳይፈርም ሲቀር ወይም የውል ማስከበሪያ ዋስትና ሳያቀርብ ሲቀር፣ የግዥ ፈፃሚው አካል በውድድሩ ሁለተኛ የወጣውን ተጫራች እንዲፈርም ያደርጋል ወይም ከሁለቱም አማራጮች የሚገኘውን ጥቅም በማነፃፀር ጨረታው በአዲስ መልክ እንደገና እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

ክፍል **2**

የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ

ማውጫ


ሀ. መግቢያ..........................................................................................1

**ለ. የጨረታ ሰነዶች.........................................................................2**

**ሐ. የጨረታዎች አዘገጃጀት...............................................................2**

**መ. የጨረታዎች አቀራረብና አከፋፈት.............................................4**

**ሠ. ጨረታዎችን መገምገምና ማወዳደር.............................................5**

**ረ.. ውል ስለመፈፀም.....................................................................5**

# ክፍል 2

## የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ

| የተጫራቾች መመሪያ (ተ.መ) መለያ | ከተጫራቾች መመሪያ ጋር የተያያዘ መረጃ |
|---|---|
| | **ሀ. መግቢያ** |
| ተ.መ. 1.1 | ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ፦ [የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ስም ይግባ]<br><br>አድራሻ፦ [አድራሻ ይግባ] |
| ተ.መ. 1.1 | የጨረታ ሰነድ የወጣበት የግዥ ዘዴ፦ [የግዥ ዘዴ ይግባ] |
| ተ.መ. 1.2 | የፕሮጀክቱ ስም፦ [የፕሮጀክቱ ስም ይግባ]<br><br>የዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች አይነት አጠቃላይ መግለጫ፦ [ የዕቃዎች አይነት አጠቃላይ መግለጫ ይግባ] |
| ተ.መ. 1.3 እና | የግዥ መለያ ቁጥር፦ [የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ] |
| ተ.መ. 1.3 | የጨረታው ሰነድ የብዙ ምድብ (lot) መለያ ቁጥር፦ [የ lot ቁጥርና መለያ ይግባ] |
| ተ.መ. 1.8 | የማዕቀፍ ስምምነቱ ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ፦ [ጊዜ ይግባ] |
| ተ.መ. 4.1 (ሀ) | ግለሰቦች፣ የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበራት በጋራና በተናጠል ተጠያቂ መሆን አለመሆናቸው ይገለፅ።<br><br>[ግለሰቦች ወይም የጋራ ማህበራት በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ካልሆኑ " በምትኩ፣የሚከተሉት ልዩ ተጠያቂነቶችና ሀላፊነቶች ለያንዳንዱ ግለሰብ ወይም የጋራ ማህበራት ተግባራዊ እንደሚሆን ይግባ " (በዝርዝር ይብራራ)] |
| ተ.መ. 4.6 (ለ) (ii) | ተጫራቾች በሚመለከተው አካል በሚወሰነው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን [መጠኑ በኢትዮጵያ ብር ይግባ] ከዚያ በላይ ለሆነ ጨረታ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ሠርቲፊኬት ማቅረብ አለባቸው |
| ተ.መ. 4.6 (ለ) (IV) | አግባብነት ያለው የሙያ ብቃት [የሙያ ብቃት ይገለፅ] ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ማቅረብ እንዳለበትና እንደሌለበት ይገለጽ |
| ተ.መ. 4.8 | ተጫራቹ ሕጋዊነቱን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የታደሱ ሰነዶች ማቅረብ አለበት።<br><br>ሀ.<br><br>ለ.<br><br>ሐ. |
| ተመ 4.9 እና 4.10 | የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ያላቸው ሠዎችና ድርሻቸው ይገለጽ፤ |

| | | |
|---|---|---|
| | ሀ.<br><br>ለ.<br><br>ሐ. | |
| ተ.መ. 5.6 | ተጫራቹ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በኢትዮጵያ ለማቅረብ እንደሚችል የሚያረጋግጥ በአምራቹ የተሰጠ የአቅራቢነት የውክልና ስልጣን ደብዳቤ ማቅረብ እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ይገለፅ። | |
| ተ.መ. 6.3 | ተጫራቹ የጨረታ ሠነዱን ለማግኘት መክፈል የሚገባው ክፍያ ካለ መጠን እና የአከፋፈል ሁኔታ ይገለጽ። | |
| **ለ. የጨረታ ሰነዶች** | | |
| ተ.መ. 7.1 እና 9.4 | ለጥያቄና ለማብራሪያ ዓላማ የመንግስት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓትን መጠቀም አለባቸው። | |
| | ግዥ ፈፃሚ አካል | *[ግዥ ፈፃሚ አካል ስምይግባ]* |
| | ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው | *[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስም ይግባ]* |
| | ቢሮ ቁጥር | *[ቢሮ ቁጥር ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ]* |
| | ፖ.ሣ.ቁ. | *[ፖ.ሣ.ቁ.ይግባ]* |
| | የመንገድ ስም | *[የመንገድ ስም ይግባ]* |
| | ከተማ | *[የከተማ ስም ይግባ]* |
| | ፖ. ሳ. ኮድ ቁጥር | *[ፖ.ሳ. ኮድ ቁጥር ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ከሲገኝ]]* |
| | አገር | |
| | ስልክ ቁጥር | *[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ]* |
| | የፋክስ ቁጥር | *[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የፋክስ ቁጥር ይግባ]* |
| | ኢ.ሜይል አድራሻ | *[ኢ.ሜይል አድራሻ ይግባ]* |
| ተ.መ. 7.1 እና 9.4 | የጥያቄዎችና ማብራሪያዎች ማቅረቢያ ቀነ-ገደብ<br><br>ቀን፦ *[ቀን፣ወር፣ እና ዓ.ም ይግባ]*<br><br>ሰዓት፦ *[ከጠዋቱ/ምሽቱ ተጠቅሶ ሰዓት ይግባ*] | |
| ተ.መ. 9.2 | ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የቅድመ ጨረታ ስብሰባ የሚካሄድ ስለመሆን አለመሆኑ ይገለጽ።<br><br>ቅድመ ጨረታ ስብሰባ የሚደረግ ከሆነ መ/ቤቱ ስብሰባው የሚካሄድበትን ቀን፦ *[ቀን፣ወር፣ እና ዓ.ም ይግባ]*<br><br>ሰዓት፦ *[ከጠዋቱ/ምሽቱ ተጠቅሶ ሰዓት ይግባ*] | |
| **ሐ. የጨረታዎች አዘገጃጀት** | | |
| ተ.መ. 11.1 | የጨረታው ቋንቋ፦ *[የጨረታው ቋንቋ ይግባ]* | |
| ተ.መ. 12.2 | በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የዋጋ ቅናሽ ተቀባይነት ያለው ስለመሆን አለመሆኑ ይገለጽ | |
| ተ.መ. 12.6 | አለም አቀፍ የንግድ ውል ቃል እትም፦ *[ጥቅም ላይ የሚውለው የአለም አቀፍ የንግድ ውል (ኢንኮተርም) ቀን ይግባ*] | |

| | |
|---|---|
| ተ.መ. 12.9 | የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው እስከ [ጊዜ ይግባ]___ ነው። |
| ተ.መ. 12.11 | ለእያንዳንዱ ሎት(lot) የቀረበው ዋጋ ቢያንስ [በፅሁፍ መቶኛ ፣በተለምዶ 100 ይግባ]___ % [በምልክት መቶኛ % ይግባ] ከተጠቀሰው እያንዳንዱ የዕቃ ዓይነት መጣጣም አለበት።<br><br>ለእያንዳንዱ ሎት(lot) የቀረበው ከእያንዳንዱ የዕቃ መጠን ጋር ቢያንስ [በፅሁፍ መቶኛ ፣በተለምዶ 100 ይግባ] በ ___% [በምልክት መቶኛ % ይግባ] መጣጣም አለበት። |
| ተ.መ 12.12 | የሕይወት ዘመን ወጪ ትንተና (Life-Cost Analysis) ታሳቢ ያደረገ ግዥ መሆን አለመሆኑ ይገለጽ። |
| ተ.መ. 13.1 | ተጫራቹ ከሀገር ውስጥ (ከኢትዮጵያ) ለሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚያቀርበው ዋጋ በ _ መሆን አለበት [የመገበያያ ገንዘብ አይነት ይግባ] |
| ተ.መ. 14.1 | ተጫራቹ የአሁኑንና [የአመታት ብዛት ይግባ] የበፊቱን የሙያ ብቃትና አቅም ማረጋገጫውን በተጫራቾች አግባብነት ማረጋገጫ ቅጽ በመሙላት ማስረጃውን ማቅረብ አለበት። |
| ተ.መ. 15.2 (ለ) | ተጫራቹ የፋይናንስ አቅሙን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት።<br><br>ሀ.<br><br>ለ.<br><br>ሐ. |
| ተ.መ. 16.3 | ተጫራቹ ከዚህ በፊት ላከናወናቸው ተመሳሳይ አገልግሎቶች ከአሠሪው አካል የመልካም ሥራ ማረጋገጫ ማስረጃ የምስክር ወረቀት [አስፈላጊው የምስክር ወረቀት ብዛት ይግባ] ማቅረብ አለበት። የሚቀርበው ማስረጃ ባለፉት ____ዓመታት [አስፈላጊው የአመታት ብዛት ይግባ] የተሠሩና የበጀት መጠናቸው [አስፈላጊው የበጀት መጠን ይግባ] ቢያንስ __ ___ የሆኑትን ነው። |
| ተ.መ. 16.7 | የግዥ ፈፃሚው አካል የተጫራቹን የቴክኒክ ብቃትና ክህሎት ለማወቅ በአካል በመገኘት ማረጋገጥ ማስፈለግ/አለማስፈለጉ ይገለፅ። |
| ተ.መ. 17.1 | ተጫራቹ የሚከተሉትን የቴክኒክ መግለጫ ማስረጃዎች ከጨረታው ጋር ማቅረብ አለበት።<br><br>ሀ. ለ. ሐ. |
| ተ.መ. 18.1 | ለማሳያነት የሚከተሉት ናሙናዎች መቅረብ አለባቸው።<br><br>ሀ.<br><br>ለ.<br><br>ሐ. |
| ተ.መ. 20.1 | አማራጭ ጨረታ ማቅረብ መፈቀድ/አለመፈቀዱ ይገለፅ። |
| ተ.መ. 20.4 | አማራጭ ጨረታዎች ከላይ በተጠቀሰው ንዑስ አንቀጽ 20.1 የተፈቀዱ ከሆነ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል። [አማራጭ ጨረታዎች ለመፍቀድ ማሟላት ያለባቸው |

<table>
<tr><td></td><td colspan="2">መስፈርቶች ካለ ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ተ.መ. 21.1</td><td colspan="2">ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ [የቀን ብዛት ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ተ.መ. 22.1</td><td colspan="2">የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ ማስፈለግ/አለማስፈለጉ ይገለፅ። ጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ የሚያስፈልግ ከሆነ ይገለፅ። (የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና መጠኑ የሚወሰነው ከተገመተው የጨረታ ዋጋ ከ 0.5% -2% በማስላት ይሆናል)</td></tr>
<tr><td colspan="3">መ. የጨረታዎች አቀራረብና አከፋፈት</td></tr>
<tr><td rowspan="8">ተ.መ. 24.1</td><td colspan="2">ተጫቾች የመጫረቻ ሠነዳቸውን ማቅረብ የሚችሉት የመንግስት የኤልክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ብቻ ይሆናል።<br><br>ቀን ....<br><br>ሰዓት.... ይግባ<br><br>ጨረታን ለማቅረብ ዓላማዎች ብቻ የሚያገለግል ግዥ ፈፃሚ አካል አድራሻ</td></tr>
<tr><td>ግዥ ፈፃሚ አካል</td><td>[ግዥ ፈፃሚ አካል ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው</td><td>[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ቢሮ ቁጥር</td><td>[ቢሮ ቁጥር ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ]</td></tr>
<tr><td></td><td>[የመንገድ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td></td><td>[የከተማ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>አገር</td><td>ኢትዮጵያ</td></tr>
<tr><td colspan="2">የጨረታ ማቅረቢያ ቀነ-ገደብ<br><br>ቀን፦ [ቀን፣ወር፣ እና አመት ይግባ ምሳሌ፦15 ግንቦት 2003 ዓ.ም ፣ወሩ በፊደል ይፃፍ]<br><br>ሰዓት፦ [ሰዓት፣ከጠዋቱ ወይም ከሰአት በኋላ ተብሎ ይግባ]</td></tr>
<tr><td rowspan="10">ተ.መ. 27.1</td><td colspan="2">ጨረታው የሚከፈትበት ሁኔታቦታና ቀንጊዜ እና ሰዓት ይግባ</td></tr>
<tr><td>ግዥ ፈፃሚ አካል</td><td>[ግዥ ፈፃሚ አካል ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው</td><td>[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ቢሮ ቁጥር</td><td>[ቢሮ ቁጥር ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ]</td></tr>
<tr><td>የመንገድ ስም</td><td>[የመንገድ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ከተማ</td><td>[የከተማ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ፖ.ሣ. ቁጥር</td><td>[ፖ.ሳ. ቁጥር ይግባ]</td></tr>
<tr><td>አገር</td><td>ኢትዮጵያ</td></tr>
<tr><td>ቀን</td><td>[ቀን፣ወር፣ እና አመት ይግባ ምሳሌ፦15 ግንቦት 2003 ዓ.ም ፣ወሩ በፊደል ይፃፍ]</td></tr>
<tr><td>ሰዓት</td><td>[ሰዓት፣ከጠዋቱ ወይም ከሰአት በኋላ ተብሎ ይግባ]</td></tr>
</table>

| | |
|---|---|
| **ሠ. ጨረታዎችን መገምገምና ማወዳደር** | |
| ተ.መ. 32.3 | ተጫራቹ የተደረጉትን የሂሳብ ስሌት ስህተት ማስተካከያዎች ስለመቀበሉ በ____ የጊዜ ገደብ *[ግዜ ይግባ]* ማሳወቅ አለበት |
| ተ.መ. 35.4 (ሐ) | ተጫራቹ ባለፉት ____ ዓመታት [አስፈላጊው የአመታት ብዛት ይግባ] በአጥጋቢ ሁኔታ ያከናወናቸውን ዋና ዋና የአቅርቦት ውል ስምምነቶች *[የውል ስምምነቶች ብዛትይግባ]* የሚያረጋግጥ በተጫራች አግባብነት ማረጋገጫ ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ አለበት። |
| ተ.መ. 35.5 (ሐ) | የተጫራቹ ባለፉት ..........አመታት ያስመዘገበው አማካኝ ዓመታዊ አማካኝ የሽያጭ መጠን (የሚጠየቀው አማካኝ የሽያጭ መጠን ይግባ) |
| ተ.መ. 36.2 | ተጫራቾች ዋጋ የሚያቀርቡበት የተለያየ የገንዘብ ዓይነት መፈቀድ አለመፈቀዱ ይገለጽ።<br><br>ለጨረታ ግምገማና ውድድር ዓላማ ሲባል የቀረቡት የተለያዩ የገንዘብ ዓይነቶች ወደ____ ገንዘብ ይቀየራሉ *[የመገበያያ ገንዘብ አይነት ይግባ]* |
| ተ.መ. 36.6 | ብዛት ያላቸው ጨረታዎች ለአንድ ተጫራች መስጠት መፈቀድ/አለመፈቀዱ ይገለፅ። በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለፁትን ፍላጎቶች አሟልቶ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች ለመወሰን የሚያስችሉ ዝርዝር ነጥቦች በክፍል 3 የግምገማና የብቃት መስፈርቶች በሚለው ላይ ተገልፀዋል። |
| ረ. ውል ስለመፈፀም | |
| ተ.መ. 44.1 | የሚገዙ ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች ብዛት (መጠን) ሊጨምር የሚችልበት የመቶኛ መጠን ___. *[የተፈቀደ ትልቁ መቶኛ ይግባ]*<br><br>የሚገዙ ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች ብዛት (መጠን) ሊቀንስ የሚችልበት የመቶኛ መጠን ___. *[የተፈቀደ ትንሹ መቶኛ ይግባ]* |

ክፍል **3**

## የጨረታዎች የግምገማ ዘዴና መስፈርቶች

### ማውጫ

**1.** ፕሮፌሽናል፣ ቴክኒካልና ፋይናንሻል የብቃት መስፈርቶች........................................1

**2.** አሸናፊ ጨረታን ስለመወሰን.....................................................................2

**3.** ልዩ አስተያየት.......................................................................................4

**4.** የበርካታ ግዥዎች ግምገማ......................................................................5

**5.** አማራጭ ጨረታዎች.................................................................................5

*[ማስታወሻ ግዥ ፈፃሚው አካል፤ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መስፈርቶች ለብቻቸው ተጫራቾችን ለመምረጥ እንደመጨረሻ ተደርገው መቆጠር የለባቸውም]*

## የጨረታዎች ግምገማ ዘዴና መስፈርቶች

ይህ ክፍል የተጫራቾች *መመሪያ* ከሚለው ክፍል 1 እና የጨረታ ዝርዝር *መረጃ* ሠንጠረዥ ከሚለው ክፍል 2 ጋር ተጣምሮ ሲነበብ ግዥ ፈፃሚው አካል አንድ ተጫራች ተፈላጊዎቹ ብቃቶች ያሉት ስለመሆኑ ለመገምገምና ለመወሰን መጠቀም ያለበትን ሁሉንም ነጥቦች፣ ዘዴዎችና መስፈርቶችን ይይዛል። ሌሎች ማናቸውም ነጥቦች፣ ዘዴዎች ወይም መስፈርቶች ጥቅም ላይ አይውሉም።

### *1.* ፕሮፌሽናል፣ ቴክኒካልና ፋይናንሻል የብቃት መስፈርቶች

የሚከተሉት የብቃት መስፈርቶች በሁሉም ተጫራቾች ተፈፃሚ ይሆናሉ። ጨረታው የቀረበው በጊዜያዊ ማህበር ከሆነ እነዚህ የብቃት መስፈርቶች በጊዜያዊ ማህበሩ በአጠቃላይ ተፈፃሚ ይሆናል። *[ተስማሚ በሆነው ፊደል ምልክት ይደረግ]*

## 1.1 የተጫራች ፕሮፌሽናል ብቃትና አቅም (የተጫራቾች *መመሪያ* አንቀጽ 14)

(ሀ) ☐ ተጫራቹ በአሁኑ ወቅት ቢያንስ ቁልፍ ሠራተኞች ያሉት [አስፈላጊው ቁጥር ይግባ]

(ለ) ☐ ከላይ በ“ሀ” ለተጠቀሱት ቁልፍ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ____ (*የሙያቸውን ዓይነት፤ ደረጃ፤* ወዘተ ይጠቀስ).

(ሐ) ☐ ተጨማሪ *መስፈርት* ካለ ይጠቀስ

## 1.2 የተጫራቹ ቴክኒካል ብቃት፣ ክህሎትና የ*ሥራ* ልምድ (የተጫራቾች *መመሪያ* አንቀጽ 16)

(ሀ) ☐ ተጫራቹ ባለፉት __ *ዓመታት* *[አስፈላጊው የአመታት ብዛት ይግባ]* ቢያንስ ይህንን ጨረታ የሚመጥን በጀት ያላቸው ______ ኮንትራቶች *[የኮንትራቶች ብዛት ይግባ]* ማከናወኑን

(ለ) ☐ ተጨማሪ *መስፈርት* ካለ ይጠቀስ

## 1.3 የተጫራቹ የፋይናንስ አቅም (የተጫራቾች *መመሪያ* አንቀጽ 15)

(ሀ) ☐ ተጫራቹ ባለፉት *ዓመታት* *[የአመታት ብዛት ይግባ]* የነበረው አማካይ የተረጋገጠ ዓመታዊ ገቢ ቢያንስ ለዚህ ጨረታ ከቀረበው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ጊዜ *[አስፈላጊው ጊዜ ይግባ*] የሚበልጥ መሆን አለበት።

(ለ) ☐ ተጨማሪ *መስፈርት* ካለ ይጠቀስ

### *2.* አሸናፊ ጨረታን ስለመወሰን

በመንግሥት ግዥ አዋጅና *መመሪያ መሠረት* የግዥ ፈፃሚው አካል የሚከተሉትን ዘዴዎች በመጠቀም አሸናፊው ተጫራች የሚመርጠው፤ *[ተስማሚ በሆነው ፊደል ምልክት ይደረግ]*

(ሀ) ☐ በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተገለፁት ፍላጐቶች አንፃር በፕሮፌሽን፣ በቴክኒክና በፋይናንስ ብቃቱ ተገምግሞ መሠረታዊ መመዘኛዎችን ያሟላና ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ ከሆነ፡፡

(ለ) ☐ ከላይ በ"ሀ" ከተመለከተው በተጨማሪ በሌሎች መስፈርቶች ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የሚያስገኝ ሆኖ ሲገኝ፡፡

ሀ. ዝቅተኛ ዋጋ የቀረበበት ጨረታ

በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 23 መሠረት የጨረታው ሰነድ የሚጠይቃቸውን የሰነድ ማስረጃዎች መሟላታቸው መመርመር አለበት፡፡

አስገዳጅ የሰነድ ማስረጃዎች በተገቢው መንገድ መሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ የግዥ ፈፃሚው አካል በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ከተጠየቁት የፕሮፌሽን፣ የሕግ፣ የቴክኒክና የፋይናንሻል ተቀባይነት ፍላጐቶች ጋር በማገናዘብ ጨረታው የተሟላ ወይም ያልተሟላ መሆኑ ይወሰናል፡፡

በመቀጠልም የግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታው የተጠየቀውን የቴክኒክ ዝርዝር ፍላጐት ማሟላት አለማሟላቱን ከመረመረ በኋላ ከቴክኒክ አንፃር ጨረታው ብቁ ነው ወይም አይደለም የሚለውን ይወስናል፡፡

የግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታው ውስጥ ያለመጣጣሞችና ግድፈቶች እንዳይኖሩ በመገምገም ለተጠየቁት ፍላጐቶች መሠረታዊ መልስ የሚሰጥ ስለመሆኑ የማጣራት ሂደቱን ይቀጥላል፡፡

የግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታው ከቁጥር እና ስሌት ስህተቶች የፀዳ መሆኑን ያጣራል፣ የቁጥርና የስሌት ስህተቶች ካሉም ለተጫራቹ የታረመውን ስህተት በማሳወቅ እርማቶችን ስለመቀበሉ በሦስት ቀናት (3) ውስጥ እንዲያሳውቅ ይጠይቃል፡፡

በመጨረሻም የጨረታው ሕጋዊነት፣ ፕሮፌሽናል፣ ቴክኒካልና ፋይናንሻል ግምገማ ከተካሄደ በኋላ የግዥ ፈፃሚው አካል በጨረታ ሰነዱ የተጠየቁትን ፍላጐቶች በመሠረታዊነት የሚያሟላና በዋጋም ዝቅተኛ ሆኖ የተገኘን ጨረታ አሸናፊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ለ. ዝቅተኛውን መስፈርት በአጥጋቢ ሁኔታ ካሟሉት መካከል ዝቅተኛ ዋጋ የቀረበበትን ወይም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ ጨረታን ስለመወሰን

ጨረታው አስገዳጅ የሆኑትን የህግ፣ የፕሮፌሽን፣ የቴክኒክና የፋይናንስ መገምገሚያዎች ማሟላቱን ከተረጋገጠ በኋላ የሁለት ደረጃ የግምገማና የነጥብ አሰጣጥ ዘዴ ይከናወናል፡፡ በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 38.4 (ረ) መሠረት የግዥ ፈፃሚው አካል ጨረታዎችን በሚገመግምበት ጊዜ ከአነስተኛ የጨረታ ዋጋ በተጨማሪ የሚከተሉትን የግምገማ መስፈርቶች በጠቀሜታ ቅደም ተከተል መሠረት ነጥብ በመስጠት ጨረታውን ይመዝናል፡፡

(ሀ) ተጨማሪ የመገምገሚያ መስፈርቶችና ለእያንዳንዱ የተቀመጠው የምዘና ነጥብ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

| ቅደም ተከተል | የመስፈርቱ ስም | ለመስፈርቱ የተሰጠው ነጥብ መቶኛ |
|---|---|---|
| 1 | መስፈርት I | |
| 2 | መስፈርት II | |
| 3 | መስፈርት III | |
| 4 | መስፈርት IV | |
| I | አጠቃላይ ተጨማሪ መስፈርት (1+2+3+4) | |
| II | የጨረታ ዋጋ | |
| III | ጠቅላላ ድምር (I+II) | 100 |

(ለ) የግዥ ፈፃሚው አካል ማንኛውም ተጨማሪ መስፈርት የሚገመግመው በሚከተለው የነጥብ ምዘና መሠረት ነው፡፡

| ምዘና | | መግለጫ |
|---|---|---|
| 10 | እጅግ በጣም ጥሩ | ከተጠየቀው መሥፈርት በላይ የሆነ፣ በጣም ጠቃሚና በጣም አስፈላጊ የሆነ |
| 9 | በጣም ጥሩ | ከመስፈርት በላይ የሆነ፣ ለፍላጐታችን ጠቃሚ የሆነ |
| 7-8 | ጥሩ | መስፈርቶችን በሙሉ ያሟላ |
| 5-6 | አጥጋቢ | አብዛኛዎቹ መስፈርቶችን በተሻለ አኳኋን ያሟላ፣ የተወሰኑ ወሳኝ ያልሆኑ መስፈርቶችን ያላሟላ ሊሆን ይችላል |
| 3-4 | ደካማ | የተጠየቁትን መስፈርቶች በዝቅተኛ ደረጃ የሚያሟላ |
| 1-2 | በጣም ደካማ | ሁሉንም ሳይሆን የተወሰኑትን መስፈርቶች ብቻ ያሟላ ወይም ወሳኝ የሆኑትን መስፈርቶች ያላሟላ |
| 0 | የማያሟላ | በማንኛውም መንገድ የተጠየቁትን መስፈርቶች ያላሟላ |

የእያንዳንዱ የቴክኒክ መስፈርት ከላይ በተቀመጠው መሠረት የምዘና ነጥብ ይሰጣቸዋል፡፡ የምዘና ውጤት የሚሰላው የምዘና ነጥቡን ከእያንዳንዱ መስፈርት ጋር በማባዛት ነው፡፡ በዚሁ የአሠራር መንገድ መሠረት የሚገኘው ውጤት የጨረታዎችን ደረጃ ለማውጣት ያገለግላል፡፡

ሁለት ተጫራቾች እኩል ነጥብ በሚያገኙበት ጊዜ የሀገር ውስጥ ምርቶችን ወይም አገልግሎቶች ለሚያቀርብ ተጫራች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

የግዥ ፈፃሚው አካል ተጫራቾች እኩል የግምገማ ውጤት በሚያገኙበት ጊዜ ለመለየት እንዲቻል በተወሰኑ ነጥቦች ላይ የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይቻላል፡፡

ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ሳያቀርቡ ቢቀሩ ወይም በድጋሚ ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ አሁንም እኩል የግምገማ ነጥብ ቢያገኙና አሸናፊውን ተጫራች መለየት ሳይቻል ሲቀር እስከተቻለ ድረስ ተጫራቾቹ በተገኙበት አሸናፊው ተጫራች በዕጣ የሚለይ ይሆናል፡፡

### 3. የህይወት ዘመን ወጪ ትንተና

የህይወት ዘመን ወጪን ታሳቢ በማድረግ ለሚፈጸም ግዥ የሚከተለውን ቀመር መጠቀም ያስፈልጋል፡-

የሕይወት ዘመን ወጪ = የመጫረቻ ዋጋ +የሕይወት ዘመን ወጪዎች ድምር (ማለትም የስራ ማስኬጃ ወጪ + የጥገና እና የመለዋወጫ ወጪ+ የማስወገጃ
ወጪ) - የንብረቱ ቀሪ ዋጋ፡፡

### 4. የአካባቢ ጥበቃን ታሳቢ ስለማድረግ

ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ቴክሎጂዎችን፣ የታዳሽ ኃይል ምንጮችን በመጠቀም ወይም ዝቅተኛ ልቀቶችን በመጠቀም የተመረቱ ምርቶችን ሊያበረታቱ የሚችሉ መስፈርቶችን በሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነዶች ውስጥ ማካተት አለባቸው፡፡

### 5. የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን

የሚፈጸሙ ግዥዎች ለአካባቢው ማህበረሰብ ያላቸውን ጠቀሜታ እንዲሁም አዎንታዊ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ተጽዕኖዎችን ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፤

### ***6.*** ልዩ አስተያየት

የግዥ ፈፃሚው አካል በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 35 መሠረት በኢትዮጵያ ለሚመረቱ ምርቶች ልዩ አስተያየት እንዲደረግ የፈቀደ ከሆነ ለጨረታዎች ውድድር ዓላማ ሲባል ብቁ ጨረታዎች በሚከተሉት መልክ ይመደባሉ።

(ሀ) ምድብ "ሀ" - በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 35.3 መሰረት በሀገር ውስጥ ለተመረቱ ዕቃዎች የቀረቡ ጨረታዎች

(ለ) ምድብ "ለ" - ሌሎች ጨረታዎች

በአንቀጽ 35.3 መሠረት ምድብ "ለ" ተብለው በተለዩት ተጫራቾች ዋጋ ላይ ይጨመራል።

### ***7.*** የበርካታ ግዥዎች ግምገማ

በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 38.6 መሠረት ግዥ ፈፃሚው አካል አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ኮንትራቶችን ለተጫራቾች መስጠት ይችላል። አፈፃፀሙም እንደሚከተለው ይሆናል።

(ሀ) በተጫራቾች ንዑስ አንቀጽ 12.10 መሠረት ቢያንስ ተፈላጊውን መቶኛ ፍላጐትና መጠን ያሟሉትን ኮንትራቶች ወይም የሎት (lot) ግዥዎችን መገምገም፣

(ለ) ግምት ውስጥ የሚገቡ፣

የመገምገሚያ መስፈርቶችን በማሟላት ዝቅተኛ ዋጋ የቀረበበት እያንዳንዱ ሎት (lot) ግዥ፣በእያንዳንዱ የብዙ ምድብ (lot) ግዥ የቀረበው የዋጋ ቅናሽና የአፈፃፀም ዘዴዎች፣ በአቅርቦትና አፈፃፀም አቅም ዙሪያ ሊኖሩ የሚችሉትን ውስንነቶችና ችግሮች ግምት ውስጥ በማስገባት የሚኖረው የተሻለና ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ።

### ***8.*** አማራጭ ጨረታዎች

በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ 20.1 መሠረት አማራጭ ጨረታዎች የተፈቀዱ ከሆነ የሚገመገሙት እንደሚከተለው ይሆናል።

ክፍል 4

የጨረታ ቅፆች

ማውጫ

**ሀ. የጨረታ ማቅረቢያ ቅፅ........................................................................1**

**ለ. የዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ...................................................3**

**ሐ. የተጫራች አግባብነት ማረጋገጫ ሠንጠረዥ.......................................................5**

1. ስለ ተጫራቾች አጠቃላይ መረጃ..........................................................5
2. የፋይናንስ አቋም..........................................................................6
3. የቴክኒክ ብቃት፣ ክህሎትና የሥራ ልምድ.............................................7
4. የሙያ ብቃትና አቅም ......................................................................8
5. የጥራት መማረጋገጫ፣የሥራ አመራርና የቁጥጥር ሥነ-ሥርዓት.........................9
6. መሣሪያዎችና ፋሲሊቲዎች................................................................9
7. የተጫራቹ ኦዲት ኤጀንሲ...................................................................9
8. የኩባንያው አደረጃጀት......................................................................9
9. የባንክ አድራሻና ሂሳብ ቁጥር.............................................................9

**መ. የጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የአሽሙር ማህበር የመረጃ ቅጽ...............................10**

**ሠ. የጨረታ ዋስትና.............................................................................11**

**ረ. በአምራቹ የተሰጠ የአቅራቢነት ሥልጣን.........................................................13**

## ሀ. የጨረታ ማቅረቢያ ቅፅ

አቅራቢው

| | የተጫራቹ ሕጋዊ ስምና የአሁን አድራሻ | ዜግነት |
|---|---|---|
| ቡድን መሪው | | |
| ሌሎች አባላት | | |
| ወዘተ | | |

እኛ ከታች የፈረምነው ከላይ የተጠቀሰው የግዥ መለያ ቁጥር [የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ] እና የጨረታ ሰነዶችን በተመለከተ የሚከተለውን እናረጋግጣለን፡፡

(ሀ) የጨረታ ሰነዱን መርምረን በሙሉ ያለምንም ተቃውሞ ተቀብለናል፣

(ለ) በጨረታ ሰነዱ ፍላጐቶች መግለጫ ውስጥ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች፣ የማስረከቢያ ጊዜና ከጨረታ ሰነዶቹ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እናቀርባለን፡፡

(ሐ) ለሚቀርቡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች በጨረታ ሠነዱ ላይ በተገለጸው  የዋስትና ጊዜ ለማቅረብ ተስማምተናል፡፡

(መ) ጨረታችን ፀንቶ የሚቆየው በጨረታ ሰነዱ የተጫራች ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ በተጠቀሰው መሠረት ከጨረታ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

(ሠ) የጨረታ ውድድሩን ለመወሰን ሲባል እዚሁ ጨረታ ውስጥ ያቀረብነው ዋጋ እና ከታች የተዘረዘሩት ሀሳቦች ከሌሎች ተወዳዳሪዎችና ተጫራቾች ያለምንም ውይይት፣ ግንኙነት ወይም ስምምነት በግላችን ብቻ ነው፡፡

(ረ) ያቀረብነው የጨረታ ዋጋ ከዚህ በፊትም ሆነ ወደፊት ጨረታ ከመከፈቱ በፊት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሆነ ተብሎ ለሌሎች ተወዳዳሪዎች ወይም ተጫራቾች እንዲያውቁት አይደረግም፡፡

(ሰ) እኛና የንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢዎቻችን  የዚህ ጨረታ ሂደት በሚያስገኘው ውጤት መሠረት ለመፈፀም በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.1 በመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን  ብቁ አይደላችሁም ተብለን ከመንግሥት ግዥ አልታገድንም፡፡

(ሸ) እኛ አልከሰርንም ወይም በመክሰር ላይ አይደለንም፡፡ ከንግድ ሥራ አልታገድንም ወይም በማንኛውም ሁኔታ የፍ/ቤት ክስ የለብንም፡፡

(ቀ) በኢትዮጵያ የታክስ ህግ መሠረት የሚፈለግብንን ታክስ የመክፈል ግዴታችንን ተወጥተናል፡፡

(በ) በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 5 ስለማጭበርበርና ስለሙስና የተመለከተውን አንብበን ተረድተናል፡፡ ስለሆነም በጨረታ ሂደትም ሆነ በውል አፈጻጸም ጊዜ  አፈፃፀም ጊዜ በእንደዚህ ዓይነት ድርጊት የማንሳተፍ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

(ተ) ከማንኛውም ተጫራች ጋር በመሆን የምዝበራና የማጭበርበር ድርጊት አልፈፀምንም፡፡

(ቸ) ጨረታው ለእኛ እንዲወሰንልን ለማድረግ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ኃላፊ  ወይም የግዥ ሠራተኛ መደለያ አልሰጠንም፣ ወይም ለመስጠት ሀሳብ አላቀረብንም፡፡

(ኀ) በጨረታ ሰነዱ አማራጭ ጨረታዎችን ለማቅረብ ከተፈቀደላቸው ውጭ እንደተጫራች ከዚህ የጨረታ ሂደት ከአንድ በላይ ጨረታ አላቀረብንም፡፡

(ነ) በግዥ ፈፃሚው አካል ዋና የፍላጐት  መግለጫ ዝግጅት ወቅት አልተሳተፍንም፣ ምንም ዓይነት የጥቅም ግጭት የለብንም፡፡

(ኘ) ጨረታችን ተቀባይነት ካገኘ በአጠቃላይ የውሎች ሁኔታ አንቀጽ 50 በተጠየቀው መሠረት አስፈላጊው የውል አፈፃፀም ዋስትና እናቀርባለን፡፡

(አ) እኛም ሆንን የንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢዎቻችን እንዲሁም ለየትኛውም የውሉ ክፍል አቅራቢዎቻችን የምናቀርበው ዕቃ ከብቁ ሀገሮች ነው፡፡

(ከ) በውል ስምምነት አፈፃፀም ጊዜ ከላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች አስመልክቶ የተደረገ ለውጥ ካለ ወዲያውኑ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለማሳወቅ ቃል እንገባለን፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ ሆን ብለን የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ መረጃ ብናቀርብ ከዚህ ጨረታ ውጭ እንደምንሆንና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ከሚያካሂዳቸው ሌሎች የግዥ ውሎች መሳተፍ እንደምንከለከል ተረድተናል፡፡

(ኸ) ዋናው የውል ስምምነት ተዘጋጅቶ እስኪፈረም ድረስ ይህንን ጨረታም ሆነ የምትልኩልን የአሸናፊነት ማሳወቂያ እንደውል ሆነው እንደማያገለግሉና የአስገዳጅነት ባህሪይ እንደሌላቸው እንረዳለን፡፡

(ወ) ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብት እንዳላችሁ እንረዳለን፡፡

ከላይ የተገለጹትን ቃሎችና ቅድመ ሁኔታዎች መስማማቴን አረጋግጣለሁ፡፡

## ለ. የዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ

ቀንና ቦታ፦ *[ጨረታው የቀረበበት ቦታ እና ቀን(ቀን፣ወር እና ኢ.ም.)ይግባ]* ____________________

የግዥ መለያ ቁጥር፦ [የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ]

አማራጭ ቁጥር፦ *[የአማራጭ መለያ ቁጥር ይግባ]*

ለ፡

*[የግዥ ፈፃሚ አካል ስም ይግባ]*

*[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስም ይግባ]*

*[አድራሻ ይግባ]*

አዲስ አበባ

| ቁጥር | የዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች ዝርዝር | | መለኪያ | ብዛት | ነጠላ ዋጋ ከታክስ በፊት | | | | ቀረጦችና ታክሶች | ነጠላ ዋጋ ታክስን ጨምሮ | ጠቅላላ ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | | 4 | 5 | 6 | | | | 10 | 11 | 12 |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| የጨረታ ዋጋ በ ___________________*(የገንዘቡ ዓይነት ይጠቀስ)*__________ | | | | | | | | | | | |
| | ከሀገር ውስጥ የሚቀርብ ግብይት | ኢትዮጵያ | መለኪያ | ብዛት | | | | | | ነጠላ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| የጨረታ ዋጋ በኢትዮጵያ ብር ________________ | | | | | | | | | | | |

## ሐ. የተጫራች አግባብነት ማረጋገጫ ሠንጠረዥ

### 1. *ስለ ተጫራቾች አጠቃላይ መረጃ*

| | |
|---|---|
| የተጫራች ህጋዊ ስም | ............................. |
| የጋራ ማህበር ከሆነ የእያንዳንዱ አባል ህጋዊ ስም | ............................... |
| የምዝገባ ቦታ | ........................................... |
| የተመዘገበበት ሀገር ህጋዊ አድራሻ | .......................................... |
| የህጋዊ ወኪል መረጃ | ስም፦................<br>ኃላፊነት፦.................<br>አድራሻ፦.................<br>ስልክ/ፋክስ ቁጥር፦.............<br>ኢሜይል አድራሻ.................. |
| የተያያዙ የኦሪጅናል ሰነዶች ቅጂዎች | የጋራ ማህበር ከሆነ የጋራ ማህበር ለማቋቋም የስምምነት ደብዳቤ ወይም ማህበሩ የተቋቋመበት ስምምነት (በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.1) መሠረት |
| | የጋራ ማህበሩ የመረጃ ቅፅ |
| | በግዥ ፈፃሚው ሀገር በመንግሥት ይዞታ የሚተዳደር ከሆነ በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.4 መሠረት በንግድ ህግ መርህ የተቋቋመና የህግና የፋይናንስ ነፃነት ያለው ለመሆኑ የሚያረጋግጡ ሰነዶች |

በጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽሙር ማህበሩ ስም የፈረመውና ከላይ የተጠቀሰው ሰው ይህንኑ ለመፈፀም የሚያስችለውን ሙሉ ኃላፊነት የተሰጠው ለመሆኑ የሚያረጋግጥ ህጋዊ የውክልና ሰነድ አያይዘን አቅርበናል፡፡

### 2. *የፋይናንስ አቋም*

*[የተጫራች ስም ይግባ]* በዚሁ ጨረታ በውጭ ኦዲተር ተረጋግጦ በቀረበው የፋይናንስ መረጃ መሠረት የማዕቀፍ አቅርቦት ውሉን ለማከናወን በቂና አስተማማኝ የገንዘብ አቅም አለን፡፡ የሚከተለው ሠንጠረዥ የፋይናንስ መረጃዎችን ያሳያል፡፡ መረጃዎች የተዘጋጁት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርትን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ሠንጠረዡ የየዓመቱን የፋይናንስ ሁኔታ ለማወዳደር በሚያስችል መልኩ ቀርቧል፡፡

| የፋይናንስ መረጃ | ያለፉት ዓመታት መረጃ [የአመት ብዛት ይግባ] በ |
|---|---|

| | [የመገበያያ ገንዘብ አይነት ይግባ] | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 2ኛ ዓመት | 1ኛ ዓመት | ያለፈው ዓመት | የአሁኑ ዓመት | አማካይ |
| ሀ. የገቢና ወጪ ዝርዝር (ከባላንስ ሺት መረጃ) | | | | | |
| 1. ጠቅላላ ሀብት | | | | | |
| 2. ጠቅላላ ዕዳ | | | | | |
| I. ልዩነት (1-2) | | | | | |
| 3. ወቅታዊ ሀብት | | | | | |
| 4. የአጭር ጊዜ ዕዳ | | | | | |
| II. ሥራ ማስኬጃ (3-4) | | | | | |
| ለ. የትርፍና ኪሳራ ዝርዝር (ከኢንካም ስቴትመንት መረጃ) | | | | | |
| 1. ጠቅላላ ሀብት | | | | | |
| 2. ከታክስ በፊት ትርፍ | | | | | |
| 3. ኪሣራ | | | | | |

በጨረታ መረጃ ሠንጠረዡ መሠረት ከላይ ካቀረብነው የፋይናንስ መረጃ በተጨማሪ የፋይናንስ አቋማችንን የሚያረጋግጡ የሚከተሉት ሰነዶችን አያይዘን አቅርበናል፡፡

የተያያዙት ሰነዶች ከሚከተሉት ሁኔታዎች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው፡፡

- ሰነዶቹ የአጋር ወይም የጋራ ማህበር ወይም የእህት ኩባንያን ሳይሆን የተጫራቹን የፋይናንስ ሁኔታ የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡
- የፋይናንስ መረጃዎቹ በተመሰከረለት አካውንታንት ኦዲት የተደረጉ ናቸው፡፡
- የፋይናንስ መረጃዎቹ የተሟሉና አስፈላጊ የሆኑ ማስታወሻዎችን ያካተቱ ናቸው፡፡
- የፋይናንስ መረጃዎቹ ከተጠናቀቀና ኦዲት ከተደረገው የሂሳብ ዘመን ጋር የተጣጣሙ ናቸው፡፡

| ዓመታዊ የገቢ መረጃ | |
|---|---|
| ዓመት | መጠንና የገንዘቡ ዓይነት |
| | |
| | |
| | |
| አማካይ ዓመታዊ ገቢ | |

አማካይ ዓመታዊ ገቢ የሚሰላው በክፍል 3 የግምገማና ብቃት መስፈርቶች ላይ በተመለከተው መንገድ በዓመታት ውስጥ የተጠናቀቁና በሂደት ላይ ያሉ የአቅርቦት ውል ስምምነቶች ጠቅላላ ዋጋ ተደምሮ ለነዚሁ ዓመታት በማካፈል ይሆናል፡፡

## 3. *የቴክኒክ ብቃት፣ ክህሎትና የሥራ ልምድ*

በጨረታው የተመለከቱትን አገልግሎቶች በተሟላ የቴክኒክና የፕሮፌሽናል ችሎታ ማከናወን እንደምንችል ለማረጋገጥ ባለፉት ዓመታት በአጥጋቢ ሁኔታ የፈፀምናቸውን የአቅርቦት ውል ስምምነቶች ዝርዝር ከታች በተመለከተው ሠንጠረዥ አቅርበናል፡፡

| | የተጫራቹ ወይም አጋር/የጋራ ማህበር ስም | |
|---|---|---|
| 1 | የአቅርቦት ውል ስምምነት ስም | |
| | አገር | |
| 2 | የደንበኛው ስም | |
| | የደንበኛው አድራሻ | |
| | የተጠሪ ስም | |
| | የተጠሪው ኃላፊነት | |
| | የስልክ ቁጥር | |
| | ኢ.ሜይል | |
| 3 | የአገልግሎቱ ዓይነት በጨረታ ሰነዱ ከተጠቀሰው የአቅርቦት ውል ስምምነት ጋር ያለው ተዛማጅነት | |
| 4 | የአቅርቦት ውል ስምምነት ኃላፊነት | ☐ ዋና ተዋዋይ<br>☐ ንዑስ ተዋዋይ<br>☐ አጋር/የጋራ ማህበር |
| 5 | አጠቃላይ የአቅርቦት መጠን በ_____. | |
| 6 | ጨረታው የተሰጠበት/የተጠናቀቀበት | |
| 7 | የመጨረሻ ርክክብ ተፈጽሟል | አዎ☐ ገና ነው☐ አይደለም☐ |
| 8 | በዚሁ ሥራ የተሰማሩ ሠራተኞች ብዛት | |
| 9 | በንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢነት የተሰጡ አገልግሎቶች ካሉ በግምት በመቶኛ ጠቅላላ የኮንትራት መጠንና የኮንትራት ዓይነት ይገለጽ | |
| 10 | ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች | |

የአቅርቦት ውሎችን በአጥጋቢ ሁኔታ ስለመፈፀማችን ከደንበኞቻችን የተሰጡ ማረጋገጫዎች/ ሰርቲፊኬቶች ከዚሁ ጋር አያይዘን አቅረበናል፡፡

## 4. *የሙያ ብቃትና አቅም*

የሙያ ብቃታችንና አቅማችንን ለማረጋገጥ ይረዳ ዘንድ በአሁኑና ባለፉት ሁለት ዓመታት የነበረ የሰው ኃይላችን የሚያሳይ ስታትስቲክስ በሚከተለው ሠንጠረዥ አቅርበናል፡፡

| አማካይ የሰው ኃይል | ከአንድ ዓመት በፊት | | ባለፈው ዓመት | | በዚህ ዓመት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አጠቃላይ | ቁልፍ ባለሙያዎች በሙያ ደረጃ | አጠቃላይ | ቁልፍ ባለሙያዎች በሙያ ደረጃ | አጠቃላይ | ቁልፍ ባለሙያዎች በሙያ ደረጃ |
| ቋሚ | | | | | | |
| ጊዜያዊ | | | | | | |
| ጠቅላላ | | | | | | |

5. *የጥራት መግረጋገጫ፣የሥራ አመራርና የቁጥጥር ሥነ-ሥርዓት*

*[ተጫራቹ ውሉን በአጥጋቢ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚከተላቸው ስርአቶችና ዝርዝር የጥራት ቁጥጥር ሂደቶች በዝርዝር ማስቀመጥ ይኖርበታል።]*

6. *መሣሪያዎችና ፋሲሊቲዎች*

*[ተጫራቹ ስራውን በአግባቡ ለማስፈጸም የሚረዱ በቂ መሳሪያዎችና ፋሲሊቲ ያለው መሆን አለመሆኑ መጥቀስ ይኖርበታል።]*

7. *የተጫራች ኦዲት ኤጀንሲ*

*[ተጫራቹ የኦዲተሮቹን ስም፤ አድራሻና ስልክ ቁጥር መስጠት ይኖርበታል።]*

8. *የኩባንያው አደረጃጀት*

*[ተጫራቹ ስራውን ከሌሎች ፕሮጀክቶች ጋር እንዴት አቀናጅቶ መስራት እንዳሰበ መግለጽ አለበት።]*

9. *የባንክ አድራሻና ሂሳብ ቁጥር*

ክፍያ የሚፈፀምበት የባንክ ሂሳብ ቁጥራችን የሚከተለው ነው። *[የባንክ ሂሳብ ቁጥር ይግባ]*

## መ. የጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽሙር ማህበር የመረጃ ቅጽ

| | | |
|---|---|---|
| .1 | በአገር በቀል ድርጅቶች መካከል ለሚመሰረት ጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽሙር ማህበሩ ስም፦ | [በአገር በቀል ድርጅቶች መካከል ለሚመሰረት ጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽሙር ማህበሩ ስም ይግባ] |
| 2 | የቦርዱ አድራሻ፦ | |
| | ፖ.ሳ.ቁ.፦ | [ፖ.ሣ.ቁ.ይግባ] |
| | የመንገድ ስም፦ | [የመንገድ ስም ይግባ] |
| | ከተማ፦ | [የከተማ ስም ይግባ] |
| | ፖ.ሳ.ኮድ.፦ | [ፖ.ሳ. ኮድ ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ] |
| | አገር፦ | [አገር ይግባ] |
| | ስልክ ቁጥር፦ | [የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ] |
| | ፋክስ ቁጥር፦ | [የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የፋክስ ቁጥር ይግባ] |
| | ኢሜይል አድራሻ፦ | [ኢሜይል አድራሻ ይግባ] |
| 3 | በኢትዮጵያ የማህበሩ/ጊዜያዊ ማህበሩ ተወካይ፦ | |
| | ፖ.ሳ.ቁ.፦ | [ፖ.ሣ.ቁ.ይግባ] |
| | የመንገድ ስም፦ | [የመንገድ ስም ይግባ] |
| | ከተማ፦ | [የከተማ ስም ይግባ] |
| | ፖ.ሳ.ኮድ.፦ | [ፖ.ሳ. ኮድ ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ] |
| | ስልክ ቁጥር፦ | [የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ] |
| | ፋክስ ቁጥር፦ | [የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የፋክስ ቁጥር ይግባ] |
| | ኢሜይል አድራሻ፦ | [ኢሜይል አድራሻ ይግባ] |
| 4 | የአባላት ስም | |
| | አባል 1፦ | [የአባሉ ህጋዊ ስምና አድራሻ ይግባ] |
| | አባል 2፦ | [የአባሉ ህጋዊ ስምና አድራሻ ይግባ] |

| | | |
|---|---|---|
| | ወዘተ. | [የአባሉ ህጋዊ ስምና አድራሻ ይግባ] |
| 5 | የቡድን መሪው አባል ስም | [የአባሉ ህጋዊ ስምና አድራሻ ይግባ] |
| 6 | የጋራ ማህበሩ/ጊዜያዊ ማህበሩ የተቋቋመበት ማስረጃ | |
| | የተፈረመበት ቀን፦ | [ቀን ይግባ] |
| | ቦታ | [ቦታ ይግባ] |
| 7 | እያንዳንዱ የሚሰራው የስራ አይነት ተጠቅሶ የአባላት የኃላፊነት መጠን በመቶኛ | [የአባላቱ የሀላፊነት ድርሻ በመቶኛ ይግባ] |

ስም፦ [ጨረታው የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስም ይግባ]
ኃላፊነት፦ [ጨረታው የሚፈርመው ሰው ኃላፊነት ይግባ]
ፊርማ፦ [እላይ የተጠቀሰው ሀላፊነትና ስም ያለው ሰው ፊርማ ይግባ]
ጨረታው ለመፈረም ሙሉ ውክልና የተሰጠው አካል [የተጫራቹ ሙሉ ስም ይግባ]
ቀን: [ቀን ይግባ] [ወር ይግባ] [ፊርማው የተፈረመበት ኢ.ም. ይግባ]

ለተጫራቾች ማስታወሻ፤

ይህ የጨረታ ዋስትና፣ ዋስትና በሰጠው የፋይናንስ ተቋም አርማ ባለበት ሰፍሮ እና የጨረታው ዋስትና የመፈረም ስልጣን ባለው አካል ተፈርሞ ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት።

## ሠ. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና

ቀን:- *[ጨረታው የቀረበበት ቀን(ቀን፣ወር እና አመት ምህረት)ይግባ]*
የግዥ መለያ ቁጥር: *[የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ]*
አማራጭ ቁጥር: *[የአማራጭ መለያ ቁጥር ይግባ]*

ለ:- *[የግዥ ፈፃሚ አካል ሙሉ ስም ይግባ]*

የተጫራች ሙሉ ስም ይግባ (ከዚህ በኋላ “ተጫራች” እየተባለ የሚጠራው) በግዥ መለያ ቁጥር [የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ] በተደረገው ጥሪ መሠረት የዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች አጭር መግለጫ ይፃፍ ለማቅረብ የመወዳደሪያ ሐሳብ (ከዚህ በኋላ “የመወዳደሪያ ሐሳብ’’ እየተባለ የሚጠራውን) በቀን *[ጨረታው የቀረበበት ቀን(ቀን፣ወር እና አመት ምህረት)ይግባ]* ያቀረበ በመሆኑ።

ሁሉም ሰዎች እንደሚያውቁት እኛ የጨረታ ዋስትና ሰጪ ድርጅት ሙሉ ስም፤ አድራሻና የተመዘገበበት አገር ስም ይሞላ የሆነ (ከዚህ በኋላ “ዋስ” እየተባልን የምንጠራ) ለ የግዥ ፈፃሚው አካል ሙሉ ስም ይሞላ (ከዚህ በኋላ “የግዥ ፈፃሚ አካል” እየተባለ ለሚጠራው) የጨረታ ዋስትናው ገንዘብና መጠን በአሀዝና ~~ቃላትና~~ በፊደል ይሞላ ለመክፈል የዋስትና ግዴታ የገባን ሲሆን ከዚህ በላይ ለተገለፀው ግዥ ፈፃሚ አካል ክፍያው በሙሉ እና በትክክል የሚከፈል ለመሆኑ ወራሾቻችን ወይም መብት የሚተላለፍላቸውን ሰዎች ግዴታ አስገብተናል። ለዚህም የዋሱ ማኅተም በ___(ቀን) _____ (ወር) ______ ዓ.ም. *[ቀን በቁጥር ይግባ]፣ [ወር ይግባ]፣[ኢ.ም. ይግባ]* ታትሞበታል።

ይህ የዋስትና ሰነድ ተፈፃሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ይሆናል።

1) በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 21.2 ካልሆነ በስተቀር ተጫራቹ በጨረታ ማቅረቢያ ሰንጠረዥ ውስጥ በገለጸው መሰረት ጨረታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ከጨረታው ከወጣ፤ ወይም
2) ግዥ ፈጻሚው አካል ጨረታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ያቀረበው የመወዳደሪያ ሐሳብ ተቀባይነት ማግኘቱን ለተጫራቹ ካሳወቀው በኋላ ተጫራቹ ጨረታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ፣
   ሀ/ ውሉን ለመፈረም ወይም/
   ለ/ በተጫራቶች መመሪያ አንቀጽ 46 መሠረት የአፈጻጸም ዋስትና ለማቅረብ፣
   ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ።

የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሁኔታዎች በማጋጠማቸው ምክንያት ገንዘቡ ሊከፈለው እንደሚገባ ጠቅሶ ከጠየቀ ለጥያቄው ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ ላይ እስከተጠቀሰው ገንዘብ መጠን ድረስ ለግዥ ፈፃሚው አካል ለመክፈል ግዴታ እንገባለን።

ይህ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የጨረታ ዋጋው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካበቃበት ዕለት ጀምሮ እስከ ሃያ ስምንተኛው (28) ቀን ድረስ (ሃያ ስምንተኛውን ቀን ጨምሮ) የፀና ሆኖ የሚቆይ ሲሆን ማኛቸውም በጉዳዩ ላይ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ከተጠቀሰው ጊዜ የዘገየ መሆን የለበትም።

ስም፦ *[ጨረታው የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስም ይግባ]*
ኃላፊነት፦ *[ጨረታው የሚፈርመው ሰው ኃላፊነት ይግባ]*

ፊርማ፦ *[እላይ የተጠቀሰው ሀላፊነትና ስም ያለው ሰው ፊርማ ይግባ]*

ጨረታው ለመፈረም ሙሉ ውክልና የተሰጠው አካል *[የተጫራቹ ሙሉ ስም ይግባ]*

ቀን፡ፊርማው የተፈረመበት *[ቀን ይግባ] [ወር ይግባ] [ኢ.ም.ይግባ]*

**[ማስታወሻ፤ይህ ከአምራቹ የተሰጠ የአቅራቢነት ፈቃድ፤ ፈቃድ በሰጠው የማምረቻ ተቋም አርማ ባለበት ደብዳቤ ሰፍሮ እና የመፈረም ስልጣን ባለው አካል ተፈርሞ ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት።]**

**ረ. በአምራቹ የተሰጠ የአቅራቢነት ሥልጣን**

ቀን:- *[ጨረታው የቀረበበት ቀን(ቀን፣ወር እና አመተ ምህረት)ይግባ*]

የግዥ መለያ ቁጥር:- *[የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ]*

አማራጭ ቁጥር:- *[የአማራጭ መለያ ቁጥር ይግባ*]

ለ [የግዥ ፈፃሚ አካል ሙሉ ስም ይግባ]

የ *<u>የዕቃዎች አጭር መግለጫ ይግባ</u>* ይፋዊ አምራች የሆነው እና በ *<u>የአምራቹን ሙሉ አድራሻ የጻፍ</u>* ፋብሪካዎች ያሉት *<u>የአምራቹን ሙሉ ስም ይግባ</u>* የወጣውን የጨረታ ማስታወቂያ በተመለከተ *<u>የተጫራቹን ሙሉ ስም አስገባ</u>* የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ እንዲያስገባ ስልጣን ሰጥተነዋል፣ አላማው እኛ ያመረትናቸውን የሚከተሉትን *<u>የዕቃዎች ስምና አጭር መግለጫ ይግባ</u>* ለማቅረብና ቀጥሎም ለመደራደርና ውሉን ለመፈረም ነው።

በዚህ ጨረታ ማስታወቂያ መሰረት እላይ የተጠቀሰው ተጫራች ያቀረባቸውን ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች በተመለከተ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 25 መሠረት እነሆ ሙሉ ጋራንቲና ዋስትና እንሰጣለን።

ስም፦ *[ከአምራቹ የተሰጠ የአቅራቢነት ፈቃድ የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስም ይግባ]*

ኃላፊነት፦ *[ከአምራቹ የተሰጠ የአቅራቢነት ፈቃድ የሚፈርመው ሰው ህጋዊ ኃላፊነት ይግባ]*

ፊርማ፦ *[እላይ የተጠቀሰው ሀላፊነትና ስም ያለው ሰው ፊርማ ይግባ]*

ጨረታው ለመፈረም ሙሉ ውክልና የተሰጠው አካል *[የተጫራቹ ሙሉ ስም ይግባ]*

ቀን:ፊርማው የተፈረመበት *[ቀን ይግባ] [ወር ይግባ] [አ.ም. ይግባ*]

# ክፍል 5፡ የእቃዎቹ መነሻ ብቁ ሀገሮች (ብቁ ሀገሮች)

የግዥ መለያ ቁጥር:-

የሚከተሉት ድንጋጌዎች ተግባራዊ ከሚሆኑባቸው ሀገሮች በስተቀር ከሌሎች ሀገሮች የሚቀርቡ ዕቃዎች ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

(ሀ) ተፈላጊ የሆነውን አገልግሎት ለመስጠት የሚደረገውን ውድድር የሚያስተጓጉል ያለመሆኑ በመንግሥት እስከታመነበት ድረስ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በሕግ ወይም በደንብ ከአንድ የተወሰነ ሀገር የንግድ ግንኙነት እንዳይደረግ የከለከለ ከሆነ፣

(ለ) በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት በቻርተሩ ምዕራፍ 7 መሠረት የተላለፈውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ከአንድ ሀገር ማንኛውም አገልግሎት እንዳይገዛ ወይም ለዚያ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት ክፍያዎች እንዳይፈፀም የከለከለ ከሆነ።

# ምዕራፍ 2

## የፍላጎቶች መግለጫ

### ክፍል 6፡ የፍላጎቶች መግለጫ

ማውጫ


**ሀ. የቴክኒክ ዝርዝር አጠቃላይ ማስታወሻ....................................................1**

**ለ. የቴክኒክ ዝርዝር፣ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብና የአግባብነት ሠንጠረዥ...................................1**

**ሐ. የቴክኒክና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ፍላጎቶች..................................................3**

1. የዕቃ አቅርቦት.....................................................................................3
2. ዕድሳትና ጥገና .....................................................................................3
3. መለዋወጫዎች/አቅርቦቶች........................................................................4
4. ሰነዶች ናሙናዎች.................................................................................4
5. ሌሎች ፍላጎቶች...................................................................................4

**መ. ንድፎች...........................................................................4**

**ሀ. የቴክኒክ ዝርዝር አጠቃላይ ማስታወሻ**

የቴክኒክ ዝርዝር የሚቀርቡበት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ሊያሟሉ የሚገባቸውን ፍላጐቶች የሚገልጽ ሲሆን የውሉ አካል ከሆኑ ሌሎች ሰነዶች ጋር አብሮ የሚነበብ ነው። የውሉ አካል በሆኑ ሰነዶች ላይ አጠራጣሪ ሁኔታዎች በሚኖሩበት ጊዜ አቅራቢው የውሉ ሁኔታዎች በሚፈቅዱት መሠረት የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ማብራሪያ መጠየቅ አለበት።

**ለ. የቴክኒክ ዝርዝር፣ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብና የአግባብነት ሠንጠረዥ**

ቦታና ቀን፦ *[ጨረታው የቀረበበት ቦታ እና ቀን(ቀን፣ወር እና ዓ.ም.)ይግባ].*
የግዥ መለያ ቁጥር፦ *[የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ]*
ለ፡

*[የግዥ ፈፃሚ አካል ስም ይግባ]*
*[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስም ይግባ]*
*[ፖ.ሣ.ቁ.ይግባ]*
*[አድራሻ ይግባ]*
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ሀ. ተጫራቾች የሚከተለውን ሠንጠረዥ ሞልተው እንዲያቀርቡ ተጠይቀዋል።

ሁለተኛው ቁልቁል ረድፍ (column) የሚያሳየው የተጠየቀውን ዕቃ ዝርዝር ነው። (በተጫራቹ ሊለወጥ አይችልም)

አምስተኛው ቁልቁል ረድፍ (column) የሚያሳየው የመወዳደሪያ ሀሳብ ሲሆን በተጫራቹ የሚሞላ ነው። ("አዎ" ወይም "ያሟላል" ብሎ መሙላት ብቻ በቂ አይደለም)

ስድስተኛው ቁልቁል ረድፍ (column) የሚያሳየው በተጫራቹ የቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ የተጠየቀውን ሁሉ "ማሟላቱን" ወይም "አለማሟላቱን" ሲሆን የማያሟላ በሚሆንበት ጊዜ ተጫራቹ የማጣቀሻ ሰነዶችን በመጥቀስ ያላሟላበትን ዝርዝር ሁኔታ መግለጽ አለበት።

ሰባተኛው ቁልቁል ረድፍ (column) ለገምጋሚዎች ክፍት ይሆናል።

ለ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጫራቹ በፍላጐት መግለጫው ከተመለከተው ወይም በተለየ ሁኔታ ያቀረበውን የፍላጎት መግለጫ ከጨረታው ጋር ማቅረብ አለበት።

ሐ. ተጫራቹ የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት የሚያረካ እስከሆነ ድረስ በፍላጐት መግለጫው ከተመለከተው ጋር በተመሳሳይ ወይም በተሻለ ሁኔታ ጥራት ያላቸው ዕቃዎች ወይም የዕቃ መለያ ቁጥሮች (catalogue) በመጥቀስ የመወዳደሪያ ሀሳቡን ማቅረብ ይችላል።

መ. ተጫራቹ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 25 በተመለከተው መሠረት ለሚያቀርባቸው ዕቃዎች ዋስትና (waranty) ማቅረብ አለበት።

ሠ. የሚቀርቡት ሰነዶች የተመረጠው ሞዴልና ሌሎች አማራጮች ካሉ በመጥቀስ የጨረታው ገምጋሚዎች ሊረዱት በሚችል መልኩ መቅረብ አለበት።

ረ. የሚቀርቡት ዕቃዎች በራሱ በአቅራቢው የተገጣጠሙ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ስም ያላቸው መሆን አለባቸው። (ራሱ የታወቀ ህጋዊ አምራች ካልሆነ በስተቀር)።

ሰ. ተጫራቹ የተጠየቁት ዕቃዎችና በመወዳደሪያ ሃሳብ ባቀረባቸው ዕቃዎች መካከል ያለው ልዩነት በግልጽ በመረዳት የጨረታው ገምጋሚዎች አካላት ሊገባቸው በሚችል መልክ ማቅረብ አለበት። ሞዴላቸውና ዓይነታቸው በትክክል ለመለየት በማይቻል ሁኔታ የሚቀርቡ ጨረታዎች በገምጋሚው ኮሚቴ ውድቅ ሊደረጉ ይችላሉ።

| ተራ ቁጥር | ዝቅተኛ ተፈላጊው የቴክኒክ መመዘኛ ነጥቦች መደበኛ መለኪያዎችን ጨምሮ | መለ ኪያ | ብዛ ት | በተጫራቹ የቀረበ የቴክኒክመግለ ጫ | በቀረበው የቴክኒክ መመዘኛ በተጫራቹ የተሰጠ መግለጫ | በቀረበው የቴክኒክ መመዘኛ በገምጋሚው የተሰጠ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

<u>አዝሎች</u>

1. በጨረታ መረጃ ሠንጠረዥ ላይ የተጠየቀ ከሆነ በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 17 መሠረት የቴክኒክ የጽሑፍ መረጃ
2. በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 25 መሠረት በድርጅቱ የተሰጠ ዋስትና
3. በተጨራቾች መመሪያ አንቀጽ 5.6 መሠረት በዕቃው አምራች የተሰጠ የማረጋገጫ ደብዳቤ

## ሐ. የቴክኒክና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ፍላጐቶች

### 1. *የዕቃ አቅርቦት*

ሁሉም የሚቀርቡት ዕቃዎች ዓለም አቀፍ ደረጃዎችንና (DIN, ISO, AISI, ወዘተ.) የኢትዮጵያ ጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን የጥራት ደረጃን ማሟላት አለባቸው። ከአምራቹ የተሰጠ የማረጋገጫ ደብዳቤም አብሮ መቅረብ አለበት።

ሁሉም የሚቀርቡት ዕቃዎች ርክክብ በሚደረግበት ወቅት ያለውን የደህንነት ፍላጐት ማሟላት አለባቸው።

በዚህ ስምምነት የሚቀርቡ ዕቃዎች አዲስ፣ ከዚህ በፊት ያልተሰራባቸው ወቅታዊ ሞዴሎችና ዘመናዊና ወቅታዊ የሆነ የተሻለ ንድፍ ያካተቱ መሆን አለባቸው።

በአንድ ነጠላ (lot) ግዥ ውስጥ የተካተቱ ዕቃዎች በሙሉ አንድ ላይ ተጓጉዘው መቅረብ አለባቸው። በከፊል ማቅረብ አይፈቀድም።

ሁሉም የሚቀርቡ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች የኢትዮጵያን የኤሌክትሪክ ደረጃ (220±10 ቮልት AC, 50HZ) የሚያሟሉ መሆን አለባቸው። ተያያዥ የኤሌክትሪክ ገመዶች፣ ማከፋፈያዎችና የኃይል ማሠራጫዎች አብረው መቅረብ አለባቸው። ጥቅም ላይ በሚውሉበት አካባቢ ካለው የአየር ሁኔታ ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው።

**2.** *ዕድሳትና ጥገና*

ጥሩ ስምና ልምድ ያለው የሀገር ውስጥ የቴክኒክ ተወካይ ወይም በመሳሪያና በሰው ኃይል የተደራጀ አገልግሎት የሚሰጥ የጥገና ማዕከል መኖር ግዴታ ሲሆን ይህንኑ በሚመለከት በሚቀርበው የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ውስጥ መጠቀስ አለበት፡፡

**3.** *መለዋወጫዎች/አቅርቦቶች*

አቅራቢው የሚያቀርባቸው ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ልዩና የተለመዱ መለዋወጫዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ይህም በዋስትና ጊዜ በተወከለው የጥገና ማዕከል አስቸኳይ ጥገና ወይም መለዋወጫ መቀየር ሲያስፈልግ ለማስፈፀም ይረዳል፡፡

**4.** *ሰነዶች ናሙናዎች*

ለእያንዳንዱ ምድብ → ኦፕሬሽናል ማንዋሎች ይቀርባሉ

ለእያንዳንዱ ምድብ → የአገልግሎት ማንዋሎች ይቀርባሉ

**5.** *ሌሎች ፍላጐቶች*

(ሌሎች ፍላጎቶች ካሉ ይዘርዘሩ)

*መ. ንድፎች*

የግዥ መለያ ቁጥር፦

| የተያያዥ ንድፎች ዝርዝር | | |
|---|---|---|
| የንድፍ ቁጥር | የንድፍ ስም | ዓላማ |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

# ምዕራፍ 3፡ ውል

## ክፍል 7፡ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች

### ማውጫ


**ሀ. አጠቃላይ ድንጋጌዎች....................................................1**

1. ፍቺዎች....................................................1
2. ኃላፊነት ስለመስጠት....................................................6
3. የተዋዋይ ወገኖች ግንኙነት....................................................6
4. ልዩ ጥንቃቄ....................................................7
5. ማጭበርበርና ሙስና....................................................7
6. ትርጓሜ....................................................9

**ለ. ውል....................................................10**

7. የውል ሰነዶች....................................................10
8. ውሉን የሚገዛ ሕግ....................................................11
9. የጨረታ ቋንቋ....................................................11
10. ማስታወቂያዎችና የፅሑፍ ግንኙነቶች....................................................11
11. ስልጣን ያለው ሀላፊ (ተወካይ ባለስልጣን)....................................................12
12. የሶስተኛ ወገን መብቶች....................................................12
13. የሶስተኛ ወገን ተጠቀሚዎች....................................................12
14. ኃላፊነትን ለሌላ ስለማስተላለፍ....................................................14
15. ንዑስ ተቋራጭ (ኮንትራክተር)....................................................15
16. የውል ማሻሻያዎችና ለውጦች....................................................16
17. በሕጐችና በደንቦች ላይ የሚደረግ ለውጥ....................................................17
18. ግብሮችና ታክሶች....................................................17
19. አስገዳጅ ሁኔታዎች....................................................18
20. ውልን ስለማፍረስ....................................................19
21. ኃላፊነት ለሌላ ማስተላለፍን ስለማገድ....................................................20
22. ውል መቋረጥ....................................................20
23. ከውል መቋረጥ በኋላ ያሉ ሁኔታዎች....................................................23
24. የመብቶችና ግዴታዎች መቋረጥ....................................................23
25. ዋስትና (WARRANTY)....................................................24
26. የአለመግባባቶች አፈታት....................................................24
27. የታወቁ ጉዳቶች ካሳ....................................................25
28. ምስጢራዊነት....................................................26
29. የፈጠራ ባለቤትነት መብት....................................................28
30. ልዩ ልዩ....................................................28

**ሐ. የግዥ ፈፃሚው አካል ግዴታዎች....................................................29**

31. ድጋፍ ማድረግ....................................................29

**መ. ክፍያ .......... 29**

32. የውል ዋጋ .......... 29
33. የዋጋ ማስተካከያ .......... 30
34. የክፍያ አፈጻጸም .......... 34
36. የውል ቅፆች .......... 36

**ረ. የአቅራቢው ግዴታዎች .......... 37**

36. የአቅራቢው ኃላፊነቶች .......... 37
37. የጋራ/ሽርክና/ ማህበር፣ ጊዜያዊ ማህበርና ማህበር .......... 37
38. ብቁነት (ውል ለመፈፀም) .......... 37
39. የስነ-ምግባር ደንቦች .......... 37
40. የጥቅም ግጭቶች .......... 38
41. የፈጠራ ባለቤትነት የካሣ ክፍያ .......... 39
42. የባለዕዳነት ገደብ .......... 40
43. አእምሯዊ ንብረት .......... 40
44. የመድን ዋስትና (ኢንሹራንስ) .......... 41
45. የምርቶች መረጃ .......... 41
46. የሂሳብ አያያዝ፣ ቁጥጥርና ኦዲት .......... 42
47. የመረጃ (ዳታ) አጠባበቅ .......... 42
48. የቀረቡ ዕቃዎች መጠንና ዋጋን የተመለከተ መግለጫ .......... 43
49. ክለሳ .......... 43
50. የውል ማስከበሪያ ዋስትና .......... 44

**ረ. የውል አፈፃፀም .......... 44**

51. የአቅርቦት ወሰን .......... 44
52. ዝርዝር መግለጫዎችና ደረጃዎች .......... 45
53. ርክክብ (ማስረከብ) .......... 45
54. የማስረከቢያ ጊዜ .......... 46
55. ማሸግ፣ ምልክት ማድረግና ሰነዶች .......... 47
56. ዕቃዎችን ስለመለየት .......... 47
57. የዕቃ ማሸጊያ ኮንቴነሮችና ሳጥኖች .......... 48
59. መሣሪያዎች .......... 48
60. ጥራት .......... 48
61. ምርመራዎችና ሙከራዎች .......... 49
62. ዕቃዎችን አለመረከብ .......... 50
63. ጊዜ ስለማራዘም .......... 51
64. የአፈፃፀም መለኪያ .......... 51

ክፍል 7

አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች

**ሀ. አጠቃላይ ድንጋጌዎች**

**1. ፍቺዎች**

1.1 በዚህ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች የተጠቀሱት ርዕሶች የውሉን ትርጉም አይወስኑም፤ አይለውጡም ወይም አይቀይሩም።

1.2 በሌላ አግባብ ካልተጠቀሰ በስተቀር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቃላትና ሀረጎች በዚህ ውል ውስጥ የሚከተለው ትርጉም ይኖራቸዋል።

| | |
|---|---|
| ሀ. ስልጣን ያለው ሀላፊ | ማለት ይህንን ውል ለማስፈፀም በማዕቀፍ ስምምነት ፈራውና በተናጠል ውል ከሚገባው ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ኃላፊነት የተሰጠውና ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት የሚወክል ሲሆን አቅራቢው በኢ.ጂ.ፒ ሲስተም እንዲያውቀው የተደረገ ሰው ማለት ነው። |
| ለ. መክሰር | ማለት ማንኛውም ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ፣<br>መክሰሩን ለማስታወቅ ለሚመለከተው ህጋዊ<br>አካል (ለፍ/ቤት) ማመልከቻ በማቅረብ ሂደት ላይ የሚገኝ ወይም ማመልከቻ ያቀረበ፣<br>ለአበዳሪዎች ጥቅም ሲባል የተለየ የአሰራር ስርአት ተበጅቶለት የሚሰራ፣<br>የከሰረ መሆኑ በፍ/ቤት የተረጋገጠ፣<br>ሀብቱንና ንብረቱን የሚያስተዳድርለት ወይም የሚጠብቅለት ባለአደራ የተመደበለት፣ ወይም<br>በአጠቃላይ ዕዳውን መክፈል ያቃተው፣ ማለት ነው |
| ሐ. ውል መፈፀም (ማሰር) | በማዕቀፍ ስምምነቱ ውስጥ በተገለፁት ሁኔታዎችና ድንጋጌዎች፣ እንዲሁም ተጨማሪ ማሻሻያዎች መሰረት የቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ለማከናወን የማዕቀፍ ስምምነት በሚፈጽመው፣ በግዥ ፈጻሚው መ/ቤትና በአቅራቢው መካከል የሚደረግ ውል ማለት ነው። ውል የሚፈጸመው የተናጠል ውል በሚገበባው መ/ቤት የግዥ ትዕዛዝ በመስጠት ሲሆን የግዥ ትዕዛዙ የውሉ አካል ሆኖ ሁለቱንም ተዋዋይ ወገኖች የሚገዛ ይሆናል። |
| መ. ማጠናቀቅ | ማለት በውሉ ውስጥ በተጠቀሱት ቃሎችና ሁኔታዎች መሠረት አቅራቢው ውሉን መፈፀሙን የሚገልፅ ነው። |

| | |
|---|---|
| ሠ. የግልግል ዳኝነት | በአንቀጽ 26 ላይ የተገለፀው የግጭት አፈታት ሂደት ማለት ነው። አለመግባባቱ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ካልተፈታ በስተቀር በውል አፈጻጸም ወቅት ያጋጠማቸውን አለመግባባት ለመፍታት አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን ሊጠቀሙ ይችላሉ። አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን ለመጠቀም የወሰኑ ከሆነ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት በተቋቋሙ እና በተገቢው አካል ዕውቅና በተሰጣቸው የግልግል ዳኝነት አካላት በኩል መሆን አለበት። |
| ረ. የውል ሰነዶች | ማለት በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች የተዘረዘሩትን ሰነዶች ማለት ሲሆን ሁሉንም አባሪዎች፣ ተጨማሪ መግለጫዎች፣ እንዲሁም በዚሁ ውስጥ በማጣቀሻነት የተካተቱትን ሁሉንም ሰነዶች እና ማንኛቸውም የእነዚሁ መሻሻያዎችን ይጨምራል። |
| ሰ. የውል ሥራ መሪ | ማለት ይህንን ውል ለማስፈፀም በአቅራቢው ኃላፊነት የተሰጠውና አቅራቢውን የሚወክል ሲሆን የግዥ ፈፃሚው አካል በፅሑፍ በሲስተም እንዲያውቀው የተደረገ ሰው ማለት ነው። |
| ሸ. የውል ዋጋ | ማለት በዚህ ውል መሠረት የግዥ ፈፃሚው አካል ለአቅራቢው የሚከፍለው ገንዘብ ማለት ሲሆን የስምና የፈቃድ ክፍያዎች፣ እንዲሁም የአእምሯዊ የባለቤትነት መብትና የመሳሰሉትን ወጪዎች ይጨምራል። |
| ቀ. የማዕቀፍ ስምምነት | ማለት የማዕቀፍ ግዥ በሚፈጽመው መ/ቤት እና በጨረታ ተወዳድረው አሸናፊ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር የዕቃዎችና አገልግሎቶችን ግዥ ለመፈጸም የሚገቢት ውል ሲሆን የውል ሰነዶችን፣ አባሪዎችንና በማጣቀሻነት የቀረቡ ሰነዶችን ይጨምራል። |
| በ የተናጠል ውል | ማለት የመንግስት መ/ቤቶች ከተፈረመው የማዕቀፍ ስምምት በመነሳት በስምምነቱ ላይ የተገለጹትን አቅርቦቶች ለመግዛት ከአቅራቢው ጋር የሚገቡት ውል ሲሆን፣ የውል ሰነዶችን፣ አባሪዎችንና በማጣቀሻነት የቀረቡ ሰነዶችን ይጨምራል። |
| ቡ. ተዋዋይ ባለስልጣን | ማለት በልዩ የውል ሁኔታዎች ላይ በተገለፀው መሰረት የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ግዥን በተመለከተ የማዕቀፍ ስምምነት የመፈፀም ወይም ደግሞ ከማዕቀፍ ስምምነቱ በመነሳት የተናጠል የአቅርቦት ውል ስምምነት ለመፈጸም ስልጣንና ተግባር ያለው ማንኛውም የመንግስት አካል ማለት ነው። |

| | |
|---|---|
| ተ. ቀን | ማለት በተከታታይ ያሉ ቀናት ማለት ነው። |
| ቸ. ርክክብ | ማለት በውሉ ውስጥ በተጠቀሱት ሁኔታዎችና ጊዜያት መሠረት አቅራቢው ዕቃዎችን ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማስተላለፍ ማለት ነው። |
| ኀ. ብቁ ሀገሮች | ማለት በክፍል 5 በተዘረዘረው መሠረት ብቁ ሀገሮችና ግዛቶች ማለት በማዕቀፍ ለሚፈጸሙ ግዥዎች የሚቀርበው ዕቃ መነሻ ሀገር ማለት ነው። |
| ነ. ማዕቀፍ ስምምነት | ማለት ከአቅራቢ ጋር የሚደረግ ስምምነት ሲሆን ተዋዋዩን ባለስልጣን ወይም ገዢ ተቋማትን በማዕቀፍ ስምምነቱ (ማለትም አንድ የመንግስት አካል የተወሰነ ነገር ለመግዛት በሚፈልግበት ወቅት ከዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ካታሎጎች ላይ የግዢ ትእዛዝ የሚያቀርቡበትን የአሰራር ስርአት ያሳያል) ላይ በተገለፁት ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች መሰረት በስምምነቱ የቆይታ ጊዜ ውስጥ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶችን እንዲያዙ ያስችላቸዋል። የማዕቀፍ ስምምነቱ በቀጣይ ለሚፈፀሙ ውሎች፤ ድንጋጌዎችና ሁኔታዎችን የሚያስቀምጥ ቢሆንም ወደፊት ለሚሰጡ ግዢዎች በተዋዋዩ ባለስልጣን ወይም ገዢው ተቋም ላይ ምንም አይነት ግዴታዎች አይጥልም። ተዋዋዩን ባለስልጣን ወይም ማንኛውንም ገዢ ተቋም የትኛውንም ዝቅተኛ ቁጥር ወይም የግዢ ትዕዛዞች ዋጋ እንዲሰጥ አይጠይቅም ወይም አያስገድድም። እንዲሁም በማዕቀፍ ስምምነቱ ስር ለማንኛውም ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ የወጪ መጠን ዋስትና አይሰጥም። በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት ስር አስገዳጅ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ የሌለ ከመሆኑም በተጨማሪ አቅራቢው በቀጥታ ምንም አይነት የክፍያ ጥያቄ አያቀርብም። የአቅራቢውን ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች ለማግኘት የግዢ ትዕዛዞች የመስጠት ስልጣን ሙሉ በሙሉ የተዋዋዩ ባለስልጣን ወይም ገዢ ተቋማት ሲሆን በዚህ ስምምነት በመጠቀማቸው ለተመሳሳይ ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች አቅርቦት ሌሎች አቅራቢዎችን ከመጠቀም አያግዳቸውም። |
| ኘ. አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች | ማለት በዚሁ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች እንደተጠቀሰው በልዩ የውል ሁኔታዎች ወይም በውል ስምምነቱ ካልተሻረ በስተቀር |

| | |
|---|---|
| | በዚህ የውል ክፍል በተገለጸው መሠረት ውሉን የሚገዛ ሰነድ ማለት ነው። |
| አ. መልካም የኢንዱስትሪ ልምድ | ማለት በውሉ ውስጥ በተካተቱት ሁኔታዎች፣ እንዲሁም አግባብነት ባላቸው በንግድ ማህበራት በታተሙ የንግድ ህጎች መሰረት በዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች አቅርቦት ጊዜ ከአቅራቢው የሚጠበቅ የክህሎት ደረጃ፣ ጥንቃቄና አርቆ አስተዋይነት ማለት ነው። |
| ከ. ዕቃዎች | ማለት በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሳሪያ፣ ሸቀጥ፣ ለገበያ የተዘጋጀ ሶፍትዌር እና እንስሳ ነው፤ |
| ወ. አገልግሎቶች | ማለት ከግንባታ ዘርፍ ሥራ እና ከምክር አገልግሎት ውጪ የሆነ ማንኛውም አገልግሎት ሲሆን፣ የኪራይ፣ የትራንስፖርት፣ የህትመት፣ የጥገና፣ የጥበቃ፣ የጽዳት፣ የኃይል አቅርቦት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የውሃ አቅርቦት እና የመሳሰሉት አገልግሎቶችን |
| ወ. መንግሥት | ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ማለት ነው። |
| ዐ. በፅሑፍ | ማለት ማንኛውም በመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥዓት አማካኝነት የተላለፈ ወይም በእጅ ወይም በታይፕ የተፃፈ ሰነድን ይጨምራል። |
| ዘ. የታወቁ ጉዳቶች | ማለት አቅራቢው በውሉ መሰረት ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በሙሉ ወይም በከፊል በውሉ ማቅረቢያ ጊዜ ለግዥ ፈፃሚው አካል ማቅረብ ሲያቅተው ወይም አንደኛው ተዋዋይ ወገን በውሉ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ውሉን ሲያፈርስ የሚከፈል ካሳ ማለት ነው። |
| ዠ. ቦታ | ማለት በዚህ ውል ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት የግዥ ፈፃሚው መ/ቤትና አቅራቢው የተስማሙበት ዕቃዎችንና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚቀርብበት ቦታ ማለት ነው። |
| የ. ወር | ማለት በተከታታይ ያሉ ወሮች ማለት ነው |
| ደ. የዋጋ ጣሪያ | ማለት ለአቅራቢው የሚከፈለው ከፍተኛ የዋጋ መጠን ማለት ነው። |
| ጀ. ወገን | ማለት የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወይም አቅራቢው ሲሆን "ወገኖች" ማለት ሁለቱንም (ወራሾቻቸውን ይጨምራል) ማለት |

| | |
|---|---|
| | ነው። |
| ገ. የዋጋ ማስተካከያ | ማለት በውሉ የቆይታ ጊዜ ውስጥ ሊፈጠር ከሚችል የዋጋ መለዋወጥ ጋር በተያያዘ በተዋዋዩ ባለስልጣን እና በአቅራቢው መካከል የሚደረግ የዋጋ ለውጥን መጋራት ማለት ነው። |
| ጠ. የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት | ማለት በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት መሰረት ለአቅራቢው የግዢ ትእዛዝ የሚሰጥና ውል የሚፈፅም የመንግስት መ/ቤት ወይም ሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ነው። |
| ጨ.የመንግስት አካል | ማለት በፌደራል መንግስት በጀት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚጠቀሙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው የመንግስት ተቋማትን ጨምሮ በተቋቋሙበት ህግ የመንግስት መ/ቤት የሚባሉ ማለት ሲሆን በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት ላይ በተገለፀው መሰረት ለአቅራቢው የግዢ ትእዛዝ በመስጠትና ከአቅራቢው ጋር ውል በመፈፀም ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶችን የሚገዙ ማንኛውም የመንግስት አካላት ማለት ነው። |
| ጰ. የግዥ ትዕዛዝ | ማለት የውሉን ቃሎችና ሁኔታዎች፣ እንዲሁም ውሉ ውስጥ ያለውን ዋጋ መሰረት በማድረግ በግዥ ፈጻሚው መ/ቤቶች ለአቅራቢው የሚሰጥ የዕቃዎችና አገልግሎቶች አቅርቦት ትዕዛዝ ነው። እያንዳንዱ የግዥ ትዕዛዝ ግዴታ ውስጥ የሚያስገባ የውል መሳሪያ ሲሆን የሚዘጋጀውም የውሉን ቃሎችና ሁኔታዎች ባገናዘበ መልክ ሆኖ የአቅርቦት ዝርዝር፣ የርክክብ ጊዜና ቦታ፣ እንዲሁም ዋጋ አካቶ የያዘ ማለት ነው። |
| ጸ.ተያያዥ አገልግሎቶች | ማለት በውሉ መሠረት የአቅራቢዎች ግዴታዎች የሆኑ እንደ መድን ዋስትና፣ ተከላ፣ ሥልጠና፣ የመጀመሪያ ጥገናና ተመሳሳይ በውሉ ምክንያት የሚከተሉ ሌሎች አገልግሎቶች ማለት ነው። |
| ፀ. ልዩ የውል ሁኔታዎች | ከስምምነቱ ጋር የተያያዙ የውል ሁኔታዎች ሲሆኑ ይኸውም ውሉን የሚከተሉና በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ የበላይነት ያላቸው ማለት ነው። |
| ፈ. ንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢ | ማለት ከአቅራቢው ጋር ዕቃዎችን ወይም ተያያዥ አገልግሎቶችን ለማቅረብ/ማከናወን የተዋዋለ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው፣ የግል ወይም የመንግሥት ድርጅት ወይም የነዚሁ ወካይና ወራሾቻቸውን ጨምሮ ማለት ነው። |

| | |
|---|---|
| ፐ. የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢ | ማለት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጋር የተዋዋለ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው፣ የግል ወይም የመንግሥት ድርጅት ወይም የእነዚህ ህብረት ማለት ነው። |
| ሀሀ. የቆይታ ጊዜ | ማለት ስምምነቱ ተፈፃሚ ከሚሆንበት ቀን ጀምሮ የዚህ የስምምነቱ የመጀመሪያው የማብቂያ ጊዜ ወይም ማንኛውም የማራዘሚያ ጊዜ ካለ የሚያበቃበት ወይም ቀደም ብሎ ስምምነቱ የሚያበቃበት ቀን ማለት ነው። |
| ለለ. ሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ | በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 ስር የተገለፁ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ክልሎችን ማለት ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ያጠቃልላል። |

**2.** *ኃላፊነት ስለመስጠት*

2.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አቅራቢውን ዕቃዎችና አገልግሎቶችን እንዲያቀርብ ኃላፊነት ሰጥቶታል::

(ሀ) አቅራቢው በውሉ አፈጻጸም በማንኛውም ወቅት ሙያዊና ትህትና በተሞላበት ሁኔታ የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ምስል ማሳየትና ማስተዋወቅ አለበት።

(ለ) አቅራቢው የውሉ ሁኔታዎችና የፍላጎት መግለጫዎችን በጥንቃቄና በትክክል ይፈጽማል።

(ሐ) አቅራቢው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የወጡትን ህጎችና ደንቦች እንዲሁም መልካም የኢንዱስትሪ ተግባር የሚፈቅደውን ሁሉ ይፈጽማል።

(መ) አቅራቢው በየጊዜው በሚመለከተው ባለስልጣን እየተሻሻሉ የሚወጡትን ፖሊሲዎች፣ ህጎችና ስነስርአቶች ያከብራል።

(ሠ) አቅራቢው በአለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን የሚወጡትን የጥራት ደረጃዎች ያከብራል።

(ረ) አቅራቢው በውሉ ዋጋና በዚሁ አንቀጽ የተጠቀሱትን የህላፊነት አሰጣጥ ቃሎችና ሁኔታዎች ያከብራል።

**3.** *የተዋዋይ ወገኖች ግንኙነት*

3.1 አቅራቢው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤቱ ስም ምንም ዓይነት ውል ወይም ግዴታ ሊገባ አይችልም ወይም ምንም ዓይነት ዕዳ ውስጥ መግባት አይችልም።

3.2 አቅራቢው ይህን ውል በሚፈጽምበት ጊዜ ራሱን የቻለ አካል ነው። በዚህ ውል ምክንያት ኤጀንሲ፣ አጋርነት፣ የጋራ ማህበር ወይም ሌላ በሁለቱም ወገኖች የጋራ የሆነ ግንኙነት አይመሰረትም።

3.3 በውሉ ሁኔታዎች መሠረት አቅራቢው ውሉን በማስፈፀም ረገድ ብቸኛው ኃላፊ ነው። ውሉን በማስፈፀም ተግባር የተሰማሩ ሁሉም ሠራተኞች፣ ተወካዮች ወይም ንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢዎች የሚሰሩት በአቅራቢው ቁጥጥር ሥር ሆነው ሲሆን የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሠራተኞች አይደሉም። ለአቅራቢው ውል በመስጠቱ ምክንያት እነዚህ ሠራተኞች፣ ተወካዮችና ንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢዎች ከግዥ ፈፃሚው አካል ጋር የውል ግንኙት የላቸውም።

## 4. ልዩ ጥንቃቄ

4.1 አቅራቢው ሊገነዘባቸው የሚገቡ ጉዳዮች፤

(ሀ) በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወይም ተወካይ የሚሰጠውን መረጃ ትክክለኛነት በተመለከተ ራሱን ለመጠበቅ ተገቢ የሆነ ማጣራት ማከናወን ይገባዋል።

(ለ) ውሉ ተግባራዊ ከሚሆንበት ቀን በፊት ሁሉንም ተገቢነት ያላቸው ጥያቄዎች ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማቅረቡን ማረጋገጥ አለበት።

(ሐ) ውሉ ውስጥ የገባው ራሱ ባደረጋቸው ተገቢ የሆኑ ጥንቃቄዎች በመተማመን ብቻ መሆን አለበት።

4.2 ከተገቢ ጥንቃቄ ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶች በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የሚፈቱ ይሆናል።

## 5. ማጭበርበርና ሙስና

5.1 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ፖሊሲ የግዥ ፈጻሚ አካላት፤ ተጫራቾችና አቅራቢዎች በግዥ ሂደትና በውል አፈጻጸም ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የግዥ ስነምግባር እንዲከተሉ የሚጠይቅ ነው። በዚሁ ፖሊሲ መሰረት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን (ከሁን በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራው) የሚወከል ሲሆን የግዥ ፈፃሚ አካላት የማጭበርበርና የሙስና ድርጊት እንዳይፈፀም የሚከለክል አሠራር በጨረታ ሰነዶቻቸው ውስጥ እንዲያካትቱ ይፈልጋል።

5.2 ለዚሁ የጨረታ ሰነድ ሲባል ባለሥልጣኑ ለሚከተሉት ቃላት ቀጥሎ የተመለከተውን ፍች ይሰጣል።

(ሀ) “የሙስና ድርጊት” ማለት የአንድን በመንግሥት የግዥ አፈጻጸም ሂደት ወይም በውል አፈጻጸም ወቅት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተሳታፊ የሆነን የመ/ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም የግዥ ክፍል የሥራ ኃላፊ ወይም የግዥ አጽዳቂና ጊዜያዊ ገምጋሚ ኮሚቴ አባላት ወይም የግዥ ባለሙያ ባለሥልጣን በግዥ ሂደት ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለማባበል (ለማግለል) በማሰብ ማንኛውም ዋጋ ያለው ነገር መስጠት፣ ወይንም ለመስጠት ማግባባት ማለት ነው።

(ለ) “የማጭበርበር ድርጊት” ማለት ያልተገባን የገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ግዴታን ላለመወጣት በማሰብ የግዥ ሂደቱንና የውል አፈፃፀሙን በሚጐዳ መልኩ ሀቁን በመለወጥና አዛብቶ በማቅረብ ሆን ተብሎ የሚፈፀም ድርጊት ነው።

(ሐ) “የመመሳጠር ድርጊት” ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ተጫራቾች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እያወቀም ሆነ ሳያውቀው በመመሳጠር ውድድር አልባና ተገቢ ያልሆነ ዋጋን መፍጠር ማለት ነው።

(መ) “የማስገደድ ድርጊት” ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሰዎችን አካልና ንብረት በመጉዳትና ለመጉዳት በማስፈራራት በግዥ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ወይም የውል አፈፃፀም ማዛባት ማለት ነው።

(ሠ) “የመግታት (የማደናቀፍ) ድርጊት” ማለት፣

በፌዴራል ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፤ በፌዴራል ኦዲተር ጀነራልና በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ወይም በኦዲተሮች የሚፈለጉ መረጃዎችን ሆን ብሎ ማጥፋት፣ ወይም ጉዳዩ የሚያውቁ አካላት ይፋ እንዳያደርጉ በማስፈራራትና ጉዳት በማድረስ መረጃዎችን እንዳይታወቁ በማድረግ፤ የምርመራ ሂደቶችን መግታት ወይም ማደናቀፍ ማለት ነው።

በዚሁ የተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 46.2 የተመለከቱትን የቁጥጥርና የኦዲት ሥራዎች ማደናቀፍ ከመግታት ድርጊት ጋር አብሮ የሚታይ ይሆናል።

5.3 ተጫራቾች በማንኛውም በውድድሩ ጊዜ ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በሙስና፣ በማጭበርበር፣ በመመሳጠር፣ በማስገደድና በማደናቀፍ ተግባር ተካፋይ መሆናቸው ከተረጋገጠ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ የጊዜ ገደብ በመንግሥት ግዥ ተካፋይ እንዳይሆኑ ይታገዳሉ። የስም ዝርዝራቸውም በመንግስት የኤልክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ፖርታል ላይ ወይም በባለሥልጣን መ/ቤቱ ድረ-ገጽ (ዌብሳይት) http://www.ppa.gov.et ላይ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል።

5.4 በብሔራዊም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ በማጭበርበርና በሙስና ድርጊት ላይ የተሰማሩ አቅራቢዎች በመንግስት በጀት የሚከናወኑ ውሎችን ለመፈጸም ብቁ አለመሆናቸውን የማሳወቅ መብት የባለሥልጣኑ ነው።

5.5 ከውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የአቅራቢዎች ሂሳቦችና ሰነዶች ባለሥልጣኑ በሚመድባቸው ኦዲተሮች እንዲመረመሩና ኦዲት እንዲደረጉ ባለሥልጣኑ የመጠየቅ መብት አለው።

5.6 ማንኛውም ከማጭበርበርና ከሙስና ጋር በተያያዘ በአቅራቢውና በግዥ ፈጻሚው አካል ወይም ከባለሥልጣኑ ጋር የሚደረገው ግንኙነት በጽሁፍ መሆን አለበት።

**6.** ትርጓሜ

6.1 በነጠላ ወይም በብዙ የተገለፁ ቃላቶች እንደፅሑፉ ይዘት ይተረጐማል።
6.2 በእነዚህ ቃሎችና ሁኔታዎች ስለተወሰነ በወንድ ፆታ የተገለጸው ለሴት ጻታም ያገለግላል።
6.3 አለም አቀፍ የንግድ ስም (ኢንኮተርም)

(ሀ) በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር የማንኛቸውም ተዋዋይ ወገኖች የንግድ ሁኔታ፣ መብቶችና ግዴታዎቻቸው በአለም አቀፍ የንግድ ስም (ኢንኮተርም) ውስጥ በተገለፀበት ሁኔታ ይሆናል።

(ለ) ዲ.ዲ.፲ (DDP) ፣ ኢ.ኤክስ.ደብሊው (EWX) እና ሌሎች ተመሳሳይ የንግድ ቃሎች ዓለም አቀፍ ንግድ ምክር ቤት ባሳተመው የኢንኮተርም አዲስ እትም ውስጥ በተጠቀሱት ደንቦች ይገዛል።

6.4 ሙሉ ስምምነት

ውሉ በግዥ ፈፃሚው አካልና በአቅራቢው ሙሉ ስምምነት የተቋቋመ ሲሆን ከዚህ በፊት በተዋዋዮቹ ወገኖች መካከል የነበሩት ሁሉም ግንኙነቶች፣ ድርድሮችና ስምምነቶች በዚህ ውል ይተካሉ።

6.5 ማሻሻያ

ማንኛውም በመንግስት የኤልክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ያላለፈ፣ በፅሑፍ ያልተደረገ፣ ቀን ያልተፃፈበት፣ በግልጽ ውሉን የማይጠቅስና ሥልጣን ባላቸው ተዋዋይ ወኪሎች ያልተፈረመ ማሻሻያ ወይም ለውጥ ተቀባይነት የለውም።

6.6 የተተወ ሆኖ ያለመቆጠር

(ሀ) ማንኛውም መዘግየት፣ መታቀብ፣ መላላት በማንኛውም ወገን የሚደረግ ፍላጎት ማርካት የውሉን ቃሎችና ሁኔታዎች በማስከበር ሂደት ወይም ያንዱ ወገን ለሌላው ጊዜ መስጠት፣ ማላላት፣ መታቀብ፣ መዘግየት ከዚህ በታች በተጠቀሰው አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 6.6 (ለ) መሠረት የሌላውን ተዋዋይ መብት ሊያሳጣበት፣ ሊጐዳው ወይም ሊለውጠው ስለሚችል አንዱ የጣሰውን የውል ግዴታ ሌላው ቸል በማለቱ ብቻ ቀጣይ ውል ማፍረስን እንደተቀበለ አያስቆጥርም።

(ለ) በውሉ ውስጥ የተጠቀሱት የተዋዋይ መብቶች፣ ሥልጣኖች ወይም መፍትሔዎች አለመስጠት ቀን በተፃፈበት ፅሑፍና በሕጉ አግባብ ስልጣን በተሰጠው የሚፈፀም ሆኖ እንዲቀር የተደረገው መብት በግልጽ መጥቀስና የመቅረት ደረጃውንም በመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን በመጠቀም መግለጽ ያስፈልጋል።

6.7 ተከፋፋይነት

ማንኛውንም የውሉን ድንጋጌ ወይም ሁኔታ መከልከል ወይም ዋጋ ማጣት ወይም ያለመከበር የሌላውን ባለ ዋጋነት ወይም መከበር ወይም መፈፀምን አያስቀርም።

**ለ. ውል**

**7. *የውል ሰነዶች***

7.1 በውሉ ውስጥ በተካተቱት ሰነዶች መካከል ግጭት ቢኖር ከዚህ በታች በተመለከተው ቅደም ተከተል መሠረት ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

(ሀ) ስምምነት
(ለ) ልዩ የውል ሁኔታዎች
(ሐ) አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች
(መ) የጨረታ መስረከቢያ ሠንጠረዥና አባሪዎች
(ሠ) ተቀባይነት ያገኙ ዕቃዎችና የእያንዳንዱ ነጠላ ዋጋ
(ረ) የዋጋ ዝርዝር
(ሰ) የተጫራቹ የአግባብነት መግለጫ ሰርቲፊኬትና አባሪዎች
(ሸ) የቴክኒክ ዝርዝር፣ የመወዳደሪያ ሀሳብ፣ የአግባብነት መግለጫ ሠንጠረዥና አባሪዎች
(ቀ) የውሉ አካል የሆነና ሌላ በልዩ የውሉ ሁኔታዎች ውስጥ የተጠቀሰ ማንኛወም ሰነድ

7.2 ውሉን የሚመሠርቱ ሰነዶች የተያያዙ፣ የሚደጋገፉና ገላጭ እንዲሆኑ የታቀዱ ናቸው።

7.3 ማንኛውም በውሉ መሠረት በግዥ ፈፃሚው አካል ወይም በአቅራቢው እንዲሟላ የሚጠየቅ ወይም የተፈቀደ የውል አፈፃፀም ተግባር እንዲሁም ማንኛውም ተፈፃሚ እንዲሆን የሚጠየቅ ወይም የሚፈቅድ- ሰነድ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ ሥልጣን በተሰጠው ሰው ትዕዛዝ የተሰጠበት ሲሆን ብቻ ነው።

7.4 ይህ ውል በግዥ ፈፃሚ አካልና በአቅራቢው መካከል የተደረገውን ስምምነት ሙሉ በሙሉ የሚይዝ ነው። ስለሆነም ውሉ ከመፈረሙ በፊት በተዋዋዮቹ መካከል ከተደረጉት ማናቸውም ግንኙነቶች፣ ድርድሮችና ስምምነቶች (በቃል ወይም በፅሑፍ ተደርጎ ቢሆንም) የበላይነት ይኖረዋል። የየትኛውም ተዋዋይ ወገን ወኪል በዚህ ውል ከተመለከተው ውጪ መግለጫ የመስጠት፣ ማረጋገጫ የመስጠት ወይም ቃል ኪዳን የመግባት ወይም በዚህ ውል ያልተጠቀሱትን ስምምነቶች የማድረግ ሥልጣን የለውም። የዚህ ዓይነቱ ተግባር ተፈፅሞ ቢገኝ ተዋዋዮቹ አይገደዱበትም ወይም ባለዕዳ አይሆኑም።

7.5 ውሉ ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ ለተጠቀሰው ጊዜ የሚያገለግል ይሆናል።

**8.** *ውሉን የሚገዛ ሕግ*

8.1 ውሉ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሕጎች መሠረት የሚገዛና የሚተረጎም ይሆናል።

**9.** *የጨረታ ቋንቋ*

9.1 በአቅራቢውና በግዥ ፈፃሚው አካል የተቋቋመው ውልም ሆነ በተዋዋዮቹ መካከል የተደረጉት ሁሉም ተያያዥ መፃፃፎችና ሰነዶች በልዩ የውል ሁኔታዎች በተጠቀሰው ቋንቋ ይጻፋሉ። ደጋፊ ሰነዶችና ሌሎች የውሉ አካል የሆኑ የታተሙ ፅሑፎች በሌላ ቋንቋ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በሌላ ቋንቋ የተፃፉ ሰነዶች በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በተጠቀሰው ቋንቋ በትክክለኛ መንገድ ተተርጉመው መቅረብ ይኖርባቸዋል። ለዚህ ውል ሲባል ተተርጉመው የቀረቡ ሰነዶች የበላይነት ይኖራቸዋል።

9.2 ወደ ገዥው ቋንቋ የሚደረገውን የትርጉም ወጪ እና ለትርጉሙ ትክክለኛ አለመሆን ተያይዞ ሊከሰት የሚችለውን የጉዳት ኃላፊነት አቅራቢው ይወስዳል።

**10.** *ማስታወቂያዎችና ግንኙነቶች*

10.1 በማንኛውም በውሉ መሠረት በአንዱ ተዋዋይ ለሌላው የሚሰጠው ማስታወቂያ በውሉ በተጠቀሰው መሠረት የመንግስት የኤልክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን በመጠቀም መሆን አለበት፡፡

10.2 አንድ ማስታወቂያ ውጤት ሊኖረው የሚችለው ማስታወቂያው በሲተሙ ተልኮ ለተዋዋዩ ሕጋዊ ተወካይ ሲደርስ ነው፡፡

10.3

**11.** *ስልጣን ያለው ሀላፊ* **(***ተወካይ ባለስልጣን***)**

11.1 በማንኛውም ባለሥልጣን የተሰጠ ወይም የተደረገ ማስታወቂያ፣ መረጃ ወይም ግንኙነት በግዥ ፈፃሚው አካል የተደረገ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

11.2 አቅራቢው የሚያቀርባቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላልተፈቀደላቸው የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሠራተኞች ማስረከብ የለበትም፡፡

**12.** *የሶስተኛ ወገን መብቶች*

12.1 ተዋዋዩ የማዕቀፍ ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት እና አቅራቢው ውል የፈፀሙት ለእያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤትና የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚዎች ጥቅም እንደሆነ ያረጋግጣሉ፡፡ በመሆኑም ተዋዋዩ ባለስልጣን እና አቅራቢው (ተዋዋዩ ባለስልጣን ውሉን የማስፈጸም ስልጣን ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ) እያንዳንዱ የመንግስት የመ/ቤትአካል እና እያንዳንዱ የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚዎች የስምምነቱን ማንኛውንም ድንጋጌ ተፈፃሚ ማድረግ እንደሚችሉ ተስማምተዋል፡፡

12.2 በዚህ ውል ንዑስ አንቀጽ 12.1 ላይ ከቀረበው በስተቀር የውሉ አካል ያልሆነ ማንኛውም ሰው የስምምነቱን ማንኛውንም ድንጋጌ ተፈፃሚ የማድረግ ምንም አይነት መብት የለውም፡፡

12.3 የውሉን ሁሉንም ወይም ማንኛውንም ድንጋጌዎች ሁለቱም ወገኖች ባላቸው ስልጣን መሰረት የውሉ አካል ያልሆነ ሰው ፈቃድ ሳይጠይቁ ወይም ምንም አይነት ማስታወቂያ ሳይሰጡ ሊያሻሽሉ ወይም ሊቀይሩ ይችላሉ፡፡

## 13. *የሶስተኛ ወገን ተጠቀሚዎች*

13.1 ማንኛውም ሶስተኛ ወገን በንዑስ አንቀጽ 12.1 መሰረት ያሉትን መብቶች ተፈፃሚ ለማድረግ ሲፈልግ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በመከተል ይፈፅማል።

(ሀ) በውሉ መሰረት የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚዎች ከመንግስት አካላት ጋር አንድ አይነት መብቶች ያሏቸው በመሆኑ በመንግስት አካላት ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ ሁሉንም ድንጋጌዎች ማክበር አለባቸው።

(ለ) የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚዎች ውሉ ለተዋዋዩ ባለስልጣን ጥቅም የተፈፀመ መሆኑን ያረጋግጣሉ። በመሆኑም በዚህ ውል ስር ያሏቸውን መብቶች የሚጠቀሙት ለተዋዋዩ ባለስልጣን ወይም ለማንኛውም የመንግስት አካላት ከሚቀርቡት እቃዎች እና/ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ብቻ እንደሆነና ለሌላ አላማ እንዳልሆነ ተስማምተዋል። የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚዎች በዚህ ውል የተሰጧቸውን መብቶች በሚጠቀሙበት ጊዜ በየትኛውም ጊዜ ውሉን የተመለከቱ ሁሉንም መረጃዎች በከፍተኛ ሚስጥራዊነት እና በአንቀጽ 28 መሰረት መያዝ አለባቸው።

(ሐ) የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚዎች በተዋዋዩ ባለስልጣን ወይም በማንኛውም የመንግስት አካል ስም ማንኛውንም ግዴታዎች መግባት የለባቸውም። እንዲሁም በተዋዋዩ ባለስልጣን ወይም በማንኛውም የመንግስት አካል ስም የትኛውንም ውክልና ማድረግ ወይም ማንኛውንም ዋስትናዎች መስጠት የለባቸውም።

(መ) ዕቃዎቹ የሚታዘዙት በሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ከሆነ አቅራቢው እነዚህን እቃዎች የሚያቀርበው ለሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ይሆናል። በመሆኑም የሚቀርቡት ደረሰኞች የሚሰጡት ለዚሁ የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ሲሆን፣ ደረሰኞቹ በሚዘጋጁት በዚህ ሶስተኛ ወገን ስም ነው። የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚው ክፍያውን የመፈፀም ኃላፊነት አለበት።

(ሠ) ተዋዋዩ ባለስልጣን በአቅራቢው ለሚደረጉ ማንኛውም የጉድለት ድርጊቶች ወይም ኪሳራዎች፣ ወይም የሶስተኛው ወገን በዚህ ውል የተሰጡትን መብቶች በሚጠቀምበት ወቅት በሌላ ሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ወይም ወጪዎች ምንም አይነት ሀላፊነት የለበትም።

(ረ) እያንዳንዱ የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ከታች በተመለከቱት ምክንያቶች በተዋዋዩ ባለስልጣን ወይም ማንኛውም የመንግስት አካል ላይ ለሚከሰቱ ወጪዎች፣ ጥያቄዎች፣ ፍላጎቶች፣ ተጠያቂነቶች፣ ጉዳቶች፣ ኪሳራዎች እና ወጪዎች (ሁሉንም የህግ ወጪዎች ጨምሮ) ለእነዚህ ወገኖች ካሳ ይከፍላል።

(ሰ) በሶስተኛ ወገን ማንኛውም ድርጊት (ተግባር) ወይም የድርጊት አለመፈፀም ጋር በተያያዘ ወይም በሶስተኛ ወገን ተጠቃሚው የዚህ ውል የትኛውም ድንጋጌ መጣስ ምክንያት ለሚደርሱ፣

(ሸ) የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚው በዚህ ውል የተሰጡትን መብቶች ሆን ብሎ በቸልተኝነት፣ በማጭበርበር፣ እምነት በማጣት ወይም በሌላ ምክንያት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ያለማስፈፀም ድርጊት ጋር በተያያዘ በአቅራቢው ወይም በሌላ የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚው ላይ ማንኛውም አይነት ጥያቄ፣ ኪሳራ፣ አደጋ፣ ጉዳት፣ ወጪ ወይም መዘግየት የሚደርስ ከሆነ።

(ቀ) የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚው ከነዚህ ተጠያቂነቶች ጋር በተያያዘ በራሱ ወጪ በቂ ኢንሹራንስ ገብቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት። እንደዚሁም ተዋዋዩ ባለስልጣን በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት የነዚህን ኢንሹራንስ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

(በ) አቅራቢው በማንኛውም የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ድርጊት ወይም የድርጊት ጉድለት ወይም በዚህ የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ማንኛውም የውሉ ጥሰት ምክንያት በማንኛውም የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ላይ ጥያቄ የሚያቀርብ ከሆነ አቅራቢው በዚህ የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ላይ በሚያቀርበው ክስ ላይ ተዋዋይ ባለስልጣኑን ወይም የትኛውንም የመንግስት አካል የማያካትት ስለመሆኑ ተስማምተዋል።

(ተ) ተዋዋይ ባለስልጣኑ የትኛውንም የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ከገዢ ተቋማት ዝርዝር ላይ ሲሰርዝ ለዚህ የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ማስታወቂያ መስጠት ያለበት ሲሆን ይህ የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚ ወዲያውኑ በዚህ ውል ስር የአገልግሎቶች ግዢ ትእዛዝ መስጠት ማቆም አለበት።

## 14. *ኃላፊነትን ለሌላ ስለማስተላለፍ*

14.1 ኃላፊነት ለሌላ ማስተላለፍ ማለት አቅራቢው ውሉን በሙሉ ወይም በከፊል በፅሑፍ ስምምነት ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ ማለት ነው።

14.2 በልዩ የውል ሁኔታ ላይ ካልተፈቀደ በስተቀር አቅራቢው ውሉን ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይችልም።

14.3 በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር አቅራቢው ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት በቅድሚያ በፅሑፍ ሳያሳውቅ ውሉን በሙሉም ሆነ በከፊል ወይም ከውሉ ጋር የተያያዘ ጥቅሞችና ፍላጎቶች ለሦስተኛ ወገን ማስተላለፍ የለበትም።

(ሀ) የአቅራቢው ደንበኛ ባንክ በዚሁ ውል መነሻነት የመክፈል ግዴታ ሲኖርበት፣

(ለ) ለአቅራቢው የመድን ዋስትና የሰጠው አካል ከአቀረበው መብት ጋር በተያያዘ ከዕዳና ከኪሣራ ለመውጣት ሲባል ለሌላ ሰው የወጣውን ወጪ ለመተካት።

14.4 ዕቃዎችን ወደተፈለገው ቦታ ለማጓጓዝ ካልሆነ በስተቀር ዕቃዎቹን የማምረትና የማቅረብ ሥራ በቅድሚያ ግዥ ፈፃሚውን አካል በፅሑፍ ሳያሳውቅና ይሁንታ ሳያገኝ ለንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢዎች መስጠት አይችልም። አቅራቢው የሚያቀርበው የይሁንታ ጥያቄ ያለበቂ ምክንያት በግዥ ፈፃሚው አካል መያዝና መዘግየት የለበትም።

14.5 በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 14.2 ዓላማ መሠረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ኃላፊነትን ለሌላ ለማስተላለፍ ጥያቄ በመቀበሉ ምክንያት አቅራቢው በውል አፈፃፀም ከሚኖረው ግዴታ (በተላለፈውም ሆነ ባልተላለፈው) ነፃ አያደርገውም።

14.6 አቅራቢው ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ፈቃድ ሳያገኝ ኃላፊነቱን ለሌላ ካስተላለፈ ያለምንም የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 20 እና 22 ውስጥ በተለከተው መሠረት የውል መቋረጥ መብቶች ተግባራዊ ያደርጋል።

14.7 ኃላፊነትን ለሌላ ማስተላለፍ በጨረታ አሸናፊ ምርጫ ጊዜ ተግባር ላይ የዋሉትን የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል። ይህም ቢሆን ግን በማንኛውም መንገድ በውል ከመሳተፍ የሚከለከል አይደለም።

14.8 ኃላፊነትን ለሌላ የማስተላለፍ ተግባር በዚህ ውስጥ ያሉትን ቃሎችና ሁኔታዎች ማካተት ይኖርበታል።

**15. *ንዑስ ውል ስምምነት*)**

15.1 ንዑስ ውል ስምምነት ተቀባይነት የሚኖረው በአቅራቢውና በንዑስ ተቋራጩ መካከል ከፊል ውሉን ለማከናወን የፅሑፍ ስምምነት ሲኖር ብቻ ነው።

15.2 አቅራቢው በውሉ ውስጥ ያልተካተቱን አገልግሎቶች ለንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢ ለመስጠት ሲፈልግ በቅድሚያ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፅሑፍ ፈቃድና ይሁንታ ማግኘት አለበት። የንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢው ማንነትና ሊሰጡት የታሰቡት አገልግሎቶች ማስታወቂያ በቅድሚያ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መቅረብ አለባቸው። የግዥ ፈፃሚው አካል በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 1ዐ መሠረት ማስታወቂያው በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ከበቂ ምክንያቶች ጋር ውሳኔውን ያሳውቃል።

15.3 የንዑስ ውል ስምምነት ቃሎች በዚህ ውል ከተመለከቱት ሁኔታዎች ጋር የሚጣጣሙ መሆን ይኖርባቸዋል።

15.4 ውል ሰጪው ወይም የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢው ጋር ምንም ዓይነት የውል ግንኙነት የለውም።

15.5 ንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢዎች በጨረታ አሸናፊ ምርጫ ጊዜ አገልግሎት ላይ የዋሉትን የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል።

15.6 አቅራቢው በንዑስ ውል ስምምነ አቅራቢዎቹ ፣ በወኪሎቹ ወይም በሠራተኞቹ ለሚፈጠሩ ድርጊቶች፣ ስህተቶችና ግድየለሽነቶች የራሱ ስህተቶችናና ግድየለሽነቶች እንደሆኑ በመቁጠር ኃላፊነት መውሰድ አለበት። የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከፊል ውሉ በንዑስ ውል ስምምነት እንዲከናወን በመፍቀዱ ምክንያት አቅራቢውን ከኃላፊነት ነፃ አያደርገውም።

15.7 አቅራቢው ያለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ፈቃድ ከፊል ውሉን ለንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢው ከሰጠ ግዥ ፈፃሚው አካል ያለምንም የፅሑፍ ማስታወቂያ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 20 እና 22 በተመለከተው መሠረት የውል መቋረጥ መብቶች ተግባራዊ ያደርጋል።

15.8 ንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢው ግዴታዎቹን በመወጣት ረገድ ደካማ ሆኖ ከተገኘ የግዥ ፈፃሚው አካል አቅራቢውን ሊተካ የሚችል ብቃት ያለው ሌላ ንዑስ ተቋራጭ እንዲያቀርብ ወይም ሥራውን ራሱ እንደገና እንዲያከናውን ሊጠይቀው ይችላል።

## 16. *የውል ማሻሻያዎችና ለውጦች*

16.1 የግዥ ፈፃሚው አካል በማንኛውም ጊዜ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 10 መሠረት ከአጠቃላይ የውሉ ማዕቀፍ ውስጥ ሳይወጣ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ በሚከተሉት ምክንያቶች በውሉ ላይ ለውጥ ለማድረግ አቅራቢውን ሊጠይቀው ይችላል።

(ሀ) በውሉ መሠረት የሚቀርቡት ዕቃዎች፣ ሥዕሎች፣ ንድፎች ወይም ዝርዝሮች በተለየ ሁኔታ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማምረት ሲያስፈልግ፣

(ለ) የማሸግ ወይም በመርከብ የማጓጓዝ ዘዴን መለወጥ ሲያስፈልግ፣

(ሐ) የማስረከቢያ ቦታውን መለወጥ ሲያስፈልግ፣

(መ) ከአቅራቢው መቅረብ ያለባቸውን ተያያዥ አገልግሎቶች መለወጥ ሲያስፈልግ፣

16.2 እንደዚህ ዓይነት ማንኛውም ለውጥ የአቅራቢውን የውሉን ድንጋጌዎች አፈፃፀም ወይም ጊዜን የሚጨምር ሲሆን በማስረከብ ወይም በአፈፃፀም እቅድ ወይም በሁለቱም ላይ ተመጣጣኝ ማስተካከያ ተደርጎ ውሉም በዚያው መሠረት ይሻሻላል። አቅራቢውም በዚህ አንቀጽ ያለውን

ማንኛውም የማስተካከያ ጥያቄ የግዥ ፈፃሚው የለውጥ ትዕዛዝ ከቀረበለት እለት ጀምሮ በ28 ቀናት ውስጥ ማረጋገጥ አለበት።

16.3 አቅራቢው አስፈላጊ በሆኑ ተያያዥ አገልግሎቶች ላይ ቀደም ሲል በውሉ ሳይካተቱ የታለፉትን ዋጋዎች በተመለከተ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጋር በመደራደር ሁለቱም በቅድሚያ መስማማት አለባቸው።

16.4 ማንኛውም በውሉ ላይ የሚደረጉ ለውጦች በሲስተም ሆኖ በተዋዋይ ወገኖች ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት መፈፀም አለበት። በፅሑፍ የሚደረጉት የውል ለውጦች ቀጣይ ማሻሻያዎችን ሊያካትተ በሚችል መልኩ መከናወን ይኖርባቸዋል።

16.5 በሲስተም የሚደረጉት የውል ለውጦች ተግባራዊ የሚሆኑት በተፈረመው የፅሑፍ ሰነድ ላይ ከሰፈረው ቀን ጀምሮ ይሆናል። በግልፅ ስምምነት ካልደተረገ በስተቀር ወደኋላ ተመልሶ ተግባራዊ አይሆንም።

16.6 እያንዳንዱ የውል ለውጥ የቅደም ተከተል ቁጥር የተሰጠውና ቀን የተፃፈበት መሆን ይኖርበታል።

16.7 በተሻሻለው ውል ላይ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር የውሉ አፈፃፀም በነበረው ሁኔታ ይቀጥላል።

**17.** ***በሕጎችና በደንቦች ላይ የሚደረግ ለውጥ***

17.1 በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልተጠቀሰ በስተቀር የጨረታ ማስረከቢያ ቀን ካለፈ በኋላ ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ ትዕዛዝ ወይም የሕግ አቅም ያለው ውስጠ ደንብ ታትሞ ቢወጣ፣ ቢጣስ ወይም የውሉ ቦታ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ውስጥ ቢሆንና ይህም የማስረከቢያውን ቀን ወይም የውሉ ዋጋ የሚለውጥ ቢሆን የማስረከቢያውን ቀን ወይም የውሉን ዋጋ የመጨመር ወይም የመቀነስ ማስተካከያ አይደረግም። በተመሳሳይ ሁኔታ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀፅ 33 መሰረት የዋጋ ማስተካከያ የተደረገ ከሆነ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ለሚከሰት የዋጋ መጨመር ወይም መቀነስ ማስተካከያ አይደረግም።

**18.** ***ግብሮችና ታክሶች***

18.1 በልዩ የውል ሁኔታዎች በሌላ አኳኋን ከተገለጸው በስተቀር ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውጭ ለሚቀርቡ ዕቃዎች ግብርና ቀረጥ፣ የቴምብር ቀረጥ፣ የንግድ

ፈቃድ ክፍያና ሌሎች ተመሳሳይ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚከፈሉ ክፍያዎች አቅራቢው መክፈል አለበት፡፡

18.2 በልዩ የውል ሁኔታዎች በተለየ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ የሚቀርቡ ዕቃዎችን እርክክብ እስኪፈፀም ድረስ ያለውን ማንኛውም ግብር ቀረጥ፣ የንግድ ፈቃድ ክፍያና የመሳሰሉትን በሙሉ አቅራቢው የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

**19.** ***አስገዳጅ ሁኔታዎች***

19.1 ለዚህ ውል ዓላማ ሲባል አስገዳጅ ሁኔታዎች ማለት ከአቅራቢው አቅም በላይ የሆኑ ያልተጠበቁ፣ ማስወገድ የማይችላቸውና በተፈለገው ሁኔታ ግዴታውን ለመፈፀም የማያስችሉ የሚከተሉት ክስተቶች ሲፈጠሩ ማለት ነው፡፡

(ሀ) ውሉን እንዳይፈፅም የተደረገ በመንግስት የተደረገ ክልከላ፣

(ለ) የተፈጥሮ አደጋዎች ማለትም የመሬት መንቀጥቀጥ፣ እሳት፣ ፍንዳታዎች፣ ጐርፍና ሌሎች ተዛማጅ የአየር ሁኔታዎች፣

(ሐ) ከውጭ አገር ወይም ከጠላት ጋር የሚደረግ ወይም የሀገር ውስጥ የእርስ በእርስ ጦርነቶች፣

(መ) ያልተጠበቀ ወይም በድንገተኛ ሁኔታ የአቅራቢው መሞት ወይም በፅኑ መታመም፣

(ሠ) ሌሎች በፍትሐብሔር ህጉ ከአቅም በላይ ሁኔታዎች ተብለው የተመለከቱ አስገዳጅ ሁኔታዎች፣

19.2 የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲከሰቱ እንደ አስገዳጅ ሁኔታዎች አይቆጠሩም፡፡

(ሀ) የሥራ ማቆም አድማዎች፣

(ለ) ውሉን ከማስፈፀም አንፃር የአቅርቦቶች ዋጋ መቀነስ ወይም መጨመር፣

(ሐ) ተዋዋይ ያለበትን የውል ግዴታ አፈጻጸም የሚያከብድ አዲስ ሕግ መውጣት፣

(መ) በአቅራቢው ወይም በንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢው ወይም በወኪሉ ወይም በሠራተኞቹ ሆን ተብሎ ወይም በግድየለሽነት የሚፈጠሩ ችግሮች፣

(ሠ) አቅራቢው በቅድሚያ ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ እና ተገቢውን ግምት ባለመውሰዱ ለሚፈጠሩ ሁኔታዎች፣ ለምልሳሌ፤ ውሉ ስራ ላይ የሚውልበትን ጊዜ፣

(ረ) ግዴታን በመወጣት ሂደት ሊያስወግዳቸው ወይም ሊቋቋማቸው የሚችሉትን ሁኔታዎች፣

(ሰ) የገንዘብ እጥረት ወይም ክፍያዎችን አለመክፈል፣

19.3 ከአስገዳጅ ሁኔታዎች በመነጨ ምክንያት አቅራቢው የውል ግዴታዎችን ባለመፈፀሙ ምክንያት የውሉን ቃሎችና ሁኔታዎች በሚፈቅደው መሠረት አስፈላጊውን ጥንቃቄና አማራጭ መፍትሔዎች ለመፈለግ ጥረት እስካደረገ ድረስ ውሉን እንዳቋረጠ አይቆጠርበትም፡፡

19.4 በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ጉዳት የደረሰበት አቅራቢ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ አለበት፡፡

(ሀ) በአጭር ጊዜ ውስጥ ግዴታውን ለመፈፀም ያላስቻሉትን ሁኔታዎች ማስወገድ፣
(ለ) በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት የሚመጡ ጉዳቶችን ለመቀነስ ጥረት ማድረግ፣

19.5 በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲከሰት አቅራቢው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በአስቸኳይ ማሳወቅ አለበት፡፡ በማንኛውም መንገድ ከአቅም በላይ የሆነን ሁኔታ ሲከሰት የተከሰተውን ችግርና ምክንያቱን በመግለፅ ቢያንስ በ 14 ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ችግሮቹ ተወግደው መደበኛ ሥራዎች በሚጀመሩበት ጊዜ በአቸስኳይ ማሳወቅ አለበት፡፡

19.6 በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት አቅራቢው ግዴታውን ማከናወን ካልቻለበት ጊዜ ጀምሮ ከ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሁለቱም ወገኖች በመልካም መተማመን የተፈጠሩት ችግሮች ተወግደው የውሉ አፈፃፀም የሚቀጥልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መወያየት/መደራደርና መስማማት ይኖርባቸዋል፡፡

## 20. *ውልን ስለማፍረስ*

20.1 አንደኛው ተዋዋይ በውሉ ውስጥ ከተጠቀሱት ግዴታዎቹ የትኛውንም ያልተወጣ ከሆነ ውል እንዳፈረሰ ይቆጠራል፣

20.2 ውል በሚፈርስበት ጊዜ ውል በመፍረሱ ምክንያት የተጐዳው ወገን የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

(ሀ) በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 27 መሠረት የጉዳት ካሣ መጠየቅ፣
(ለ) ውሉን ማቋረጥ

20.3 ተጐጂው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚሆንበት ወቅት የጉዳት ካሣውን ለአቅራቢው ከሚከፍለው ክፍያ ቀንሶ ያስቀራል፡፡ እንዲሁም የውል ማስከበሪያ ዋስትናውን ይወርሳል፡፡

## 21. ኃላፊነት ለሌላ ማስተላለፍን ስለማገድ

21.1 አቅራቢው በውሉ ውስጥ የተመለከቱትን ግዴታዎች ማከናወን ሳይችል ሲቀር ግዥ ፈፃሚው አካል ከታች የተዘረዘሩትን በመግለፅና የፅሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት በውሉ የተገለፁ ሀላፊነቶች እና ክፍያዎችን እንዲታገዱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

(ሀ) የጉድለቱን ምንነት በመግለጽ፣

(ለ) አቅራቢው ጉድለቶቹን ከ30 ባልበለጡ ቀናት ውስጥ እንዲያርም በማሳወቅ፣

## 22. ውል መቋረጥ

22.1 ተዋዋይ ወገኖች ውል ከፈረሙ ቡኋላ የውሉ ድንጋጌዎቹ በልዩ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 7.6 በተመለከተው የውል ጊዜ ተግባራዊ ካልሆኑ ውሉ ይቋረጠል፡፡

22.2 ውሉ የሚቋረጠው በግዥ ፈጻሚው መ/ቤትና በአቅራቢው በተገባው ውል ውስጥ የተካተቱትን ሌሎች መብቶች ወይም ስልጣኖች በማይጻረር መልኩ መሆን አለበት፡፡

22.3 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች የተመለከቱት ምክንያቶች ሲያጋጥሙ ለአቅራቢው ለውሉ መቋረጥ ምክንያቱንና የውሉ መቋረጥ ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን በመግለፅ ከ30 ቀናት ያላነሰ የፅሑፍ ማስታወቂያ በመስጠትና (በፊደል “ነ” ከዚህ በታች የተጠቀሰው ሁኔታ ሲያጋጥም ከ60 ቀን ያላነሰ የፅሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት) በዚህ ንዑስ አንቀጽ 22.3 ከ(ሀ) እስከ (ኘ) ከተዘረዘሩት አንዱ ሲከሰት ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

(ሀ) አቅራቢው ዕቃዎቹን ወይም አገልግሎቶቹን በውሉ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ሳያቀርብ ሲቀር ወይም በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 63 መሠረት በተራዘመለት ጊዜ ሳያቀርብ ሲቀር ወይም ያቀረባቸው ዕቃዎች የተጠየቀውን የቴክኒክ ዝርዝር/ፍላጐት ያላሟላ ሲሆን፣

(ለ) አቅራቢው በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 21 መሠረት ግዴታዎቹን እንዲወጣ የተሰጠውን የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ/ማስታወቂያ ተከትሎ በ30 ቀናት ውስጥ ጉድለቶችን ለማስተካከል ካልቻለ፥

(ሐ) አቅራቢው ዕዳውን መክፈል ሲያቋርጥ ወይም ሲከስር፣

(መ) አቅራቢው በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 26.2 መሰረት በተደረገ ውይይት በተደረሰበት የመጨረሻ ውሳኔ መሠረት ሳይፈፅም ሲቀር፣

(ሠ) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አቅራቢው ከ60 ቀናት ላላነሰ ጊዜ የአገልግሎቶቹን ዋነኛውን ክፍል መፈፀም የሚያቅተው ሲሆን፣

(ረ) አቅራቢው ያለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ስምምነት ውሉን ወይም ሥራውን ለንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢ ሲያስተላልፍ፣

(ሰ) አቅራቢው በመ/ቤቱ የግዥ ሂደት ከስነ ምግባር ጋር በተያያዘ በህግ ወጥ ተግባር ላይ መሳተፉ በሚመለከታቸው አካላት እና በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሲረጋገጥ፥

(ሸ) አቅራቢው የውል ግዴታዎቹን ባለመፈፀሙ ምክንያት የአቅርቦት ውል የማፍረስ ተግባር መፈፀሙ ሲታወቅ፣

(ቀ) አቅራቢው በጨረታ ውድድር ወቅት ወይም ውሉን በሚያስፈፅምበት ጊዜ በማጭበርበርና በሙስና ድርጊት መሳተፉ ሲታወቅ፣

(በ) በውሉ ማሻሻያ አካል ካልተመዘገበ በስተቀር አቅራቢው ድርጅት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሰውነት ለውጥ ሲያደረግ፣

(ተ) ማናቸውም ውሉን ለማስፈፀም የማያስችሉ ሕጋዊ ሁኔታዎች ሲከሰቱ፣

(ቸ) አቅራቢው ተፈላጊውን ዋስትና ሳያቀርብ ሲቀር ወይም ዋስትና የሰጠው አካል በገባው ቃል መሠረት ቃሉን ሳይጠብቅ ሲቀር፣

(ኀ) የግዥ ፈፃሚው አካል የግዥ ፍላጐት አሳማኝ በሆነ ምክንያት ሲለወጥ፣

(ነ) በውል ዋጋውና ገበያ ላይ ባለው የገበያ ዋጋ ሰፊ ልዩነት በመኖሩ ምክንያት የግዥ ፈፃሚውን አካል ጥቅሞች የሚጐዳ ሆኖ ሲገኝ፣

(ኘ) የግዥ ፈፃሚው አካል በራሱ ፍላጐትና አመቺነት ውሉን ምንጊዜም ሊያቋርጠው ይችላል፣

(አ) ከፍተኛ የጉዳት መጠን ደረጃ ላይ ተደረሰ የሚባለው በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 27.1(ለ) የተመለከተውን ሲሟላ ነው።

22.4 አቅራቢው በዚህ ንዑስ አንቀጽ 22.4 ከ (ሀ) እስከ (መ) ከተጠቀሱት ሁኔታዎች አንደኛው ሲያጋጥም ከ30 ቀናት ያላነሰ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ማቋረጥ ይችላል።

(ሀ) ግዥ ፈፃሚው አካል በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 26 መሠረት በግልግል ጉዳይ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በውሉ መሠረት ለአቅራቢው መከፈል የሚገባውን ክፍያ ከአቅራቢው ጥያቄ በቀረበለት በ30 ቀናት ውስጥ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ፣

(ለ) የግዥ ፈፃሚው አካል በውሉ ግዴታ የገባበትን መሠረታዊ የሆነ ጉዳይ ሳይፈፀም በመቅረቱ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ45 ቀናት ጊዜ ውስጥ (አቅራቢው በተሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ) በውሉ መሠረት ሳይፈፅም የቀረ እንደሆነ፣

(ሐ) አቅራቢው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከአቅርቦቱ ዋነኛውን ክፍል ከ60 ቀናት ባላነሰ ጊዜ መፈፀም ሳይቻል የቀረ እንደሆነ፣

(መ) የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 26 መሠረት በግልግል በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሠረት ሳይፈፅም የቀረ እንደሆነ፣

22.5 በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 22.3 ከ(ሀ) እስከ (ነ) ወይም በንዑስ አንቀጽ 22.4 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች በመከሰታቸው ምክንያት በሁለቱም ወገኖች ያለመግባባት ሲፈጠር ያለመግባባቱ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 26 በተመለከተው መሠረት የሚፈታ ይሆናል፡፡

22.6 በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 22.3 ከ(ሀ) እስከ (ነ) በተመለከተው ምክንያት የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውሉን ሲያቋርጥ በአቅራቢው በሙሉ ወይም በከፊል ያልቀረቡትን ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሌላ መንገድ ግዥ መፈፀም ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አቅራቢው ውል ያልተቋረጠባቸውን ግዴታዎች መፈፀሙን ይቀጥላል፡፡

22.7 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውሉን ያቋረጠው በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 22.3 (ኘ) ምክንያት ከሆነ ውሉ የተቋረጠው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አመቺነት ሲባል መሆኑን በመግለጽ የውል አፈፃፀሙ መቋረጡንና ከመቼ ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚሆን መግለፅ አለበት፡፡

22.8 የግዥ ፈፃሚው አካል ውሉን ያቋረጠው በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 22.3 (ኘ) መሠረት ሲሆን የተጠናቀቁና ከማስጠንቀቂያ በኋላ በ28 ቀናት ውስጥ ለመረከብ ዝግጁ መሆን የሚችሉ ዕቃዎችን በውሉ ዋጋና ሁኔታ ይረከባል፡፡ ለቀሩት ዕቃዎች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ቀጥሎ ያሉትን አማራጮች መከተል ይችላል፡፡

(i) ያለቀውን ከፊል ዕቃ ወይም አገልግሎት በውሉ ጨረታ ዋጋ መረከብ፣ እና/ወይም

(ii) ቀሪውን መሰረዝና በከፊል ለተጠናቀቁት ዕቃዎችና አገልግሎቶች የተስማሙበትን ዋጋ እንዲሁም አቅራቢው ቀደም ሲል ለገዛቸው ዕቃዎችና ቁሳቁሶች መክፈል አለበት፡፡

22.9 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውሉን ያቋረጠው በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 22.3 (ሐ) ምክንያት ከሆነ ለአቅራቢው የሚከፈለው ካሣ አይኖርም፡፡ ውል የማቋረጡ ድርጊት የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ያለውን የመክሰስ መብት ወይም ሌላ መፍትሔ የሚጎዳ ወይም የሚገድብ መሆን የለበትም፡፡

22.10 የግዥ ፈፃሚው አካል ውሉን ያቋረጠው በዚህ አንቀጽ መሠረት አንዳንድ ጥርጣሬዎችን ለማስወገድ ሲሆን የውሉን ዋጋ መሠረት በማድረግ አቅራቢው ክፍያ የመጠየቅ መብቱን አይገድበውም፡፡

**23.** *ከውል መቋረጥ በኋላ ያሉ ሁኔታዎች*

23.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤትና አቅራቢው ውሉ ከተቋረጠ ወይም ከተጠናቀቀ በኋላም ቢሆን የውሉን ግዴታዎች፣ ድንጋጌዎችና ሁኔታዎች ለማክበር ሁለቱም ወገኖች ተስማምተዋል፡፡

23.2 ውሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ከዕቃዎችና አገልግሎቶች አቅርቦት ጋር በተየያዘ በሙሉም ሆነ በከፊል የተያዙ መረጃዎች፣ ሰነዶችና ጽሑፎች (በኤሌክትሮኒክ የተያዙትንም ይጨምራል) አቅራቢው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማስረከብ አለበት፡፡ አቅራቢው በርክክብ ወቅት ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሙሉ ትብብር ማድረግ አለበት፡፡ የሚያደርገው ትብብርም ያለምንም እንቅፋት ሰነዶችን፣ ሪፖርቶችን፣ ማጠቃለያዎችንና ሌሎች መረጃዎችን በተሟላ ሁኔታ ለግዥው ፈፃሚ መ/ቤት በማስረከብ ይሆናል፡፡

**24.** *የመብቶችና ግዴታዎች መቋረጥ*

24.1 ውሉ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 22 መሠረት ሲቋረጥ ወይም ውሉ ሲጠናቀቅ ከውሉ ጋር የተያያዙት መብቶችና ግዴታዎችም ከዚህ በታች በተጠቀሱት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ይቋረጣሉ፡፡

(ሀ) እነዚህ መብቶችና ግዴታዎች በውሉ መቋረጥ ወይም መጠናቀቅ ቀን የነበሩ ከሆነ፣

(ለ) በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 46 መሠረት አቅራቢው የሂሳብ ሰነዶችና ሌሎች ጽሑፎች ኦዲትና ምርመራ እንዲደረግባቸው የመፍቀድ ግዴታ ሲኖርበት፣

(ሐ) በተዋዋይ ወገኖች በሕግ የተሰጠ መብት ሲሆን፣

(መ) ከታች በተመለከተው አንቀጽ 25 መሠረት የዋስትና መብት ሲኖር፡፡

**25.** *ዋስትና* **(Warranty)**

25.1 በውሉ ውስጥ በተለየ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር የሚቀርቡት ዕቃዎች በሙሉ አዲስ፣ ከዚህ በፊት ጥቅም ላይ ያልዋሉ፣ ወቅታዊ፣ ዘመናዊ ሞዴሎችና ንድፎችን ያካተቱ መሆን አለባቸው፡፡

25.2 በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 52.1 መሠረት አቅራቢው ያቀረባቸው ዕቃዎች ከንድፍ ስሕተትና ከመሳሰሉት ነፃ መሆናቸውንና ለአገልግሎት በሚውሉበት ሀገር ውስጥ በተፈለገው ሁኔታ መጠቀም የሚቻል መሆኑ ማረጋገጥ አለበት፡፡

25.3 በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 53.1 መሠረት አቅራቢው የሚያቀርበው ዋስትና ዕቃዎቹ በሙሉ ወይም በከፊል ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ በልዩ የውል ሁኔታ በሚገለጸው መሠረት ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት።

25.4 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተረከባቸው ዕቃዎች ውስጥ ችግር ያለባቸው መኖራቸውን ካረጋገጠ የችግሩን ሁኔታ በመግለጽ ወዲያውኑ ለአቅራቢው ማሳወቅ አለበት። በተቻለ መጠን አቅራቢው በአካል ቀርቦ ችግሩን እንዲመረምር ለማድረግ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሁሉንም አማራጮች መጠቀም ይኖርበታል።

25.5 አቅራቢው ማስታወቂያ እንደደረሰው በልዩ የውል ሁኔታዎች በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ችግር ያለባቸውን ዕቃዎች ከግዥ ፈፃሚው አካል ምንም ተጨማሪ ወጪ ሳይጠይቅ መቀየር ወይም መጠገን ይኖርበታል።

25.6 አቅራቢው የተበላሹትን ወይም ችግር ያለባቸውን ዕቃዎች ወደ አምራቹ ለመውሰድና መልሶ ወደ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለመመለስ የሚወጣውን ወጪ የመሸፈን ኃላፊነት አለበት።

25.7 አቅራቢው ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ በልዩ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 25.5 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት ዕቃዎቹን ካልቀየረ ወይም ካልጠገነ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን እርምጃ ይወስዳል። የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚወስደው እርምጃ ምክንያት ለሚከሰቱ ወጪዎችና ሌሎች ሥጋቶች አቅራቢው ኃላፊነት ይወስዳል።

**26.** *የአለመግባባቶች አፈታት*

26.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጽሑፍ ካላሳወቀው በስተቀር አቅራቢው አለመግባባቶች በሚፈጠሩበት ጊዜም ቢሆን የውሉ ሁኔታዎች ማስፈፀሙን ለመቀጠል ሁለቱም ወገኖች ተስማምተዋል።

26.2 ከውሉ የሚመነጩ ማንኛውንም አለመግባባቶች ወይም ውዝግቦች የግዥ ፈፃሚው አካልና አቅራቢው በቀጥታና ይፋ ባልሆነ ሰላማዊ ድርድር ለመፍታት ማንኛውንም ጥረት ያደርጋሉ።

26.3 ተዋዋዮቹ የተነሱትን አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ መፍታት ካልቻሉ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 26.4 በተመለከተው የአለመግባባቶች አፈታት ሥርዓት መሠረት የሚከናወን ይሆናል።

26.4 ከላይ በንዑስ አንቀጽ 26.3 መሠረት ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በውል አፈጻጸም ወቅት ያጋጠማቸውን አለመግባባት ለመፍታት አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን የሚጠቀሙ ከሆነ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት በተቋቋሙ እና በተገቢው አካል ዕውቅና በተሰጣቸው የግልግል ዳኝነት አካላት በኩል ይሆናል፡፡

26.5 ተዋዋዮች አለመግባባትን ወይም ውዝግብን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከጀመሩበት ዕለት ጀምሮ በ28 ቀናት ውስጥ መፍታት ካልቻሉ በልዩ የውል ሁኔታው በሚገለጸው መሰረት አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን መጠቀም ይችላሉ፡፡ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን የሚጠቀሙ ከሆነ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት በተቋቋሙ እና በተገቢው መ/ቤት ዕውቅና በተሰጣቸው አካላት በኩል ያለበት ሲሆን መ/ቤቱ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን የሚጠቀም ከሆነ በልዩ የውል ሁኔታዎች ላይ ማሳወቅ አለበት፡፡ ከላይ በተዘረዘሩት አማራጮች መፍታት ካልተቻለ አንደኛው ወገን የኢትዮጵያ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ሊያቀርበው ይችላል፡፡

26.6 በሕጉ መሠረት ወደ ዳኝነት አካል ማቅረብ የሚችሉት በተዋዋዮቹ ወገኖች ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው፡፡

**27.** *የታወቁ ጉዳቶች ካሳ*

27.1 በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 19 በተመለከተው ካልሆነ በስተቀር አቅራቢው ዕቃዎቹንና አገልግሎቶቹን በሙሉ ወይም በከፊል በውሉ ጊዜ ውስጥ መፈፀም ሲያቅተው ሌሎች የመፍትሔ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው ግዥ ፈፃሚው አካል የውል ዋጋን መሠረት አድርጎ የጉዳት ማካካሻውን በሚከተሉት ስልቶች ሊቀንስ ይችላል፡፡

(ሀ) ያልቀረቡ ዕቃዎች ዋጋ ላይ በየቀኑ 0.1% ወይም 1/1000 (ከአንድ ሺህ አንድ) ቅጣት፡፡ በየቀኑ የሚፈፀመው ቅጣት ዕቃዎቹ እስኪቀርቡ ድረስ ይቀጥላል፡፡

(ለ) ከፍተኛው የጉዳት ካሣ መጠን ከውል ዋጋው 10% በላይ መብለጥ አይችልም፡፡

27.2 አቅራቢው ውል በመፈጸም ረገድ በመዘግየቱ የውሉ ስራዎች ላይ ጉዳት የሚደርስ ሲሆን የግዥ ፈጻሚው አካል ከፍተኛው የጉዳት ካሳ መጠን (10%) እስኪደርስ ድረስ መጠበቅ ሳያስፈልገው በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 22 መሰረት የቅድሚያ ማስታወቂያ በመስጠት ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

**28.** *ምስጢራዊነት*

28.1 ተዋዋይ ወገኖች ሰነዶችንና መረጃዎችን ለሦስተኛ ወገን ሳያስተላልፉ በምስጢር መያዝ ይኖርባቸዋል። ያለአንደኛው ወገን ስምምነት የተፃፈ ስምምነት ወይም በሌላኛው ወገን የተሰጠውን ማንኛውም ሰነድ (ማስረጃ) ወይም ሌላ መረጃ ከውል በፊት፣ በውል ጊዜ ወይም በኋላ የተሰጠ ቢሆንም እንኳ ለሌላኛው ተዋዋይም ሆነ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት ከሕግ ጋር የሚቃረን፣ ተቀባይነት የሌለውና ውድድርን የሚገታ ተግባር ነው። ከላይ የተጠቀሱት ቢኖሩም አቅራቢው ለንዑስ ተቋራጭ ለውሉ አፈፃፀም የሚረዱትንና ከግዥ ፈፃሚው አካል የተረከባቸውን ሰነዶች፣ ማስረጃዎችና ሌሎች መረጃዎች ምስጢርነታቸው እንዲጠበቅ ቃል በማስገባት ሊሰጠው ይችላል።

28.2 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከአቅራቢው የተቀበላቸውን ሰነዶች፣ ማስረጃዎችና ሌሎች መረጃዎች ከውሉ ጋር ለማይዛመዱ ምክንያቶች ሊገለገልበት አይችልም። በተመሳሳይ ሁኔታም አቅራቢው ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተቀበላቸውን ሰነዶች፣ መረጃና ሌላ ማስረጃ ከተፈለገው ግዥ ወይም አገልግሎት ውጭ ለሌላ ዓላማ አይገለገልበትም።

28.3 በዚህ አንቀጽ የተጣሉት የምስጢራዊነት ግዴታዎች ቢኖሩም ቀጥለው የተዘረዘሩት ሁኔታዎች በተዋዋይ ወገኖች ላይ ተግባራዊ አይሆኑም።

(ሀ) ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወይም አቅራቢው የውሉን አፈፃፀም ፋይናንስ ከሚያደርጉ ሌሎች ተቋማት ጋር የሚጋራው መረጃ፣

(ለ) በተዋዋዮች ጥፋት ባልሆነ ሁኔታ ውሉ በሚመሰረትበት ወቅት ወይም ወደፊት በሕዝብ ይዞታ ሥር የሚገባ መረጃ፣

(ሐ) መረጃውን ለማውጣት ሕጋዊ ሥልጣን ባለው አካል አማካኝነት ሦስተኛ አካል ዘንድ የደረሰ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

(መ) መረጃው ይፋ በወጣበት ጊዜ ለተዋዋይ ወገን ከመድረሱ አስቀድሞ በሶስተኛ ሰው የተያዘ ለመሆኑ ሊረጋገጥ የሚችል ሲሆን፣

(ሠ) አንደኛው ተዋዋይ ወገን መረጃው ይፋ እንዲሆን በጽሑፍ የፈቀደ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

28.4 ተዋዋይ ወገኖች ውሉ ከመመስረቱ በፊት የነበራቸውን ጠቅላላ እውቀት፣ ልምድና ክህሎት ለመጠቀም አይከለከሉም።

28.5 የግዥ ፈፃሚው አካል ከኦዲቲንግና ከወቅታዊ የገበያ ዋጋዎች ጥናት ጋር የተያያዙ ምስጢራዊ መረጃዎች አቅራቢውን በየጊዜው በጽሑፍ እያሳወቀ ለሶስተኛ ወገን መስጠት ይችላል። መረጃውን የሚቀበሉት የሶስተኛ ወገን አካላትም መረጃውን ለተፈለገበት ዓላማ በመጠቀም ረገድ በምስጢር እንዲጠብቁና እንዲጠቀሙ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጥረት ያደርጋል። የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተጨባጭ መረጃ ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ ሳያረጋግጥ የዝቅተኛ ዋጋ ጥያቄ አያቀርብም።

28.6 አቅራቢው ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ተስማምቷል።

(ሀ) በንዑስ አንቀጽ 28.6 (ለ) መሠረት መረጃን ይፋ ማድረግ ወይም አለማድረግ ውሳኔ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውሳኔ ብቻ መሆኑን፣

(ለ) በንዑስ አንቀጽ 28.6 (ሀ) መሠረት አቅራቢው በመረጃዎች ይፋ ማድረግና አለማድረግ ሂደት ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጋር መተባበር አለበት። በዚሁ ረገድ አቅራቢው የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚያቀርብለትን የትብብርና የድጋፍ ጥያቄ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ መልስ ለመስጠት ተስማምቷል።

28.7 አቅራቢውና ንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢው በቁጥጥራቸው ስር የሚገኘውን መረጃ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሲጠይቅ በ5 የሥራ ቀናት (ወይም የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚወሰነው ሌላ የጊዜ ገደብ) መስጠት አለባቸው።

28.8 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የአቅራቢውን ምስጢራዊ መረጃ ይፋ በማድረግ ሂደት መመሪያዎች በሚፈቅዱት መሠረት አቅራቢውን ማማከር ይኖርበታል።

28.9 በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩት የምስጢራዊነት የውል ሁኔታዎች ውሉ ከመመስረቱ በፊት በተዋዋይ ወገኖች ዘንድ የነበሩ የሚስጢራዊነትን ሁኔታዎች በማንኛውም ሁኔታ ሊያሻሽሉ አይችሉም።

28.10 አንቀጽ 28 ያካተታቸው የምስጢራዊነት ሁኔታዎች (የግል መረጃን ይጨምራል) ላልተወሰነ ጊዜ ፀንተው ይቆያሉ። በዚህ ውል በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር የዚህ አንቀጽ ሁኔታዎች ውሉ ከተቋረጠ ወይም ከተጠናቀቀ በኋላ ለ3 ዓመታት ፀንተው ይቆያሉ።

28.11 አቅራቢው በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ሳይፈፀም ሲቀር የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወዲያውኑ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን የማቋረጥ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**29.** *የፈጠራ ባለቤትነት መብት*

29.1 በልዩ የውል ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በአቅራቢው አማካይነት የሚቀርቡ የንድፎች፣ ሰነዶችና ሌሎች ዕቃዎች መረጃ የባለቤትነት መብት የአቅራቢው ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በሌላ ሦስተኛ አካል ለግዥ ፈፃሚው በቀጥታ ወይም በአቅራቢው አማካኝነት የሚቀርብ የሦስተኛ አካል መረጃ የባለቤትነት መብት የሦስተኛው አካል ይሆናል፡፡

**30.** *ልዩ ልዩ*

30.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በዚህ ውል መሰረት ስልጣን በተሰጠው በማንኛውም ሰው የሚወሰን ማንኛውም ውሳኔ ወይም በዚህ ውል መሰረት በአጠቃላይ ወይም በዝርዝር የሚፈጸምን ተግባር ለማከናወን ስልጣን የተሰጠውን ሰው ማንነት ለማወቅ አቅራቢው ሲጠይቅ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ያሳውቃል፡፡

30.2 አቅራቢው በየጊዜው ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት የውሉን ሁኔታዎች በተግባር ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን ማንኛውንም አግባብነት ያላቸው ደንቦች ወይም ተጨማሪ ሰነዶችን የማስፈጸም ተግባር ይኖረዋል፡፡

30.3 ማንኛውም የውሉ አካል በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውድቅ ከተደረገ ወይም ህጋዊ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ከተደረገ እንደዚህ አይነቱ በፍርድ ቤት ወይም በህግ ለአንድ ለተወሰነ የውሉ አካል ደንቦች ውድቅ መደረግ ወይም ህጋዊ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው መደረግ ለቀሪው የውሉ አካል ተጽዕኖ አይኖረውም፡፡

30.4 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወይም አቅራቢው ውሉን ካለመፈጸሙ የተነሳ ወይም የውሉን ደንቦችና ሁኔታዎች በትክክል ካለማካሄዱ የተነሳ ወይም ደግሞ ይህንን ውል የሚጥስ ሁኔታ ከተከሰተ የዚህ ውል ተከታታይ ደንቦችና ሁኔታዎችን ማስቀረት ወይም መጣስ ሆኖ አይቆጠርም፡፡

30.5 እያንዳንዱ ወገን ውሉን ለማዘጋጀት ወይም ለማስፈጸም የሚወጡትን ማንኛውም ወጪዎች፤ የህግና ሌሎች ወጪዎችን ጨምሮ የየራሱን ወጪዎች የመሸፈን ሀላፊነት አለበት፡፡

30.6 አቅራቢው በህግ በኩል ወይም በማንኛውም ፍ/ቤት የክስ ሂደት እንደሌለበት፤ በማንኛውም የአስተዳደር አካላት የአቅራቢው የፋይናንስ ሁኔታ ወይም የንግድ ስራውን ወይም እንቅስቃሴውን ሊነካ ወይም ሊያስጠይቅ የሚችል ጉዳይ የሌለው መሆኑን ዋስትና ይሰጣል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ አራቅቢው ውሉን ለመዋዋል የሚያግደው ምንም አይነት የውል ሁኔታ እንደሌለ፤ እንዲሁም አቅራቢው በውሉ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ አደጋዎችና አጋጣሚዎችን

በመገንዘብ ወይም በውሉ ውስጥ ያሉትን ማንኛውም ግዴታዎችና መረጃዎች በመረዳት በዚሁ መሰረት ሊፈጽም የተስማማ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

30.7 በዚህ ውል ውስጥ የተካተቱት መብቶችና መፍትሔዎች አጠቃላይ በመሆናቸው በሌላ ውል ውስጥ ከተሰጡ መብቶች ወይም መፍትሔዎች ጋር ሊራመዱ የሚችሉ ናቸው፡፡ በዘህ አንቀጽ ውስጥ "መብት'' ሲባል ማንኛውም ስልጣን፣ መብት፣ መፍትሔ ወይም የንብረት ባለቤትነት ወይም የዋስትና ባለመብትነትን ያካትታል፡፡

#### ሐ. የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግዴታዎች

### **31.** *ድጋፍ ማድረግ*

31.1 በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በተገለፀው አግባብ መሰረት በዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ወቅት አቅራቢው ከሚመለከታቸው አካላት ዕቃዎችን የማስገቢያ ፈቃዶች ሲፈልግና ድጋፍ እንዲደረግለት ሲጠይቅ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተቻለውን ሁሉ ድጋፍና እገዛ ያደርግለታል፡፡

31.2 በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 31.1 መሠረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ኃላፊነቱን በመወጣት ሂደት የሚያጋጥሙትን ወጪዎች የመሸፈን ኃላፊነት አለበት፡፡

#### መ. ክፍያ

### **32.** *የውል ዋጋ*

32.1 በዚህ ውል መሰረት ማንኛውም ጭማሪዎችና ማስተካከያዎች ወይም ቅናሾች ሊደረግ የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የውሉ ዋጋ በስምምነቱ ላይ የተገለፀው ብቻ ይሆናል፡፡

32.2 የውል ዋጋ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተደረገባቸውን ቅናሾች ጨምሮ ነው፡፡ እንዲሁም የውል ዋጋ የማሸጊያ ዕቃዎች፣ የመጫንና የማውረድ፣ የማጓጓዣና የመሳሰሉት ወጪዎችን፣ እንዲሁም ተገቢ የሆኑ ግብሮችና ቀረጦችን ይጨምራል፡፡

32.3 ከታች በተመለከተው አንቀጽ 33 ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በዚህ ውል መሠረት ለቀረቡት ዕቃዎችና ለተከናወኑ አገልግሎቶች አቅራቢው የሚጠይቀው ዋጋ በጨረታ ካቀረበው ዋጋ የተለየ መሆን የለበትም፡፡

32.4 በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 17.1 በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የውል ዋጋ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 32.1 ውስጥ ከተመለከተው በላይ ሊጨምር የሚችለው ተዋዋዮች በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 16 መሠረት በተጨማሪ ክፍያ ላይ የተስማሙ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

**33.** *የዋጋ ማስተካከያ*

33.1 የውሉ ዋጋ ውሉ በሚፈፀምበት የመጀመሪያ ሶስት (3) ወራት ውስጥ አይቀየርም፡፡

33.2 በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት መሰረት ከተወሰኑ እቃዎች ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ውሉ ተፈፃሚ ከሚሆንበት ቀን ጀምሮ ከሶስት (3) ወራት በኋላ ሊቀርብ ይችላል፡፡

33.3 አቅራቢው ያቀረበው የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው አቅራቢው ተጠይቆ ቢያንስ በዓመት ሊያቀርብ ከሚገባው የውል መጠን አንድ አራተኛውን ካቀረበ በኋላ ብቻ ነው፤

33.4 የማዕቀፍ ግዥ አቅራቢዎች ቁጥር ከአንድ በላይ ሲሆንና የሚያቀርቡት ዕቃ ምርት መለያ ወይም የንግድ ስም የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ ለአቅራቢዎቹ የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ እያንዳንዱ አቅራቢ ውል የገባበት ምርት በገበያ ላይ ያመጣውን የዋጋ ልዩነት ብቻ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

33.5 አቅራቢው የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ካላቀረበ በስተቀር ሁሉም ዋጋዎች አይቀየሩም፡፡ አቅራቢው ለማዕቀፍ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ማስታወቂያ በመስጠት ይህን ድንጋጌ በማንኛውም ሰአት መጠቀም ይችላል፡፡

33.6 በዚህ አንቀፅ ላይ በተገለፀው መሰረት የማዕቀፍ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ በውሉ ዋጋ ላይ ጭማሪ ወይም ቅናሽ ሊያደርግ ይችላል፡፡

33.7 ውሉ አንድ ጊዜ ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ ይህ ድንጋጌ በውሉ የቆይታ ጊዜ ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

33.8 በሁሉም የወደፊት አቅርቦቶች ላይ እንደአስፈላጊነቱ የዋጋ ማስተካከያዎች ይወሰናሉ፡፡

33.9 በዚህ ውል ላይ በግልፅ ካልተቀመጠ በስተቀር የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው በልዩ የውል ሁኔታዎች ላይ በግልፅ ተጠቅሰው ለተቀመጡት ዕቃዎች ብቻ ነው፡፡

33.10 በምርት ወይም አገልግሎቶች ዓይነት ላይ ተመስርቶ በውሉ ዋጋ ላይ የሚደረጉ የዋጋ ማስተካከያዎች እንደ ቅደምተከተላቸው ከታች በተዘረዘሩት በኢትዮጵያ የስታቲስቲክስ አገልግሎት የሚሰጡ የዋጋ ኢንዴክሶች ወይም ከአምራች ድርጅቶች ወይም ባለስልጣን መ/ቤቱ በማዕከል በሚያስጠናው የገበያ ዋጋ ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መወሰን አለባቸው፡፡

(ሀ) በተጠቃሚ የዋጋ ኢንዴክስ ላይ የሚኖሩ ለውጦች በምርቱ ወይም አገልግሎቱ ላይ ተፅእኖ የሚፈጥሩ ከሆነ፣ ወይም

(ለ) በአምራቹ የዋጋ ኢንዴክስ ላይ የሚኖሩ ለውጦች በምርቱ ወይም አገልግሎቱ ላይ ተፅእኖ የሚፈጥሩ ከሆነ፣ ወይም

(ሐ) በአገልግሎት ሰጪ የዋጋ ኢንዴክስ ላይ የሚኖሩ ለውጦች በምርቱ ወይም አገልግሎቱ ላይ ተፅእኖ የሚፈጥሩ ከሆነ፣ ወይም

(መ) በአማካይ የገቢ ኢንዴክስ ላይ የሚፈጠሩ ለውጦች በአገልግሎቱ ላይ ተፅእኖ የሚፈጥሩ ከሆነ።

33.11 የማዕቀፍ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት  የዋጋ ማስተካከያን እንዲወሰን የሚያስችሉ ሁሉንም ስሌቶችና ደጋፊ መረጃዎች አቅራቢው ለተዋዋዩ የማዕቀፍ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ማቅረብ አለበት።

33.12 በመነሻነት በሚወሰደው የዋጋ ኢንዴክስ እና በወርሀዊ የዋጋ ኢንዴክስ መካከል በሚፈጠሩ ልዩነቶች ላይ ተመስርቶ የክፍያ ማስተካከያዎች ላይ ጭማሪ ወይም ቅናሽ ሊደረግ ይችላል።

33.13 በእያንዳንዱ እቃ ላይ የሚደረግ ማስተካከያን ለመወሰን የሚከተለውን ቀመር ከላይ ከተገለፁት መስፈርቶች ጋር በማጣመር ይሰላል።

የተዋ = (የአዋ - የቀዋ) + የውዋ

የተዋ (Adjusted Price) = ለአቅራቢ የሚከል የተስተካከለ ዋጋ

የቀዋ (Base Price) = የዕቃው/አገልግሎቱ ጨረታው በተከፈተበት ወቂት የነበረ የገበያዋጋ

የአዋ (Current Price) = የዕቃው/አገልግሎቱ ዋጋ ማተካከያ በሚደረግበት ወር የገበያዋጋ

የውዋ (Contract Price) = በውል ላይ የተገለፀ እና ለአቅራቢው ለሚከፈለው ክፍያ እንደ መነሻ ሆኖ የሚያገለግል ዋጋ

33.14 የእያንዳንዱ የተመዘገበ ክፍል ክፍልፋይ እና በዋጋ ማስተካከያ ቀመር ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ ትክክለኛ ጥምር ክፍሎች በልዩ የውል ሁኔታዎች ይወሰናሉ።

33.15. በውሉ ዋጋ ላይ ለሚደረግ ጭማሪ የሚቀርበው ማመልከቻ የክፍያው ቀን ከሚጀምርበት ቀን ከ 14 ቀን በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የዋጋ ጭማሪ ከሚቀርብበት ቀን ቀጥሎ ባለው የክፍያ ቀን ከምርቱ ጋር በተያያዘ እንደ አዲስ የውሉ ዋጋ ተፈፃሚ ይሆናል።

33.16 በውሉ ላይ የሚደረግ የዋጋ ጭማሪ ሁለቱ ወገኖች በሌላ ቀን ላይ በጽሁፍ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር ከምርት ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ተዋዋዩ ባለስልጣን የዋጋ ጭማሪውን አስመልክቶ ማስታወቂያ ከሚቀበልበት ቀን ጀምሮ  አዲስ የውሉ ዋጋ ተፈፃሚ ይሆናል።

33.17 ተዋዋዩ ባለስልጣን በንዑስ አንቀፅ 33.12 መሰረት ማስታወቂያ የተሰጠበት ወይም ጥያቄ የቀረበበት የዋጋ ጭማሪን አስመልክቶ   አቅራቢው ባቀረበው የዋጋ ማስተካከያ ማስታወቂያ ወይም ጥያቄ መነሻነት የውሉ ዋጋ አቅራቢው ሊረዳው  በሚችለው መጠን ብቻ ጭማሪ የሚደረግበት ሲሆን ተስተካክሎ ጭማሪ የተደረገበት የውሉ ዋጋ ሁለቱ ወገኖች በሌላ ወገን ላይ ስምምነት ካላደረጉ

በስተቀር እንደ ሁኔታው በንኡስ አንቀጽ 33.14 እና 33.15 ላይ በተገለፀው ቀን ከምርት ወይም አገልግሎት ጋር እንደ አዲስ የውል ዋጋ ተፈፃሚ ይሆናል።

33.18 በዚህ ስምምነት መሰረት በአቅራቢው የሚደረግ ማንኛውም የዋጋ ቅናሽ ተዋዋዩ ባለስልጣን በጽሁፍ ስምምነቱን ካላሳወቀ በስተቀር በስምምነቱ የቆይታ ጊዜ ውስጥ ተቀናሽ አይደረግም።

33.19 በዋጋ ማስተካከያው ቀመር ስሌት መሰረት የሚገኘው የተስተካከለ የውል ዋጋ ከዜሮ በታች ሲሆን ማስተካከያ በሚደረግበት ወቅት በውል ዋጋ መሰረት ማቅረብ ይቻላል። ሆኖም በዚህ ወቅት የመንግሥት መ/ቤቱ አዋጭ አለመሆኑን ሲያምንበት ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል።

33.20 በሚደረገው የዋጋ ማስተካከያው መሰረት የሚኖረው ጭማሪ ከመጀመሪያው የውል ዋጋ 30% (ሠላሳ በመቶ) በላይ ሲሆን ውሉ እንዲቋረጥ ይደረጋል።

## 34. *የክፍያ አፈጻጸም*

34.1 የግዥ ፈፃሚው አካል በዚህ አንቀጽ የውል ግዴታዎች መሠረት አቅራቢው ላቀረባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች በውል ዋጋው መሠረት ለአቅራቢው ክፍያ ይፈጽማል።

34.2 አቅራቢው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለሚያቀርበው የክፍያ ጥያቄ ተገቢ የክፍያ መጠየቂያ ሰነድ በማያያዝ መሆን አለበት። ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ክፍያ መፈፀም የሚችለው በውሉ ውስጥ የተጠቀሱት ግዴታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ነው። ተዋዋይ ወገኖች በተከታታይ ኢንስቶልሜንት (Installment) መሠረት ክፍያ እንዲፈፀም ሲስማሙ አቅራቢው ለእያንዳንዱ ርክክብ የክፍያ ጥያቄና የክፍያ መጠየቂያ ማቅረብ ይጠበቅበታል።

34.3 ትክክለኛ የክፍያ መጠየቂያ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል።

(ሀ) የግዥ ትዕዛዙ የመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መቅረብ አለበት።

(ለ) የተፃፈበት ቀንና መለያ ቁጥር፣

(ሐ) እንዲከፈል የተጠየቀው የገንዘብ መጠን፣

(መ) እንዲከፈል የተጠየቀው የገንዘብ መጠን በውሉ መሠረት በትክክል የተሰላ መሆን አለበት፣

(ሠ) የሚቀርበው የክፍያ መጠየቂያ ግዥ ፈፃሚው መ//ቤት በቀላሉ ሊያረጋግጠው በሚችል አኳኋን የዕቃዎች ወይም አገልግሎት መግለጫ፣ ብዛት፣ መለኪያና የእያንዳንዱን ዋጋ የሚያሳይ መሆን አለበት፣

(ረ) የሚቀርበው የክፍያ መጠየቂያ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተወካይ ከተረጋገጠ የዕቃ መረከቢያ ሰነድ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት። የዕቃ መረከቢያ ሰነዱ በውሉና በግዥ ትዕዛዙ መሠረት ዕቃዎችና አገልግሎቶች መቅረባቸውን ማረጋገጫ ነው፣

(ሰ) የክፍያ መጠየቂያ ሰነዱ የአቅራቢውን የባንክ ቁጥርና አድራሻ መረጃ ማካተት አለበት።

(ሸ) እንደአስፈላጊነቱ የክፍያ መጠየቂያ ሰነዱ ከሽያጭ ታክስ ነፃ (የነፃ መብት ካለ) መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ተሟልተው ካልቀረቡ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተሟልተው እስኪቀርቡለት ድረስ ክፍያውን ሊያዘገየው ይችላል።

34.4 በዚሁ ንዑስ አንቀጽ 34.3 መሠረት ተቀባይነት ያለው ፋክቱር ሲቀርብ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በልዩ የውል ሁኔታ ውስጥ በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተገቢውን ክፍያ ለአቅራቢው መፈፀም አለበት።

34.5 በውሉ መሠረት ለአቅራቢው የሚፈፀመው ክፍያ በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በተመለከተው የገንዘብ ዓይነት ነው።

34.6 በአቅራቢው የሚቀርበው የክፍያ መጠየቂያ የታክስ ክፍያዎችን ለይቶ የሚያሳይ መሆን አለበት።

34.7 ተጨማሪ የግዥ ትዕዛዝ በሲስተም በቅድሚያ ካልተሰጠ በስተቀር ከግዥ ትዕዛዝ በላይ ለሚቀርቡ ዕቃዎች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ኃላፊነት የለበትም።

34.8 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤትት በአቅራቢው የቀረበውን የክፍያ ጥያቄ ስለተቀበለ ብቻ አቅራቢው የውል ግዴታዎቹን እንደተወጣ አያስቆጥርም።

34.9 በንዑስ አንቀጽ 34.10 መሰረት የውል ዋጋ በውሉ ጊዜ ጭማሪ አይደረግበትም።

34.10 በንዑስ አንቀጽ 33 መሰረት በቀረበው የዋጋ ማስተካከይ ለይ በሁለቱም ወገኖች በ3 ወር ውስጥ ስምምነት ላይ ካልደረሱ ልዩነታቸውን በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 26 መሰረት መፍታት የኖርባቸዋል።

34.11 አቅራቢው የቅድሚያ ክፍያ እንዲሰጠው ከጠየቀ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከውል ዋጋው ከ30% ያልበለጠ ሊከፍለው ይችላል።አቅራቢው የቅድሚያ ክፍያ ጥያቄ በሚጠይቅበት ጊዜ ከጠየቀው መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ እንደአቅራቢው ምርጫ ከታወቀ ባንክ የሚሰጥ የተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ማቅረብ አለባቸው።

34.12 የቅድሚያ ክፍያ ዋስትናው የጊዜ ገደብ ካበቃና አቅራቢው ሊያራዝመው ፈቃደኛ ካልሆነ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በውሉ መሠረት ከሚከፍለው ክፍያ እኩል መጠን ያለው ገንዘብ ቀንሶ ያስቀራል።

34.13 ውል በማንኛውም ምክንያት ከተቋረጠ አቅራቢው የወሰደውን የቅድሚያ ክፍያ ለማካካስ ሲባል የቅድሚያ ክፍያ ዋስትናውን መውረስ ይችላል።

## 35. *የውል ቅፆች*

35.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤትና አቅራቢው በውሉ ካልተስማሙ በስተቀር

(ሀ) የዕቃ ማስረከቢያ ሰነዱ ከእያንዳንዱ የዕቃ ርክክብ ጋር መቅረብ ይኖርበታል፣

(ለ) የሚቀርበው የክፍያ መጠየቂያ አቅራቢው በሲስተም ማቅረብ ይኖርበታል፣

(ሐ) ሁሉም የዕቃ ማስረከቢያ ሰነዶች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የግዥ ትዕዛዝ ቁጥር፣ ስም፣ አድራሻ፣ የዕቃዎቹ መግለጫና ብዛት፣ ለማሸግያ ሳጥኖች ተጨማሪ ክፍያ መኖር አለመኖሩ፣ የማሸጊያ

ሳጥኖች የሚመለሱ ስለመሆናቸው ወይም አለመሆናቸውና የመሳሰሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

35.2 ንዑስ አንቀጽ 35.1 ላይ የተገለጹት ከሌሎች የውሉ ሁኔታዎች ጋር መጣጣም ይኖርባቸዋልል፡፡

35.3 ተዋዋይ ወገኖች በቅድሚያ በጽሑፍ ሲስማሙና ሌሎች አማራጮችን ለመጠቀም ሲፈልጉ አንቀጽ 35.1 ግምት ውስጥ ላይገባ ይችላል፡፡

*ረ. የአቅራቢው ግዴታዎች*

## 36. *የአቅራቢው ኃላፊነቶች*

36.1 አቅራቢው በአቅርቦት ወሰን ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም ዕቃዎችና አገልግሎቶች በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 51 እና በማስረከቢያ እና ማጠናቀቂያ ዕቅድ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 53 መሠረት ማቅረብ አለበት፡፡

## 37. *የጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽሙር ማህበር*

37.1 አቅራቢው የጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽሙር ማህበር ከሆነ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚኖረውን ውል በማስፈፀም ሂደት አባላቱ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ናቸው፡፡ የጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽሙር ማህበሩ የሚመራ ሰው ይወክላሉ፡፡ የጥምረት ወይም የሽርክና ወይም የእሽሙር ማህበሩን ውህደትና አመሠራረት የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሳያውቅ መቀየር አይቻልም፡፡

## 38. *ብቁነት (ውል ለመፈፀም)*

38.1 በውሉ መሠረት የሚቀርቡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በክፍል 5 በተመለከተው መሠረት ብቁ ከሆኑት አጋሮችና ግዛቶች መነሻ ይኖራቸዋል፡፡

38.2 ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ሲባል “መነሻ” ማለት ዕቃዎቹ የተቆፈሩበት፣ ያደጉበት ወይም የተመረቱበት ወይንም አገልግሎቱ የቀረበበት ማለት ነው፡፡ ዕቃዎች ተመረቱ የሚባለው በፋብሪካ ተፈብርከው ሲወጡና በምርት ሂደት ውስጥ ሲያልፉ ወይም መሠረታዊ የሆነ አካላዊ መገጣጠሞች ተደርጎባቸው ሲሰሩና አካላቶቹ በመሠረታዊ ፀባዮቻቸው በዓላማ ወይም በአገልግሎት ተቀባይነት ያለው አዲስ ምርት ሲገኝ ማለት ነው፡፡

38.3 የዕቃዎቹና የአገልግሎቶቹ የመነሻ ሀገር ከአቅራቢው ዜግነት ጋር የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡

## 39. *የስነ-ምግባር ደንቦች*

39.1 አቅራቢው በዚህ ውል የተመለከቱትን ግዴታዎች በሚያከናውንበት ጊዜ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ታማኝ አማካሪ ሆኖ ማከናወን ያለበት ሲሆን የግዥ ፈፃሚውን አካል ፈቃድ ሳያገኝ በማንኛውም ጊዜ ከውሉ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ መግለጫ የመስጠት ወይም ከውሉ አፈፃፀም ጋር ተቃራኒ የሆኑ ድርጊቶች መፈፀም የለበትም፡፡

39.2 አቅራቢው፣ የንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢው ወይም የአቅራቢው ሠራተኛ ወይም ወኪል ከዚህ ውል ጋር በተያያዘ ለግዥ ፈፃሚው አካል ማባበያ ለመስጠት የጠየቀ፣ ወይም የሰጠ ከሆነ፣ ስጦታዎችና ጉቦ ያቀረበ ከሆነና ተመሳሳይ ድርጊቶችን መፈፀሙ ከተረጋገጠ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል።

39.3 አቅራቢው ከዚህ ውል ሊያገኝ የሚገባው ሙሉ ክፍያ በውል ዋጋው የተመለከተውን ብቻ ነው። በዚህ ውል መሠረት ከሚያከናውናቸው ተግባራት ወይም ሊፈጽማቸው ከሚገባ ግዴታዎች ጋር በተያያዘ የንግድ ኮሚሽን፣ ቅናሾች ወይም ቀጥተኛ ያልሆኑ ክፍያዎች መጠየቅና መቀበል የለበትም።

39.4 ከዚሁ ውል ጋር በተያያዘ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አቅራቢው ያለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ፈቃድ ምንም ዓይነት ኮሚሽን ወይም የባለቤትነት ክፍያ መቀበል አይችልም።

39.5 አቅራቢውና ሠራተኞቹ ከዚህ ውል ጋር በተያያዘ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያገኙትን መረጃ (መረጃው ከውሉ በፊት፣ በውሉ ጊዜ ወይም ከውሉ በኋላ የተገኘ ቢሆንም) በምስጢር መጠበቅ አለባቸው። ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጽሑፍ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር መረጃውን ለሦስተኛ ወገን አሳልፈው መስጠት የለባቸውም። ከዚህም በተጨማሪ ለዚሁ ውል አፈፃፀም ሲባል ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጥናትና ምርምር እንዲሁም በሙከራ የተገኙ ውጤቶችን በምስጢር መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

39.6 የዚህ ውል ሁኔታዎች ያልተለመዱ የንግድ ወጪዎችን አያስተናግዱም። ያልተለመዱ የንግድ ወጪዎች የሚባሉት ውሉ ውስጥ ያልተጠቀሱ ሕጋዊ ላልሆኑ አገልግሎቶች የሚከፈሉ ኮሚሽኖችና የመሳሰሉትን ያካትታል። እንደዚህ ዓይነት ያልተለመዱ የንግድ ወጪ ጥያቄዎች ሲነሱ ውሉ እንዲቋረጥ ይደረጋል።

39.7 አቅራቢው ከውሉ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውሉ ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ ማረጋገጫ እንዲያቀርብ ሲጠየቅ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል። የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አጠራጣሪ የሆኑ የንግድ ሁኔታዎች መኖራቸውን ከገመተ እውነታውን ለማወቅ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ሊጠይቅ ወይም በአካል ተገኝቶ ሊያጣራ ይችላል።

## 40. የጥቅም ግጭቶች

40.1 አቅራቢው በውል አፈጻጸም ሂደት እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከልና ለማስወገድ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች መውሰድ አለበት። የጥቅም ግጭቶች በተለይ ከኢኮኖሚያዊ ፍላጎት የተነሳ፣ በዝምድና ወይም በሌሎች ግንኙነቶች ወይም የጋራ ፍላጎቶች ምክንያት ሊመነጩ ይችላሉ። ማንኛውም በውል አፈጻጸም ወቅት የሚከሰቱ የጥቅም ግጭቶች ያለምንም መዘግየት ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጽሑፍ መቅረብ ይኖርባቸዋል።

40.2 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል በአቅራቢው በኩል እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎችን ትክክለኛነት የማጣራትና አስፈላጊ ከሆነም ተጨማሪ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው። የአቅራቢው ሰራተኞችና የማኔጅሜንት አባላት የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ በሚችሉ ተግባራት አለመሳተፋቸውን አቅራቢው ማረጋገጥ ይኖርበታል። በእንደዚህ አይነት ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች ቢኖሩ አቅራቢው በአንቀጽ 24 የተመለከተውን በማይጻረር መልኩ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ምንም አይነት ካሳ ሳይጠይቅ አቅራቢው ወዲያውኑ በሌሎች ሰራተኞች መለወጥ ይኖርበታል።

40.3 አቅራቢው የሰራተኞቹን ነጻነት ከሚጎዳ ከማንኛውም ግንኙነት መቆጠብ አለበት። ከእንደዚህ አይነት ተግባር ካልተቆጠበና ሰራተኞቹ ራሳቸውን ችለው በነጻነት የማይሰሩ ከሆነ በውሉ ውስጥ የተመለከቱት የጉዳት ካሳ ክፍያዎች እንደተጠበቁ ሆነው የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ያለምንም ማስታወቂያ ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል።

40.4 ውሉ ከተጠናቀቀ ወይም ከተቋረጠ በኋላ አቅራቢው የሚኖረው ተግባር ከዚህ በፊት በቀረቡ ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች ብቻ የተወሰነ ይሆናል። በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ካልተፈቀደ በስተቀር አቅራቢው ወይም ሌላ ከአቅራቢው ጋር ግንኙነት ያለው አቅራቢ በዕቃዎችና አገልግሎቶች በማቅረብ ተግባር ላይ እንዳይሳተፉ ይደረጋል።

## 41. የፈጠራ ባለቤትነት የካሣ ክፍያ

41.1 አቅራቢው ከአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 41.2 በተጣጣመ መልኩ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ፣

(ሀ) ዕቃዎቹን በኢትዮጵያ ውስጥ በመጠቀሙ፣ ወይም

(ለ) በአቅራቢው የተመረቱትን ዕቃዎች በመሸጡ ምክንያት ሰራተኞቹን ወይም ሀላፊዎቹን በማንኛውም አይነት ክሶች፣ እርምጃዎች ወይም የአስተዳደር ሂደቶች፣ አቤቱታዎች፣ ጥፋቶችና ጉዳቶች የሚከሰቱ ማንኛውም አይነት ወጪዎችን (የጠበቃ ክፍያና ተያያዥ ወጪዎችን ይጨምራል)፣ እንደዚሁም በአገልግሎት ሞዴሎች፣ በተመዘገቡ ንድፎች፣ የንግድ ምልክቶች፣ የባለቤትነት ይዞታዎች ወይም ሌሎች በተመዘገቡም ሆነ ባልተመዘገቡ የአዕምሮአዊ መብቶች ምክንያት የሚከሰቱ ወጪዎችን ለመካስና የግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱን ከጉዳት ነጻ ለማድረግ ተስማምቷል።

41.2 እንዲህ ያለው ካሳ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ከውሉ ውጪ ወይም ከውሉ በፊት በነበረ የዕቃዎች ወይም የመለዋወጫዎች ወይም አገልግሎቶች አጠቃቀምና በአቅራቢው ከቀረቡት ጋር ግንኙነት ወይም ተዛማጅነት የሌላቸውን አይመለከትም።

41.3. በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 41.1 መሰረት በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ላይ የፍ/ቤት አቤቱታ ከቀረበ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወዲያውኑ ለአቅራቢው ያሳውቃል። አቅራቢውም በራሱ ወጪ እና በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ስም ለቀረቡት ክሶች ወይም አቤቱታዎች ፍ/ቤት በመቅረብ ምላሽ ይሰጣል።

41.4. አቅራቢው ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማስታወቂያው በደረሰው በ 28 ቀናት ውስጥ ለቀረቡት ክሶች ወይም አቤቱታዎች ምላሽ እንደሚሰጥ ካላሳወቀ፣ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በራሱ ስም ጉዳዩን የመከታተልና የማካሄድ ነጻነት አለው።

41.4 የግዥ ፈፃሚው አካል ከአቅራቢው በሚያቀርብለት ጥያቄ መሰረት የቀረቡትን የፍ/ቤት ክሶች ወይም አቤቱታዎች ምላሽ በመስጠት ረገድ የሚችለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል። በዚህ ሂደት ውስጥ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚያወጣቸው ማንኛውም አግባብነት ያላቸው ወጪዎች በአቅራቢው ይመለስለታል።

41.5 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አቅራቢውና ሰራተኞቹን ወይም ሀላፊዎቹንና የንዑስ ውል ስምምነት አቅራቢዎቹን በማንኛውም አይነት ክሶች፣ እርምጃዎች ወይም የአስተዳደር ሂደቶች፣ አቤቱታዎች፣ ኪሳራዎችና ጉዳቶች ምክንያት የሚከሰቱ ማንኛውም አይነት ወጪዎችን (የጠበቃ ክፍያና ተያያዥ ወጪዎችን ይጨምራል)፣ እንዲሁም በማናቸውም አይነት የፈቃድ ማስረጃዎች፣ የአገልግሎት ሞዴሎች፣ የተመዘገቡ ንድፎች፣ የንግድ ምልክቶች፣ የባለቤትነት ይዞታዎች ወይም ሌሎች በተመዘገቡም ሆነ ባልተመዘገቡ የአዕምሮአዊ መብቶች ወይም በማንኛውም በንድፍ፣ በዳታ፣በስዕል ወይም በስፔስፊኬሽን ምክንያት የሚከሰቱ ወጪዎችን ለመካስና አቅራቢውን ከጉዳት ነጻ ለማድረግ ተስማምቷል።

## 42. የባለዕዳነት ገደብ

42.1 በወንጀል፣ በግድየለሽነት ወይም ሆን ተብሎ በሚፈጠር ያልተገባ ሥነ ምግባር ካልሆነ በስተቀር

(ሀ) በውል ውስጥም ሆነ ከውል ውጭ በማንኛውም ቀጥተኛ ካልሆነ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚከሰት ጥፋትና ጉዳት፣ ከጥቅም ውጭ መሆን ወይም የምርትና ትርፍ መጥፋት አቅራቢው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ኃላፊ አይሆንም። እነዚህ ገደቦች ግን ከውል ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ ለሚከሰቱ ሌሎች ጉዳቶች አቅራቢው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጉዳት ካሣ እንዳይከፍል አያደርጉትም።

(ለ) የአቅራቢው አጠቃላይ ኃላፊነት በውሉ መሠረትም ሆነ ከውል ውጭ በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ ከተመለከተው አጠቃላይ የውል ዋጋ አይበልጥም። ነገር ግን ይህ ገደብ ችግር ያለባቸውን ዕቃዎች ወይም

መሣሪያዎች ማስጠገኛና መተኪያ ዋጋን አይጨምርም፣ ወይም በሙብት ማስከበሪያ ጥሰት ምክንያት ለግዥ ፈፃሚው አካል ሊከፈል የሚገባውን ግዴታ አይመለከትም።

## 43. አአምሯዊ ንብረት

43.1 ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ 42 መሠረት አቅራቢው ከማንኛውም ግለሰብ በሚቀርብ የአእምሯዊ ንብረት መብት ጥያቄ ምክንያት የሚከሰቱ ማንኛቸውንም ወጪዎችና ተመሳሳይ ሁኔታዎች የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ለመካስ ተስማምቷል።

## 44. የመድን ዋስትና (ኢንሹራንስ)

44.1 በልዩ የውል ሁኔታዎች በተለየ አኳኋን ካልተጠቀሰ በስተቀር በዚህ ውል መሠረት የሚቀርቡ ዕቃዎች በቀላሉ ሊቀየሩ የሚችሉ ገንዘቦችን በመጠቀምና አለም አቀፍ የንግድ ቃሎችን መሠረት በማድረግ በመጋዘን ውስጥ፣ በመንገድና በጉዞ ላይ፣ በርክክብና በመሳሰሉት ሂደቶች ወቅት ለሚደርስባቸው አደጋዎች የመድን ዋስትና መግባት አለባቸው።

## 45. የምርቶች መረጃ

45.1 አቅራቢው ከግዥ ፈፃሚው አካል በሚያደርገው የሚዲያ (Media) ስምምነት መሠረት በየጊዜው የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በብቸኝነት ተጠቃሚ የሚሆንበትን የምርት መረጃ ያቀርብለታል።

45.2 አቅራቢው ለግዥ ፈፃሚው አካል የሚያቀርበው የምርት መረጃ የተሟላና ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል። እንዲሁም የምርት መረጃው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ላይ ምንም አይነት ዕዳ የሚያስከትሉ ዳታዎች ወይም መግለጫዎች አለመያዛቸው ሲረጋገጥ በዚህ አንቀጽ መሰረት ህትመቱ እንዲካሄድ ይደረጋል።

45.3 የምርት መረጃው የተሟላ ወይም ትክክለኛ ባልሆነበት ወቅት፣ አቅራቢው ለግዥ ፈፃሚው አካል ያልተሟሉትን ወይም የተዘለሉትን በመግለጽ በምርት መረጃው ውስጥ ስለሚጨመሩ ወይም ስለሚሻሻሉ ሁኔታዎች ወዲያውኑ ያሳውቃል።

45.4 አቅራቢው ለግዥ ፈፃሚው አካል ከሮያሊቲ ክፍያ ነፃ የሆነ የምርት መረጃ ለመጠቀምና በስራ ላይ ለማዋል፣ እንዲሁም በውስጡ ያሉትን ማንኛውንም ዕቃዎችና አገልግሎቶች በየጊዜው ለግዥ ፈፃሚው አካል ይሰጣል። የግዥ ፈፃሚው አካል በዚህ ንዑስ አንቀጽ ወይም በዚህ ውል በተቀመጠው መሰረት ለአቅራቢው ምንም አይነት የምርት መረጃን የማሳየት ወይም የማስተዋወቅ ሙብት ላይሰጠው ይችላል።

45.5 የግዥ ፈፃሚው አካል ለራሱ ጥቅም በሚያመች መንገድ በአቅራቢው የተሰጠውን የምርት መረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ በኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የውስጥ ግንኙነት በኤሌክትሮኒክስ መልክ ወይም በመንግስት አካላት ድረ ገጽ ወይም በማንኛውም ሚዲያ ወይም የመንግስት ካታሎግ ውስጥ እንዲወጣ የማድረግ መብት አለው።

45.6 እንደዚህ ያለው የምርት መረጃ በግዥ ፈፃሚው አካል በኤሌክትሮኒክስም ሆነ በሌላ መንገድ በህትመት ይፋ ከመውጣቱ በፊት፣ አቅራቢው እንዲያጸድቀው ይሰጠዋል። አቅራቢው እንዲያጸድቀው የሚሰጠውን ህትመት አላስፈላጊ ለሆነ ጊዜ ማዘግየት የለበትም። አንዳንድ ጥርጣሬዎችን ለማስወገድ ሲባል በዚህ ንዑስ አንቀጽ ወይም በዚህ የውል ስምምነት መሰረት አቅራቢው የግዥ ፈፃሚው አካል የምርት መረጃውን በማንኛውም የአገልግሎት ካታሎግ እንዳያወጣ የማስገደድ ሙብት አይኖረውም።

45.7 በአንቀጽ 42 እና 45.8 መሰረት በቀረቡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ምክንያት ለሚነሱ ማንኛውም አይነት ዕዳዎች፣ ኪሳራዎች፣ ክፍያዎች፣ ወጪዎች፣ አቤቱታዎች፣ ወይም የፍርድ ሂደቶቸ ወይም የግዥ ፈፃሚውን አካል

ዕቃዎችና አገልገሎቶች በመንግስት ካታሎግ ላይ ይፋ በማውጣቱ ምክንያት ለሚከሴቱ ማናቸውም ወጪዎች አቅራቢው ለመካስ ተስማምተዋል፡፡

45.8 ከላይ በንዑስ አንቀፅ 45.7 የተመለከተው ቢኖርም አቅራቢው በግዥ ፈፃሚው አካል ፈቃደኝነት ወይም ግድየለሽነት ለሚፈጠሩ ማንኛቸውም የተሳሳቱ የዕቃዎችና አገልገሎቶች መግለጫዎች ወይም ዕቃዎችና አገልገሎቶችን ከማስተዋወቅ ጋር በተያያዘ በግዥ ፈፃሚው አካል ለሚፈጠሩ ችግሮች አቅራቢው ካሳ የመክፈል ሀላፊነት የለበትም፡፡

## 46. *የሂሳብ አያያዝ፣ ቁጥጥርና ኦዲት*

46.1 አቅራቢው በዚህ ውል መሠረት ለሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች አለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝ መርሆችን የተከተለ ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዝገቦች መያዝ ይኖርበታል፡፡ የሂሳብ መዝገቦቹ የዕቃዎቹን ዝርዝርና ዋጋዎች በግልጽ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፡፡

46.2 የፌዴራል ዋና ኦዲተርና የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን ኦዲተሮች በየጊዜው የግዥውን ኢኮኖሚያዊ ብቃትና ጥራት ለማረጋገጥ ሰነዶችን ሊመረምሩ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ አቅራቢው እንደአስፈላጊነቱ የፅሑፍ ማብራሪያዎች እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል፡፡ አቅራቢው ከዚህ ውል ሁኔታዎች ጋር በማያያዝ ሥልጣን በተሰጠው አካል የሙስናና ሌሎች ማጣራቶች ሲደረጉ ሙሉ ትብብር ማድረግ አለበት፡፡

## 47. *የመረጃ (ዳታ) አጠባበቅ*

47.1 አቅራቢው የመረጃ ጥበቃ ህጐች በሚፈቅዱት መሠረት ውሉን መፈፀም አለበት፡፡ አቅራቢው በተለይ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተስማምቷል፡፡

(ሀ) አስፈላጊ የሆኑ ቴክኒካዊና ድርጅታዊ የመረጃ ጥበቃ ሥርዓቶችን ለማደራጀት፤

(ለ) የውሉን ሁኔታዎች ሲያስፈጽም በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ስም የግል መረጃዎችን መጠቀም የሚችለው ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ትዕዛዝ (ፈቃድ) ሲያገኝ ብቻ መሆኑን፣

(ሐ) በዚህ አንቀጽ በተመለከቱት ግዴታዎች መሠረት አቅራቢው የተጠየቁትን ፍላጎቶች የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የአቅራቢው ሰነዶች ኦዲት እንዲያደርግ ለመፍቀድና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማቅረብ ተስማምቷል፡፡

47.2 በአቅራቢው፤ በሠራተኞቹ ወይም በወኪሎቹ አማካኝነት ለሚከሰት የመረጃ መውደም፤ መጥፋት ወይም መጎዳት፤ እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖች ከተስማሙበት ውጭ ፈቃድ ሳያገኙ የግለሰብ ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሰው የግል መረጃ በመጠቀማቸው ምክንያት በግዥ ፈፃሚው አካል ላይ ለሚደርስበት ጉዳቶች፣ ወጪዎችና ዕዳዎች ካሣ ለመክፈል አቅራቢው ተስማምቷል፡፡

## 48. *የቀረቡ ዕቃዎች መጠንና ዋጋን የተመለከተ መግለጫ*

48.1 በተዋዋዩ ባለስልጣን ወይም ማንኛውም የግዥ ተቋም የሚጠየቅ ከሆነ አቅራቢው በውሉ መሰረት በተጠናቀቀው አመት ውስጥ ያቀረባቸውን እቃዎችና አገልግሎቶች ወይም ውሉ የሚቋረጥ ከሆነ ውሉ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ እስከተቋረጠበት ቀን ድረስ ያቀረባቸውን እቃዎችና አገልግሎቶች የሚገልፅ የተሟላ መግለጫ ውሉ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ በእያንዳንዱ ሩብ አመት ወይም ውሉ ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለማዕቀፍ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ወይም ገዥው ተቋም ማቅረብ አለበት፡፡ መግለጫው በዚህ ውል መሰረት እቃዎቹን እና ተያያዥ

አገልግሎቶችን ያቀረበላቸውን ተዋዋይ ባለስልጣን ወይም ማንኛውም ገዢ ተቋም ትክክለኛ ማንነት የሚገልጽ ዝርዝር መያዝ አለበት። የመግለጫው ፎርማትና የዝርዝር ይዘቱን በተመለከተ በተዋዋዩ ባለስልጣን ወይም ማንኛውም ገዥ ተቋም እና በአቅራቢው መካከል በፅሁፍ ስምምነት ይደረግበታል።

48.2 አቅራቢው ውሉ በሚፈፀምበት ቀን ወይም ከዚያ በኋላ ለማንኛውም የማዕቀፍ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ወይም ገዥ ተቋም በእርሱ የቀረቡ እቃዎችና አገልግሎቶች መጠንና ዋጋ የያዘ ትክክለኛና ወቅታዊ መዝገብ እነዚህን እቃዎችና አገልግሎቶች ያቀረበለትን የማዕቀፍ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤትወይም ማንኛውም ገዥ ተቋም ትክክለኛ ማንነት ከሚገልፅ ዝርዝር ጋር በመደበኛ የስራ ቦታው ማስቀመጥ አለበት። የማዕቀፍ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ወይም ማንኛውም ገዥ ተቋም እና በአቅራቢው መካከል ማንኛውንም የኦዲት ሂደት በተመለከተ በመንግስት ኤሌክትሮኒክ የግዥ ሥርዓት የሚደረግ ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕቀፍ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤትወይም ማንኛውም ገዥ ተቋም በቅድሚያ ቀጠሮ በመያዝ በመደበኛ የስራ ሰአቶች ወደ አቅራቢው መደበኛ የስራ ቦታ የመግባት እና የማዕቀፍ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤትወይም ማንኛውም ገዥ ተቋም በአቅራቢው የቀረበ ማንኛውም መግለጫ ትክክለኛና የተሟላ መሆኑን ለማጣራት በአቅራቢው መዝገቦች ላይ ምርመራ የማድረግ መብት አለው።

## 49. *ክለሳ*

49.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ባለሥልጣን በሚጠይቀው መሠረት በዚህ የውል ሁኔታዎች ከቀረቡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች በተገናኘ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የእርካታ ደረጃ ለማየት አቅራቢው በኤሌክትሮኒክስ ሠርዓት ወይም በአካል በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ቶ የውይይቱ ተካፋይ መሆን ይጠበቅበታል። በውይይቱ ላይ የሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ከፍተኛ ባለሙያዎችና ሌሎች ሠራተኞች ተሳታፊ ይሆናሉ። ሁለቱም ወገኖች የውይይት አጀንዳ በስምምነት ያዘጋጃሉ።

## 50. *የውል ማስከበሪያ ዋስትና*

50.1 አቅራቢው አሸናፊነቱ ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ባሉት አሥራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ የውል ማስከበሪያ ዋስትና መጠኑ በልዩ የውል ሁኔታዎች የተጠቀሰውን ዋስትና በማቅረብ ውል ይፈርማል።

50.2 የውል ማስከበሪያ ዋስትናው ገንዘብ አቅራቢው የውል ግዴታዎችን መወጣት ሲያቅተው በግዥ ፈፃሚው አካል ላይ ለሚደርሰው ማንኛውም ኪሣራ በካሣ መልክ ይከፈላል።

50.3 የውል ማስከበሪያ ዋስትናው በልዩ የውል ሁኔታዎች በተጠቀሰው የገንዘብ መጠን እንደተጫራቹ ምርጫ ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ፣ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተር ኦፍ ክሬዲት መቅረብ አለበት።

50.4 በልዩ የውል ሁኔታዎች በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የአቅራቢው የውል ግዴታዎችና ሌሎች የዋስትና ጉዳዮች መጠናቀቃቸው ከተረጋገጠ ከ 28 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የውል ማስከበሪያ ዋስትናውን ለአቅራቢው ይመልስለታል።

50.5 ከላይ በንዑስ አንቀጽ 50.2 የተመለከተው ቢኖርም በውል አፈፃፀም ግዴታዎች ያልተሟሉ ሁኔታዎች ቢኖሩም እንኳ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ያልተሟሉት ጉዳዮች በአቅራቢው ምክንያት አለመሆኑን ካረጋገጠ የውል ማስከበሪያ ዋስትናው ለአቅራቢው ይመለሳል።

50.6 በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 50.5 መሠረት ከውል ማስከበሪያ ዋስትና ለአቅራቢው መመለስ ሂደት ጋር በተያያዘ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እጁ ላይ ያሉ ሰነዶች ለመንግሥት የግዥና ንብረት ባለሥልጣን ወይም ሌሎች ሕጋዊ አካላት ማስረከብ ሲኖርበት ሰነዶቹን ማስረከብ ይኖርበታል፡፡

### ረ. ውል አፈፃፀም

## 51. *የአቅርቦት ወሰን*

51.1 የሚቀርቡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች በልዩ የውል ሁኔታዎች በተገለፀው የፍላጐት መግለጫ መሠረት ይሆናል፡፡

51.2 በውሉ ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር በውሉ ውስጥ በግልጽ ባይጠቀስም ለዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ ምንነት የነዚህ ያልተጠቀሱት ዕቃዎች መኖር ለዋናዎቹ ዕቃዎችና አገልግሎቶች አሰጣጥና አፈፃፀም አስፈላጊ መሆናቸው ከታወቀ በውሉ ውስጥ እንደተጠቀሰ ይቆጠራል፡፡

## 52. *ዝርዝር መግለጫዎችና ደረጃዎች*

52.1 የቴክኒክ መግለጫዎችና ንድፎች

(ሀ) በአቅራቢው የሚቀርቡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች በውሉ የተመለከተውን የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

(ለ) አቅራቢው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወይም በወኪሉ የተዘጋጀውን ንድፍ፣ መረጃ፣ ስዕል፣ ዝርዝር መግለጫ ወይም ሌሎች ማሻሻያዎችን ወይም በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ስም የተነደፈ ወይም የቀረቡ ዝርዝር መግለጫዎችን ማስታወቂያ በመስጠት ኃላፊነት ላይወስድ ወይም ላይቀበላቸው ይችላል፡፡

(ሐ) በዚህ ውል መሠረት የሚቀርቡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች በፍላጐቶች መግለጫ ውስጥ ከተጠቀሰው ደረጃ ጋር መጣጣም አለባቸው፡፡ በመግለጫው ውስጥ የተጠቀሰ ደረጃ ከሌለም ደረጃው ከዕቃዎች መነሻ ሀገር ጋር የተጣጣመ ወይም የላቀ መሆን አለበት፡፡

52.2 በውሉ ውስጥ ስለአፈፃፀሙ ሕጐችና ደረጃዎች ተጠቅሰው ከሆነ በፍላጐት መግለጫ ውስጥ የተጠቀሱት ሕጐችና ደረጃዎችም ከነዚሁ ጋር የተጣጣመ መሆን አለባቸው፡፡ በውል አፈፃፀም ወቅት ማንኛውም የሕጐችና የደረጃዎች ለውጦች በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 14 ጋር መጣጣማቸው እየታየ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

## 53. *ርክክብ* (*ማስረከብ*)

53.1 አቅራቢው በልዩ የውል ሁኔታ ወይም በግዥ ትዕዛዝ በተመለከተው ወይም ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተስማሙበት ቦታ ዕቃዎቹን ማስረከብ አለበት፡፡

53.2 ርክክብ የሚፈፀመው ዕቃዎቹ በመረከቢያ ቦታው ደርሰው ከጭነት ሲራገፍና በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተመደበ ተወካይ ወይም ሠራተኛ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፡፡ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ዕቃዎቹን የሚረከብ ሠራተኛ ወይም ተወካይ በመረከቢያው ቦታው ተገኝቶ እንዲረከብ ይመድባል፡፡

53.3 በልዩ የውል ሁኔታ ንዑስ አንቀጽ 53.1 ከተገለፀው ውጭ የግዥ ፈፃሚው አካል ዕቃዎቹ በአስቸኳይ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲቀርብለት ሲፈልግ በዚህ ምክንያት አቅራቢው የሚያጋጥሙትን ተጨማሪ ወጪዎች ለግዥ ፈፃሚው አካል ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

53.4 ከርክክብ ቀን በፊት ወይም በከፊል ለሚደርሱ ዕቃዎች ርክክብ ለመፈፀም በቅድሚያ የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ስምምነት ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

53.5 በልዩ የውል ሁኔታዎች በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር የገቢና ወጪ ዕቃዎች ፈቃድ የማውጣትና ፈቃዱን በማግኘት ሂደት ለሚፈጠሩ መዘግየቶች ኃላፊነት የአቅራቢው ነው፡፡

53.6 የሚቀርቡት ዕቃዎች ከኢትዮጵያ ውጭ ሲሆን አቅራቢው የዕቃዎቹን መነሻ ሀገር ትክክለኛ መረጃ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ከግዥው ጋር የተያያዙ ቀረጦችና ታክሶች የመክፈል ኃላፊነትም የአቅራቢው ይሆናል፡፡

53.7 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ዕቃዎቹን በተከፋፈለ ሁኔታ ለመረከብ ሲስማማ እያንዳንዱን የተከፋፈለ ርክክብ በሚያሳይ መልክ በአንድ ውል ይካተታሉ፡፡ አቅራቢው አንዱንም የተከፋፈለ ርክክብ ማስረከብ ቢያቅተው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ምርጫ ሙሉ አቅርቦቱን ላይረከብ ይችላል፡፡

53.8 የዕቃዎቹ ማጓጓዣ ወጪ ለብቻው እንዲሆን ሲፈለግ ወይም በውል ዋጋ ላይ በተደረጉ ቅናሾች ምክንያት ሸቀጦቹ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለማጓጓዝ ሲፈለግ ይህንኑ የሚያረጋግጥ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ኃላፊነት በተሰጣቸው ኃላፊዎች የተፈረመ የፅሑፍ መረጃ መኖር አለበት፡፡

በአስቸኳይ ሁኔታዎች ምክንያት በፅሑፍ የተረጋገጠ መረጃ ሳይኖር ሲቀር ይህንኑ የሚያረጋግጥ በተዋዋይ ወገኖች በተቻለ ፍጥነት የተዘጋጀ የፅሑፍ ማስረጃ መኖር አለበት፡፡

53.9 በአቅራቢው መቅረብ ስላለባቸው የጭነት ሁኔታዎችና ሌሎች ሰነዶችን በተመለከተ በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በተገለፀው መሰረት ይሆናል፡፡

## 54. የማስረከቢያ ጊዜ

54.1 የማስረከቢያ ጊዜ በግዥ ማዘዣው መሠረት (ወይም በሌላ መንገድ በሁለቱ ወገኖች መካከል በተደረገ ስምምነት) ይወሰናል፤ ሆኖም በግልጽ ስምምነት የተደረገበት ጊዜ ከሌለ የማስረከቢያ ጊዜው የግዥ ማዘዣው በተሰጠ በ 14 ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

54.2 የማስረከቢያ ጊዜው በሁለቱ ወገኖች መካከል በግዥ ማዘዣው መሠረት ስምምነት ካልተደረገበት ወይም በሌላ መንገድ ስምምነት ካልተደረገበት (የግዥ ማዘዣው በተሰጠ በ 14 ቀናት ውስጥ በግልጽ የተደረገ ስምምነት የተደረገበት የማስረከቢያ ጊዜ በሌለበት ሊፈጠር የሚችለውን ጥርጣሬ ለማስቀረት) የማዕቀፍ ውል ፈጻሚው መ/ቤት ወይም የማንኛውም ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት መብት ወይም የመፍትሄ እርምጃ የመውሰድ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የማስረከቢያ ጊዜው አስፈላጊ ግዴታ ሆኖ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

54.3 ማንኛውም ወገን ከሶስት ቀናት የማያንስ ማስጠንቀቂያ በቅድሚያ ለሌላው ወገን በመስጠት ስምምነት የተደረገበትን የማስረከቢያ ጊዜ መቀየር ይችላል፡፡

54.4 አቅራቢው በንዑስ አንቀጽ 54.1 መሠረት ስምምነት በተደረገበት ጊዜ ውስጥ ማንኛውንም ዕቃ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ካላስረከበ የማዕቀፍ ስምምነት ውል የሚገባው መ/ቤት ወይም ማንኛውም ሌላ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት በዚሁ የውል ግዴታ ጥሰት ምክንያት የማንኛውንም ሌላ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ የግዥ ማዘዣና ግዥ መስረዝና ለሌሎች ምትክ ዕቃዎች ግዥ በውል ሰጪው ወይም በማንኛውም ሌላ ግዥ ፈጻሚ አካል ለአቅራቢው ሊከፈል ይችል ከነበረው በላይ የወጣውን ማንኛውንም ወጪ ማስመለስ ወይም ወጪውን ለማካካስ ማንኛውንም ሌላ ተገቢ አማራጭ መጠቀም ይችላል፡፡ አቅራቢው

ለሶስት ተከታታይ ጊዜ በንዑስ አንቀጽ 54.1 መሠረት ስምምነት በተደረገበት ጊዜ ዕቃውን ካላስረከበ ተዋዋዩ ባለሥልጣን ወይም ማንኛውም ሌላ ግዥ ፈጻሚ አካል በንዑስ አንቀጽ 22 መሠረት ውሉን ማቋረጥ ይችላል።

## 55. *ማሸግ፣ ምልክት ማድረግና ሰነዶች*

55.1 በውሉ በተመለተው መሠረት አቅራቢው ዕቃዎቹ በሚጓጓዙበት ወቅት ጉዳት እንዳይደርስባቸው ወይም እንዳይሰበሩ፣ መጠኑ ያለፈ ሙቀትና ቅዝቃዜ እንዳይጐዳቸው፣ በጉዞ ወቅት ጨውና እርጥበት እንዲሁም በክፍት መጋዘን ጉዳት እንዳይደርስባቸው ዕቃዎቹ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ መታሸግ አለባቸው። በእሽግ ጊዜ የታሸጉት ዕቃዎች መጠንና ክብደት፣ እንዲሁም በተራራቁ ማስረከቢያ ቦታዎች መካከል የሚያጋጥሙ ችግሮችና የከባድ ዕቃዎች አያያዝ አገልግሎት የሌሉባቸው ሩቅ ማስረከቢያ ቦታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

55.2 በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር የሚከተሉት መረጃዎች በእሽጉ ውጫዊ አካል ላይ መታየት (መለጠፍ) አለባቸው።

(ሀ) የዕቃዎቹ መግለጫ (ዓይነት)፣ የዕቃዎቹ ክብደትና የግዥ ፈፃሚ መ/ቤተት የግዥ ትዕዛዝ ቁጥር፣
(ለ) በእሽጉ ውስጥ ያለው የዕቃዎች ብዛት፣
(ሐ) በመጋዘን አያያዝ ላይ የሚኖር ልዩ መመሪያ፣
(መ) የዕቃዎቹ የመጨረሻ መጠቀሚያ ቀን (የሚኖር ከሆነ)፣
(ሠ) የባች (batch) መለያ ቁጥር
(ረ) የዕቃዎቹ አምራች ስምና የአቅራቢው ስም
(ሰ) ዕቃው የተመረተበት ቀን
(ሸ) የአጠቃቀም ሁኔታ
(ቀ) የምርት ቦታ

## 56. *ዕቃዎችን ስለመለየት*

56.1 ዕቃዎቹን ለመለየት የሚረዱ ምልክቶች፣ ሰዎች፣ መለያ ቁጥሮችና ሌሎች መረጃዎች ወይም የዕቃው መነሻ ሀገር፣ በመንግሥት ወይም በሌላ መ/ቤት ኢንስፔክሽን የተካሄደባቸው ሪፖርቶችና የመሳሰሉት በሙሉ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መሰጠት አለባቸው።

## 57. *የዕቃ ማሸጊያ ኮንቴነሮችና ሳጥኖች*

57.1 በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እንዲቆይ ካልታዘዘ በስተቀር አቅራቢው ዕቃ ታሽጐባቸው የመጡት ኮንቴይነሮችና ሳጥኖች በማስረከቢያ ሰነዱ ላይ ከተመለከተው የርክክብ ቀን ጀምሮ ባሉት 21 ቀናት ውስጥ መመለስ አለበት። በአቅራቢው ያልተመለሱ ባዶ ኮንቴይነሮች በግዥ ፈፃሚው አካል ሊመለሱ ወይም እንደአመቺነቱ የግዥ ፈፃሚው አካል በመረጠው ቦታ ሊቀመጡ ይችላሉ። በግዥ ፈፃሚው አካል ኮንቴይነሮቹን ለመመለስ ወይም ለማስቀመጥ የወጡት ወጪዎች በሙሉ የአቅራቢው ኃላፊነት ይሆናሉ።

## 58. ንብረትና ስጋት

58.1 ርክክብ ቢፈፀምም የዕቃዎቹ የውል ዋጋ እስኪከፈል ድረስ የዕቃዎቹ ባለቤትነት ከአቅራቢው አይተላለፍም።

58.2 ዕቃዎቹ በርክክብ ቦታ ቢደርሱም ባይደርሱም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች ኃላፊነት የአቅራቢው ይሆናል።

## 59. መሣሪያዎች

59.1 ከግዥ ትዕዛዙ ጋር በተገናኘ ማናቸውም በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለአቅራቢው የተሰጡ መሣሪያዎች፣ ንድፎች፣ ዝርዝሮች ወይም ሌሎች መረጃዎች ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ስጋቶች ኃላፊነት የአቅራቢው ቢሆንም ንብረትነታቸው ግን የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሆኖ ይቆያል። አቅራቢው ይህንኑ የግዥ ትዕዛዝ ለማስፈፀም ብቻ ይጠቀምባቸዋል። በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እንዲመለስ ሲጠየቅም አቅራቢው ወዲያውኑ መመለስ አለበት።

59.2 ማናቸውም ውሉን ለማስፈፀም የሚጠቀምባቸውን የአቅራቢው የሆኑ መሣሪያዎችን ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የዕቃዎቹን ዋጋ ከፍሎ ባለቤትነቱን ለማስተላለፍ የፅሑፍ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር ባለቤትነቱ የአቅራቢው ሆነው ይቆያሉ።

## 60. ጥራት

60.1 የሚቀርቡት ዕቃዎች አዲስና በፍላጐት መግለጫው በተመለከተው መሠረት ወይም ከዚህ በፊት በዋቢነት ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከቀረበው ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው። በሌላ ሁኔታ ስምምነት ካልተደረሰ በስተቀር ዕቃዎቹ ሁሉንም ደረጃዎች፣ ዝርዝሮችና ሁኔታዎች ያሟሉና ለተፈለገው ሥራ ጥሩ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ መሆን አለባቸው። እነዚህን ጥርጣሬዎች ለማስወገድ ይቻል ዘንድ አቅራቢው ዕቃዎቹ ያልተጣሉ ወይም ከዚህ በፊት ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ዋስትና መስጠት አለበት።

60.2 አቅራቢው ስለሚቀርቡት ዕቃዎች የግዥ ትዕዛዝ ከመሰጠቱ በፊትም ይሁን በኋላ የተሰጡት መግለጫዎች በሙሉ ትክክለኛና በሙያ የተደገፉ ለመሆናቸው ማረጋገጥና ዋስትና (Warranty) መስጠት ይኖርበታል።

60.3 አቅራቢው ከሚቀርቡት ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ከአምራች፣ ከሌላ አቅራቢ ወይም ከሌላ ሶስተኛ ወገን የሚነሱ የመብት ጥያቄዎችን ሀላፊነት የሚወስድ መሆኑን ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ዋስትና ወይም ጋራንቲ መስጠት ይኖርበታል።

## 61. ምርመራዎችና ሙከራዎች

61.1 አቅራቢው በፍላጐቶች መግለጫ ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት በራሱ ወጭና በግዥ ፈጻሚ መ/ቤትላይ ምንም ወጭ ሳያስከትል በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት በእቃዎቹና በተያያዥ አገልግሎቶች ላይ ምርመራዎችንና ሙከራዎችን ማካሄድ አለበት።

61.2 በልዩ የውል ሁኔታ በሚገለጸው መሠረት ምርመራዎችና ሙከራዎች በአቅራቢው ግቢ ውስጥ ወይም በንዑስ የውል ስምምነት አቅራቢ ግቢ፣ ወይም በማስረከቢያ ቦታና ወይም በዕቃዎቹ የመጨረሻ መድረሻ ወይም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ በሌላ ቦታ ይደረጋሉ። በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 61.3 መሠረት ምርመራዎችና ሙከራዎችን በአቅራቢው ወይም በንዑስ የውል ስምምነት አቅራቢው ቅጥር ግቢ የሚደረጉ ሲሆን ሁሉንም አስፈላጊ ሁኔታዎች እንዲሁም ንድፎች እና የምርት ዳታዎች ማግኘትን ጨምሮ በግዥ ፈጻሚው ላይ ምንም ክፍያ ሳይከተል ለሙከራ ዝግጁ ማድረግ አለበት።

61.3 በልዩ የውል ሁኔታ ላይ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር የግዥ ፈጻሚው ወይም ኃላፊነት የተሰጠው ወኪል በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 61.2 መሠረት ማንኛውንም የራሱን ወጭዎች ችሎ ኢንስፔክተሮች የሚያደርጉትን ሙከራ (ፍተሻ) መታዘብ ይችላል።

61.4 አቅራቢው የተጠቀሰውን ምርመራ/ሙከራ ለማካሄድ ሲዘጋጅ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በቂ ጊዜ በመስጠት ያስታውቃል። የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወይም ተወካዩ በምርመራ ወቅት ከመገኘት ጋር ተያይዞ ከአምራቹ ወይም ከሌላ ሶስተኛ ወገን ፈቃድ ወይም ስምምነት ማግኘት ሲያስፈልግ ይህን የማሟላት የአቅረቢው ሀላፊነት ይሆናል።

61.5 በቀረበው ጥያቄ መሠረት በአቅራቢው ላይ የሚያደርሰው ወጭ በእቃዎቹ ዋጋ ላይ የሚደመር ከሆነ የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት በውል ውስጥ ባይጠቅስም በእቃዎቹ ሁኔታና አፈጻጸም፣ በቴክኒካዊ ዝርዝሮች፣ በሕግና በውል በተጠቀሰው ደረጃ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ምርመራ ወይም ፍተሻ እንዲያደርግ አቅራቢውን መጠየቅ ይችላል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ በምረመራው/ሙከራው ሂደት ምክንያት የአምራቹ ወይም የአቅራቢው አፈፃፀም ላይ የተወሰነ መዘግየትን አስከትሎ ከሆነ በማቅረቢያና ማጠናቀቂያ ጊዜ ላይ ተመጣጣኝ የሆነ አስተያየት ሊደረግ ይችላል፡፡

61.6 አቅራቢው የሙከራውንና የምርመራውን ሪፖርት ለግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

61.7 የግዥ ፈጻሚው ምርመራውን ወይም ፍተሻውን የማያልፍ ወይም ከመዘርዝሮቹ ጋር የማይጣጣሙ ዕቃዎችን በሙሉ ወይም ከፊሎቹን ላለመቀበል ይችላል፡፡ በዚህ መሠረት ምርመራ ያላለፉ ዕቃዎችን አቅራቢው የመተካት ወይም የማስተካከልና በግዥው ፈጻሚው ላይ ምንም ወጭ ሳያስከትል ለድጋሚ ምርመራ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 61.4 መሠረት የግዥ ፈጻሚውን በማሳወቅ በድጋሚ ምርመራውን ማድረግ አለበት፡፡

61.8 እቃዎቹ ምርመራ ካለፉ እና/ወይም የፍተሻ መስፈርቱን ካሟሉ ወይም ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወይም ወኪሉ ከተገኙ ወይም በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 61.6 መሠረት ማንኛውም ዓይነት ሪፓርት ከቀረበ አቅራቢው ከማንኛውም የዋስትና ክፍያ እና ኃላፊነት ነፃ እንደሚሆን ተስማምቷል፡፡

## 62. *ዕቃዎችን አለመረከብ*

62.1 በአጠቃላይ የውል ሁኔታ ንዑስ አንቀጽ 62.4 የተመለከተው ቢኖርም የሚቀርቡት ዕቃዎች በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወይም እሱ በሚወክለው አካል በአጠቃላይ የውል ሁኔታ አንቀጽ 53 መሠረት መመርመር አለባቸው፡፡ በምርመራው ውጤት መሠረት ዕቃዎቹ በዚህ ውል የተመለከተውን የፍላጐት መግለጫ የማያሟሉ ከሆነ ወይም የተበላሹ ወይም የጥራት ጉድለት ያለባቸው ከሆነ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሊረከብ አይችልም፡፡

62.2 በአጠቃላይ የውል ሁኔታ ንዑስ አንቀጽ 62.4 የተመለከተው ቢኖርም የግዥ ፈጻሚው አካል ለአቅራቢው የሚከተሉትን ያሳውቀዋል፡፡

(ሀ) በቀረቡት ዕቃዎች ላይ ችግር መኖሩን በመግለፅ አቅራቢው ችግሮቹን በአስቸኳይ እንዲመረምር ማሳወቅ፣

(ለ) በቀረቡት ዕቃዎች ላይ በጉዞ ወቅት የመጠን ጉድለት ወይም የደረሰ ጉዳት ሲኖር ተዋዋይ ወገኖች በተስማሙት መሠረት ዕቃዎች ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 14 ቀናት ማሳወቅ፡፡

62.3 ከዕቃዎቹ መካከል መጠነኛ ማሳያ በዋቢነት ተወስዶ በማንኛውም መንገድ የዕቃዎቹ ሁኔታ ከውሉ የፍላጐት መግለጫ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሁሉንም ዕቃዎች ላይቀበላቸው ይችላል፡፡

62.4 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ዕቃዎቹን የተረከባቸው ቢሆንም እንኳን መብቱ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ በተለይም የዕቃዎቹ ርክክብ በመፈፀሙ ወይም እንስፔክሽን በመካሄዱ ወይም ክፍያ በመፈፀሙ ዕቃዎቹን እንደተቀበለ ማረጋገጫ ሊሆኑ ወይም ዕቃዎቹን ላለመመለስ ምክንያቶች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ የግዥ ፈፃሚው አካል ዕቃዎችን ያለመመለስ ወይም ያለመቀጠል መብቱ የሚያበቃው የዕቃዎቹን የውል ሁኔታዎች አጣርቶ ምንም አይነት የውል ጉድለት እንደሌለባቸው ካረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

62.5 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ያልተቀበላቸውን ዕቃዎች አቅራቢው በራሱ ወጪ በ14 ቀናት ውስጥ ማንሳት ይኖርበታል፡፡ አቅራቢው በዚሁ ጊዜ ዕቃዎቹን ማንሳት ካልቻለ የግዥ ፈፃሚው አካል በሚያመቸው መንገድ ዕቃዎቹን ለአቅራቢው ሊመልስለት ይችላል፡፡ በመመለስ ሂደት የሚኖሩ ስጋቶችና የማጓጓዝ ወጪዎች እንዲሁም ዕቃዎቹ መጋዘን ውስጥ የቆዩበት ጊዜ የመጋዘን ኪራይ ወጪ በአቅራቢው የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## 63. ጊዜ ስለማራዘም

63.1 በውሉ አፈፃፀም ሂደት በማንኛውም ጊዜ አቅራቢው ወይም ንዑስ የውል ሥምምነት አቅራቢ የዕቃዎቹን ርክክብ ወይም አገልግሎቶች አፈፃፀምን በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 53 መሠረት ለማጠናቀቅ የሚያስተጓጉሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት የችግሩ መንስኤዎችና ችግሩን ለመፍታት የሚወስደውን ጊዜ በመግለፅ በአስቸኳይ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማስታወቅ አለበት፡፡ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤትም ማስታወቂያውን እንደተቀበለ ሁኔታውን ገምግሞ በራሱ ፍላጎት የአቅራቢውን የአፈፃፀም ጊዜ ማራዘም ይችላል፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ተዋዋዮቹ የተራዘመውን ጊዜ ውሉን በማሻሻል ያፀድቁታል፡፡

63.2 በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 19 መሰረት በአስገዳጅ ሁኔታዎች ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ወይም በዚህ ንዑስ አንቀጽ 63.1 መሠረት የጊዜ ማራዘሚያ ካልተሰጠው በስተቀር አቅራቢው የውል ግዴታውን አፈፃፀም ቢያዘገየው በአንቀጽ 27 መሠረት የጉዳት ካሣ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 64. የአፈፃፀም መለኪያ

64.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በአቅራቢው የቀረቡትን ዕቃዎች በፍላጎት መግለጫው የተጠቀሰውን መስፈርት ወይም መስፈርቱ ካልተጠቀሰም ዕቃው መደበኛ የሙያ ደረጃ ማሟላት አለማሟላቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

64.2 በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተመለከቱት የግዥ ፈፃሚው መ/ቤቱ መብቶች ማንኛውም የመንግስት አካል ሊኖረው የሚገባ መብቶችና መፍትሔዎችን ያካተተ ይሆናል፡፡

64.3 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተዋዋይ ወገኖች የውሉን አፈጻጸም የተሳካ ለማድረግ መረጃዎችን በመለዋወጥና የአፈጻጸም መመዘኛ መስፈርቶችን በማዘጋጀት ተባብረው ይሰራሉ፡፡ እንደዚህ አይነት ስምምነቶች በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሲስተም ተመዝግበው ይቀመጣሉ፡፡

## ክፍል 8፡ ልዩ የውል ሁኔታዎች

ማውጫ


**ሀ. አጠቃላይ ሁኔታዎች.......................................................................1**

**ለ. ውል..................................................................................1**

**ሐ. የግዥ ፈፃሚው አካል ግዴታዎች...........................................................3**

**መ. ክፍያ...............................................................................4**

**ሠ. የአቅራቢው ግዴታዎች...................................................................4**

**ረ. የውል አፈፃፀም........................................................................4**

# ክፍል 8

## ልዩ የውል ሁኔታዎች

የሚከተሉት ልዩ የውል ሁኔታዎች አጠቃላይ የውል ሁኔታዎችን የሚያሟሉ ናቸው። በማንኛውም ጊዜ በልዩ የውል ሁኔታዎችና በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች መካከል ያለመጣጣም በሚኖርበት ጊዜ በዚህ ልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ውስጥ ከተጠቀሱት የበላይነት ይኖራቸዋል።

| አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች (አ.ው.ሁ) አንቀጽ መለያ | ልዩ የውል ሁኔታዎች | |
|---|---|---|
| **ሀ. አጠቃላይ ሁኔታዎች** | | |
| | የግዥ መለያ ቁጥር፡- *[የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ]* | |
| አ.ው.ሁ. 1.2 (ተ) | የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት *[የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ሙሉ ስም ይግባ]* | |
| አ.ው.ሁ. 1.2 (ፐ) | የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው *[የአቅራቢው ሙሉ ስም ይግባ]* | |
| አ.ው.ሁ. 6.3 (ሀ) | የንግድ ቃሎቹ ትርጉም የሚገለፁት በ_*[የንግድ ድርጅት ስም ይግባ]* | |
| አ.ው.ሁ. 6.3 (ለ) | የአለም አቀፍ የንግድ ቃሎች እትም *[የአለም አቀፍ የንግድ ቃሎች አመልከት ምሳሌ፡- የአለም አቀፍ የንግድ ቃሎች 2010]* | |
| **ለ. ውል** | | |
| አ.ው.ሁ. 7.1 (ቀ) | በአ.ው.ሁ አንቀጽ 7.1 ከተዘረዘሩት ሰነዶች በተጨማሪ የሚከተሉት ሰነዶች የውሉ አካል ናቸው።<br>ሀ.<br>ለ.<br>ሐ. | |
| አ.ው.ሁ. 7.3 | የግዥ ፈፃሚው አካል አድራሻ እንደሚከተለው ይሆናል። | |
| | ተወካይ /ኃላፊ | *[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስምና ሀላፊነት ይግባ]* |
| | | |
| | የመንገድ አድራሻ | *[የመንገድ ስም ይግባ]* |
| | ከተማ | *[የከተማ ስም ይግባ]* |
| | | |
| | አገር | |
| | ስልክ ቁጥር | *[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ]* |
| | ፋስክ ቁጥር | *[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የፋክስ ቁጥር ይግባ]* |
| | ኤ.ሜይል አድራሻ | *[ኢ.ሜይል አድራሻ ይግባ]* |
| | የአቅራቢው አድራሻ እንደሚከተለው ይሆናል | |
| | ተወካይ /ኃላፊ | *[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስምና ሀላፊነት ይግባ]* |
| | | |
| | የመንገድ አድራሻ | *[የመንገድ ስም ይግባ]* |
| | ከተማ | *[የከተማ ስም ይግባ]* |
| | | |

| | | |
|---|---|---|
| | አገር | [አገር ይግባ] |
| | ስልክ ቁጥር | [የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ] |
| | ፋስክ ቁጥር | [የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የፋክስ ቁጥር ይግባ] |
| | ኤ.ሜይል አድራሻ | [ኢ.ሜይል አድራሻ ይግባ] |
| አ.ው.ሁ. 7.5 | የውሉ ጊዜ: [የውል ጊዜ ይግባ] | |
| አ.ው.ሁ. 8.1 | ውሉ የሚገዛበት ህግ: [ውሉ የሚገዛበት ህግ ይግባ] | |
| አ.ው.ሁ 9.1 | የውል ቋንቋ: [ቋንቋ ይግባ] | |
| አ.ው.ሁ 10.1 | ለግዥ ፈፃሚው አካል ማስታወቂያ የሚላከው በሚከተለው አድራሻ ነው | |
| | ግዥ ፈፃሚው አካል | [የግዥ ፈፃሚ አካል ስም ይግባ] |
| | ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው | [ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስም ይግባ] |
| | | [ቢሮ ቁጥር ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ] |
| | | |
| | የመንገድ አድራሻ | [የመንገድ ስም ይግባ] |
| | ከተማ | [የከተማ ስም ይግባ] |
| | | |
| | አገር | ኢትዮጵያ |
| | የስ. ቁጥር | [የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ] |
| | የፋስክ ቁጥር | [የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የፋክስ ቁጥር ይግባ] |
| | ኢ.ሜይል አድራሻ | [ኢ.ሜይል አድራሻ ይግባ] |
| | ለአቅራቢው ማስታወቂያ የሚላከው በሚከተለው አድራሻ ነው | |
| | አቅራቢው | [የአቅራቢው ስም ይግባ] |
| | ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው | [ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስም ይግባ] |
| | የቢሮ ቁጥር | [ቢሮ ቁጥር ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ] |
| | | |
| | የመንገድ አድራሻ | [የመንገድ ስም ይግባ] |
| | ከተማ | [የከተማ ስም ይግባ] |
| | | |
| | አገር | ኢትዮጵያ |
| | የስ. ቁጥር | [የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ] |
| | ሀ.<br><br>ለ.<br><br>ሐ. ቁጥር | [የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የፋክስ ቁጥር ይግባ] |
| | ኤሜይል አድራሻ | [ኢ.ሜይል አድራሻ ይግባ] |
| አ.ው.ሁ. 14.2 | ኃላፊነትን ለሌላ ማስተላለፍ መቻል አለመቻሉ ይገለጽ። | |
| አ.ው.ሁ. 17.1 | የማስረከቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ በህጐችና ደንቦች ላይ ለውጦች ቢኖሩ የውሉን አጠቃላ ዋጋ መጨመር ወይም መቀነስ ስለመቻል አለመቻላቸው ይገለጽ | |

| | |
|---|---|
| አ.ው.ሁ 18.1 | ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚቀርቡ ዕቃዎች አቅራቢው ከሚከተሉት በስተቀር አስፈላጊ የሆኑ ታክሶችና የጉምሩክ ግዴታዎች፣ የንግድ ፈቃድ ክፍያዎችና ተመሳሳይ ግዴታዎችን የማሟላት ኃላፊነት አለበት። [አቅራቢው የማይጠየቅባቸው ጠቃሚ የሆኑ የታክሶችና የጉምሩክ ግዴታዎች ዝርዝር ይግባ]<br>ሀ.<br>ለ.<br>ሐ. |
| አ.ው.ሁ 18.2 | ከኢትዮጵያ ውስጥ ለሚቀርቡ ዕቃዎች አቅራቢው ከሚከተሉት በስተቀር አስፈላጊ የሆኑ ታክሶች፣የንግድ ፈቃድ እቃዎችና ውሎችን ተመሳሳይ ግዴታዎች የማሟላት ኃላፊነት አለበት። [አቅራቢው የማይጠየቅባቸው ጠቃሚ የሆኑ የታክሶችና የጉምሩክ ግዴታዎች ዝርዝር ይግባ]<br>ሀ.<br>ለ.<br>ሐ. |
| አ.ው.ሁ 25.3 | ዋስትናው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ: [ዋስትናው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ይግባ] |
| አ.ው.ሁ 25.5 | የመጠገኛና የመተኪያ ጊዜ: [ብልሽት ያለባቸው እቃዎች የመጠገኛና የመተኪያ ጊዜ ይገለፅ] |
| አ.ው.ሁ 26.5 | አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ፣<br><br>(i) ☐ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን የምንጠቀም ከሆነ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት በተቋቋሙ እና በተገቢው መ/ቤት ዕውቅና በተሰጣቸው የግልግል ዳኝነት አካላት በኩል መሆን አለበት።<br><br>(ii) ☐ አለመግባባት ሲፈጥር...........አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን በመጠቀም ይፈታል።<br><br>(iii) ውል ፈፃሚ አካላት በሚገቡት ውል ግልግል ዳኝነት አካሉ፣<br><br>ተፈፃሚ የሚሆነውን ሕግ፣ የዳኝነት አካሉ ስብጥር፣<br><br>ዳኞች የሚመረጡበት መንገድ፣ እና ሌሎች የስነ<br><br>ስርዓት ድንጋጌዎች ይካተቱ። |
| **ሐ. የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግዴታዎች** | |
| አ.ው.ሁ 31.1 | አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አቅራቢው የሚከተሉትን ፍላጐቶች ለማሟላት እንዲችል ድጋፍ/እገዛ ያደርጋል።<br>ሀ.<br>ለ.<br>ሐ. |
| **መ. ክፍያ** | |
| አ.ው.ሁ 33.9 | የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸውን ዕቃዎች ዝርዝር ይገለጽ። [ዝርዝር ይግባ]<br>ሀ.<br>ለ. |

| | |
|---|---|
| አ.ው.ሁ 33.14 | የዋጋ ማስተካከያ አፈጻጸም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ [ተግባራዊ የሚሆነው ክፍልፋይና ቀመር ይግባ]<br>ሀ.<br>ለ. |
| አ.ው.ሁ 34.4 | የግዥ ፈፃሚው አካል የውል ዋጋውን ለአቅራቢው የሚከፍለው የጊዜ ገደብ ነው [የቀናት ብዛት ይግባ]፡፡ |
| አ.ው.ሁ 34.5 | ከሀገር ውስጥ ለቀረቡት ዕቃዎች ለአቅራቢው ሁሉም ክፍያየሚከፈለው በኢትዮጵያ ብር ነው፡፡<br>ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚቀርቡ ዕቃዎች ለአቅራቢው ክፍያ የሚከፍለው በ____ [የመገበያያ ገንዘብ አይነት ይግባ] ይሆናል፡፡ |
| ሠ. የአቅራቢው ግዴታዎች | |
| አ.ው.ሁ 42.1 (ለ) | አጠቃላይ የኃላፊነት መጠን _____ ነው [አጠቃላይ የኃላፊነት መጠን ይግባ] |
| አ.ው.ሁ 44.1 | የመድን ዋስትና ሽፋን የሚሆነው በሚከተለው የአለም አቀፍ የንግድ ቃል (ኢንኮተርም) መሠረት ይኖራል፡፡ |
| አ.ው.ሁ 50.1 | የውል ማስከበሪያ ዋስትና መጠን [የውል አፈጻጸም ዋስትና  መጠን ይመልከት]_____ ይሆናል |
| አ.ው.ሁ 50.3 | ተቀባይነት ያላቸው የውል ማስከበሪያ ዋስትና ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው [በግዥ ፈፃሚው አካል ተቀባይነት ያላቸው የውል ማስፈፀምያ ዋስትና ስምና መግለጫ  ይግባ]<br>ሀ.<br>ለ.<br>ሐ.<br>የገንዘቡ ዓይነት_____ ይሆናል፡፡ [የውል ዋስትና መገበያያ ገንዘብ አመልክት] |
| አ.ው.ሀ 50.4 | የውል ማስከበሪያ ዋስትና የሚለቀቀው (ነፃ የሚሆነው) [ የውል ማስከበሪያ ዋስትና በምን አይነት ሁኔታ ነፃ እንደሚሆን ይግባ] |
| ረ. የውል አፈፃፀም | |
| አ.ው.ሁ 51.1 | የአቅርቦት ወሰን የሚተረጐመው: [ክፍል 6፣ የፍላጎቶች መግለጫ ወይም የአቅርቦት ወሰን የት እንደሚተረጎም ይግባ] |
| አ.ው.ሁ 53.1 | አቅራቢው ዕቃዎቹን የሚያስረክብበት ቦታ: [የማስረከብያ ቦታ ይዘርዝር] |
| አ.ው.ሁ 53.5 | የገቢና ወጪ ዕቃዎች ፈቃድ የማግኘት ኃላፊነት የማን እንደሆነ ይገለጽ፡፡ |
| አ.ው.ሁ 53.9 | በአቅራቢው መቅረብ ያለባቸው የማጓጓዣና ሌሎች ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ [ኢንኮተርምን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው፡፡ አስፈላጊ ካልሆኑ መሰረዝ ይቻላል፡፡]<br>• ዋናውና ሁለት ኮፒ ኤይርወይ ቢል ወይም ቢል ሆፍ ላዲንግ<br>• የእሽጋ ዝርዝር<br>• ግዥ ፈፃሚው አካል ተጠቃሚ መሆኑ የሚያሳይ ኢንሹራንስ ሰርተፊኬት<br>• የእቃዎቹ መነሻ ሀገር የሚያሳይ ሰርተፊኬት |

| | |
|---|---|
| | • የእንስፔክሽን ሰርተፊኬት<br>• ደሊቨሪ ኖት<br>• ሌላ አስፈላጊ የሆነ ሰነድ |
| አ.ው.ሁ 55.2 | የሚከተሉት ዝርዝሮች ዕቃዎቹ በታሸጉበት መያዣ ውጫዊ አካል መታየት (መለጠፍ) አለባቸው *[የማሸግያው ማብራርያ ይግባ]*<br>ሀ.<br>ለ.<br>ሐ. |
| አ.ው.ሁ 61.2 | ምርመራና ሙከራ የሚደረግበት ቦታ፡- ________ *[የምርመራና ሙከራ የሚደረግበት ቦታ የምርመራውና የሙከራው ቦታ ይገለፅ]* |
| አ.ው.ሁ 61.3 | ምርመራ እና ሙከራ ለማድረግ የሚወጣውን ወጪ የመሸፈን ኃላፊነት የማን እንደሆነ ይገለጽ። *[የምርመራና ሙከራ የሚደረግበት ወጪ የመሸፈን ኃላፊነት ይገለፅ]* |

# ክፍል 9፡ የውል ቅፆች

## ማውጫ

**ሀ. የማዕቀፍ ስምምነት....................................................1**

1. መነሻ....................................................1
2. የማዕቀፍ ስምምነት....................................................2
3. የማዕቀፍ ስምምነቱ ቃሎች....................................................2
4. የማዕቀፍ ስምምነቱ የተፈጻሚነት ወሰን....................................................3
5. የአቅራቢነት ሀላፊነት ስለመስጠት....................................................3
6. ሁሉን አቀፍነት....................................................3
7. የውል ሰጪው አካል አቋም....................................................4
8. የማዕቀፍ ስምምነት አፈጻጸም- ልዩ ውል ስለመፈፀም....................................................4
9. ግንኙነት....................................................5
10. በግዥ ፈጻሚ አካላት ላይ ስለሚደረግ ለውጥ....................................................6
11. ልዩ ውል ሲመሰረት ስለሚፈጸም ክፍያ....................................................6
12. ልዩ ልዩ....................................................6

**ለ. የውል ማስከበሪያ ዋስትና....................................................8**

**ሐ. የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና....................................................9**

## ሀ. የማዕቀፍ ስምምነት

ግዥው የሚፈፀመው፡- *[የእቃውና  አገልግሎቶች አይነት ይግባ]*

የግዥ መለያ ቁጥር፡

ይህ የግዥ ማዕቀፍ ስምምነት ዛሬ *[ቀን ይግባ]* ወር *[ወር ይግባ]* ዓ.ም. *[ዓ.ም. ይግባ]* ______*[የግዥ ፈፃሚው አካል ስም ይግባ*] በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ _____ አድራሻ *[አድራሻ ይግባ*]________(በዚህ ስምምነት “"ውል ሰጪ ባለሥልጣን" እየተባለ በሚጠራው)፣

እና

በ *[የአቅራቢው ስም ይግባ]*______በ______ የተመዘገበ አድራሻ *[የአቅራቢው አድራሻ ይግባ]* ያለው__________(በዚህ ስምምነት “አቅራቢ” እየተባለ በሚጠራው)፣

መካከል የተደረገ ነው።

መግቢያ

(ሀ) ውል ሰጪው ባለሥልጣን  ለተወሰኑ ዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች (በዚህ ስምምነት "ዕቃዎች"  እየተባሉ ለሚጠቀሱት አቅርቦት ከውሉ በአባሪነት በተያያዘው ሰነድ ዝርዝር በተገለጸው መሠረት  ለአቅራቢው ጥያቄ በማቅረቡ (ወይም ሌላ አቅራቢ መሰየም የሚችል በመሆኑ)፤

(ለ) አቅራቢው ለሥራው የሚያስፈልገው ችሎታ፣ የሠራተኛና የቴክኒክ አቅም ያለው መሆኑን በመግለጹና ዕቃዎቹን በውሉ ቃሎችና ሁኔታዎች መሠረት ለማቅረብ በመስማማቱ፤

በሁለቱ ወገኖች መካከል የሚከተለው ስምምነት ተደርጓል።

## 1. መነሻ

1.1 ውል ሰጪው ባለሥልጣን በማዕቀፍ ስምምነቱ በተገለጸው መሠረት ለተወሰኑ ዕቃዎች ግዥ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ስም የማዕቀፍ ስምምነት አድርጓል።

1.2 በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት አንቀጽ 8 መሠረት የግዥ ማዕቀፉን መጠቀም የሚችሉት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት የመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ የትምህርት ተቋማት፣ የመንግሥት ተቋማትና ሌሎች መሰል አካላት ዝርዝር በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድረ-ገጽ http://www.ppa.gov.et ተገልጾአል። በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት የመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ የትምህርት ተቋማት፣ የመንግሥት ተቋማትና ሌሎች መሰል አካላት ግዥ ፈጻሚ አካላት እየተባሉ ይጠቀሳሉ።

1.3 ውል ሰጪው ባለሥልጣን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በፌዴራል መንግሥት ባለበጀት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣የትምህርት ተቋማት፣ የመንግሥት ተቋማትና ሌሎች መሰል አካላት ዝርዝር ላይ በቅድሚያ ለአቅራቢው የአንድ ወር ማስታወቂያ በመስጠት በየጊዜው ማሻሻያ ሊያደርግ ይችላል።

1.4 የዕቃ ግዥ ማዘዣ የሚሰጠው ግዥ ፈጻሚ አካል ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አንዱ ሲሆን የሚሰጠው የግዥ ማዘዣ በውሉ ቃሎች መሠረት ሆኖ የግዥ ውሉና በአቅራቢው ስምምነት የተደረገባቸው የውል ሁኔታዎች ለዕቃዎቹ ግዥ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## 2. የማዕቀፍ ስምምነት

2.1 ይህ የማዕቀፍ ስምምነት የሚከተሉትን ሰነዶች ያካትታል፡

1. ስምምነት
2. ልዩ የውል ሁኔታዎች
3. አጠቃላይ የውልሁኔታዎች
4. የጨረታ ማቅረቢያ ሰነድና አባሪዎች
5. የዋጋ ዝርዝር
6. ተቀባይነት ያላቸው ዕቃዎች ዝርዝርና የእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ
7. የተጫራች የህጋዊነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና አባሪዎች
8. የቴክኒክ ዝርዝር፣ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ፣ የህጋዊነት ማረጋገጫና አባሪዎች
9. (በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ የተጠቀሱ ሌሎች ሰነዶች የዚህ ውል አካል ናቸው)

2.2 የዚህ ማዕቀፍ ስምምነት አላማ ስምምነት በተደረገበቸው የተወሰኑ ዕቃዎች አይነትና ስምምነት በተደረገበት ዋጋ መሠረት አቅራቢው ለግዥ ፈጻሚው አካል የሚያቀርበውን የዕቃ ዝርዝር ለመወሰን ነው።

2.3 የማዕቀፍ ስምምነቱ በፍላጎት መግለጫው ክፍል 6 በዝርዝር የተገለጸውን የዕቃዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች አቅርቦት የሚመለከት ነው።

2.4 የማዕቀፍ ስምምነቱ ሰነዶች ተደጋጋፊነት ያላቸው ሲሆን በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት ለሚሰጠው የግዥ ማዘዣ ትክክለኛ አፈጻጸም፣ የሚያስፈልገውን የዕቃ ዝርዝር ለማካተትና ለማመልከት ታስበው የተዘጋጁ ናቸው። በማዕቀፍ ስምምነቱ ሰነዶችና በማዘዣው ዝርዝር መካከል ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ ሰነዶቹ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

2.5 የዚህ የማዕቀፍ ስምምነት አካል ሆኖ በተለየ መንገድ ካልተገለጸ በስተቀር ይህን የማዕቀፍ ስምምነት ወይም በዚህ ስምምነት የተገለጸውን ዕቃ ዝርዝር የሚመለከት በቅድሚያ የሚደረግ ማንኛውም ድርድር በጽሁፍ ሆኖ የዚህ የማዕቀፍ ስምምነት አካል ተደርጎ በአባሪነት መያያዝ አለበት። በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት ድንጋጌዎች የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ ወይም ማሻሻያ ፣ በማዕቀፍ ስምምነቱ ሰነዶችና አግራጭ ጊዜዎችን በሚመለከት የሚደረግ ማንኛውንም ለውጥ ጨምሮ፣ በጽሁፍ መደረግ ያለበት ሆኖ ከማዕቀፍ ስምምነቱ ጋር በአባሪነት መያያዝ አለበት።

## 3. የማዕቀፍ ስምምነቱ ቃሎች

3.1 የማዕቀፍ ስምምነቱ በመጨረሻው ተዋዋይ ወገን ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል።

3.2 የማዕቀፍ ስምምነቱ ሥራዎች ስምምነቱ ስራ ላይ ከሚውልበት ቀን በፊት ሊጀመሩ አይችሉም። ውል ከመፈፀሙ በፊት ወይም የግዥ ትዕዛዝ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ሁኔታ የዕቃዎች ርክክብ ማድረግ አይቻልም።

3.3 የማዕቀፍ ስምምነቱ በልዩ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 7.6 ለተገለጸው ጊዜ የተደረገ ሲሆን ይህ ሥራ ላይ መዋል ከሚጀምርበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል። የውል ጊዜውና በማዕቀፍ ስምምነቱ የተገለጸ ማንኛውም ሌላ ጊዜ በሌላ መንገድ ካልተገለጸ በስተቀር በተከታታይ ባሉ ቀናት ይሰላል።

3.4 የውል ወይም የግዥ ማዘዣ ቅፆች የማዕቀፍ ስምምነቱ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ተፈርመው መመለስ አለባቸው። የማዕቀፍ ስምምነቱ የውል ወይም የግዥ ማዘዣ ጊዜ ካበቃ በኋላም ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፤ ሆኖም ከስድስት ወር መብለጥ የለበትም።

## 4. የማዕቀፍ ስምምነቱ የተፈጻሚነት ወሰን

4.1 የማዕቀፍ ስምምነቱ በውል ሰጪው ባለስልጣን፣ በግዥ ፈጻሚ አካላትና የተወሰኑ ዕቃዎችን ለግዥ ፈጻሚ አካላት ወይም ለውል ሰጪው ባለስልጣን በሚያቀርበው አቅራቢ መካከል በሚደረግ ግንኙነት ተፈጻሚ ይሆናል።

4.2 በማዕቀፍ ስምምነቱ ጊዜ ውል ሰጪው ባለስልጣንና ግዥ ፈጻሚ አካላት ከአቅራቢው ማንኛውንም ዕቃ ግዥ የመፈጸም ግዴታ የሌለባቸው መሆኑን አቅራቢው አረጋግጧል።

4.3 በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት በጨረታ ማስታወቂያው የሚገለጸው አመታዊ የፍላጎት መጠን ግምት ብቻ ሲሆን ውል ሰጪው ባለሥልጣን ስለ ግምቱ ትክክለኝነት ኃላፊነት የለበትም።

4.4 በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ለሚገዛ የማንኛውም ዕቃ ብዛትና ዋጋ ውል ሰጪው ባለሥልጣን ወይም ማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል ኃላፊነት ወይም ግዴታ የለባቸውም፤ አቅራቢውም ይህንኑ ግዴታ ወይም ኃላፊነት መነሻ በማድረግ የማዕቀፍ ስምምነት አለማድረጉን ያረጋግጣል።

4.5 ውል ሰጪው ባለስልጣንና አቅራቢው ይህ የውል ስምምነት በፍላጎት መግለጫው (በስፔስፊኬሽን) ለተገለጹት ዕቃዎች ግዥ ተፈጻሚነት እንደሚኖረው ተስማምተዋል።

4.6 አቅራቢው በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት ቃሎች ተስማምቷል፤ በተጨማሪም የማዕቀፍ ስምምነቱ በዚህ ብቻ ሳይወሰን ከአቅራቢው ጋር የተደረገ ስምምነት ጨምሮ ከማንኛውም ሌላ ስምምነት በላይ ተፈጻሚነት እንደሚኖረው በግልጽ ተስማምቷል።

## 5. *የአቅራቢነት ሀላፊነት ስለመስጠት*

ውል ሰጪው ባለስልጣን ወደፊት በውሉ የተገለጹት ዕቃዎችን ሊያቀርቡ የሚችሉ ብቁ አቅራቢዎችን ይመርጣል፤ አቅራቢውም በውል ሰጪው ባለስልጣን ወይም በማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል ለሚሰጠው የውል ስምምነት ብቁ ተደርጎ ይወሰዳል።

## 6. *ሁሉን አቀፍነት*

6.1 የማዕቀፍ ስምምነቱን መፈፀም በውል ሰጪው ባለስልጣን ወይም በግዥ ፈጻሚው አካል ላይ በማንኛውም ሁኔታ የግዥ ማዘዣ ለአቅራቢው የመስጠት ግዴታን አያስከትልም። አቅራቢው በማዕቀፍ ስምምነቱ መሠረት የውል ስምምነት ካላደረገ በስተቀር በማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል ላይ (ውል ሰጪውን ባለስልጣን ጨምሮ) ማንኛውንም የክፍያ ጥያቄ ማንሳት አይችልም። የማዕቀፍ ስምምነቱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው አቅራቢው ከውል ሰጪው ባለሥልጣን ወይም ከግዥ ፈጻሚው አካል የተወሰኑ የውል ስምምነቶች ሲፈጽምና የግዥ ትዕዛዝ ሲሰጠው ብቻ ይሆናል።

6.2 አቅራቢው ከዚህ የማዕቀፍ ስምምነት ጋር በተያያዘ በማንኛውም ጉዳይ የማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል ብቸኛ አቅራቢ ሆኖ አይሾምም። ማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል (ውል ሰጪውን ባለስልጣን ጨምሮ) ከማንኛውም ሌላ አቅራቢ ግዥ በመፈፀሙ አቅራቢው በማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል ላይ (ውል ሰጪውን ባለስልጣን ጨምሮ) የክፍያ ጥያቄ ማንሳት አይችልም።

6.3 የውል ስምምነት ከተፈፀመና የግዥ ትዕዛዝ ከተሰጠ አቅራቢው በማዕቀፍ ስምምነቱ ቃሎችና ሁኔታዎች መሠረት ተገቢ ምላሽ በመስጠት ማንኛውንም ዕቃ በአግባቡ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት።

6.4 ከአቅራቢው ውጪ ሌሎች አቅራቢዎች በጨረታ ማስታወቂያው መሠረት በማዕቀፍ ስምምነት የመሳተፍ መብት ሊሰጣቸው ይችላል። በማዕቀፍ ስምምነቱ መሠረት ወደፊት ተመሳሳይ ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ሌሎች አቅራቢዎች ሊመረጡ ይችላሉ።

## 7. *የውል ሰጪው አካል አቋም*

7.1 ውል ሰጪው ባለስልጣን በግዥ ፈጻሚ አካላት ስም እንዳስፈላጊነቱ በየጊዜው ማንኛውንም ግዥ ለመፈጸም በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን የማዕቀፍ ስምምነት አዘጋጅቷል። በአቅራቢውና በሚመለከታቸው ግዥ

ፈጻሚ አካላት ውል ሲፈፀም ውል ሰጪው ባለስልጣን የውል ስምምነቱ አካል ተደርጎ አይቆጠርም፡፡ ስለሆነም ውል ሰጪው ባለስልጣን ከዚህ የውል ስምምነት ጋር በተያያዘ በግዥ ፈጻሚ አካላት ለሚፈጸም ማንኛውም ጥፋት ወይም ጉድለት ኃላፊነት የለበትም፡፡

## 8. የማዕቀፍ ስምምነት አፈጻጸም- ልዩ ውል ስለመፈፀም

8.1 በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ስምምነቱ በሚቆይበት ጊዜ በማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል በየጊዜው የሚሰጥ የግዥ ማዘዣ በጽሁፍ ይሆናል፡፡

8.2 ማንኛውም የግዥ ማዘዣና እያንዳንዱ የውል ሰነድ በግዥ ፈጻሚው አካል የሚሰጥ ሆኖ ማዘዣውን ፈርሞ ከተቀበለበት ወይም ዕቃው በአቅራቢው መቅረብ ከሚጀምርበት ቀን በአቅራቢው ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

8.3 በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት ቀድሞ በተሟላው ሁኔታ መሠረት በግዥ ፈጻሚው አካል ተቀባይነት ያለው የግዥ ማዘዣ ከቀረበ፤

(ሀ) አቅራቢው በግዥ ማዘዣው መሠረት ዕቃዎቹን ለግዥ ፈጻሚው አካል ያቀርባል፤

(ለ) አቅራቢው የግዥ ማዘዣው ሲደርሰው በግዥ ፈጻሚው አካልና በአቅራቢው መካከል ራሱን የቻለ የተለየ የውል ስምምነት እንደተደረገ ይቆጠራል፤ ለውል አስተዳደር፣ ለወጪ ግምትና ለተጠራቀመ ወጪ እንዲሁም በማዕቀፍ ስምምነቱ አንቀጽ 8.4 እና 8.5 መሠረት ለሚደረግ ክፍያ አፈጻጸም በአቅራቢውና በግዥ ፈጻሚው አካል መካከል የውል ስምምነት እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡

8.4 በአቅራቢው የሚቀርብ የማንኛውም ዕቃ ማዘዣ የሚሰጠው በጽሁፍ ብቻ ይሆናል፡፡ በጽሁፍ የሚሰጥ የግዥ ማዘዣ ተከታታይ ቁጥር መያዝ ያለበት ሆኖ የማዕቀፍ ስምምነቱን ቃሎችና ሁኔታዎች እንዲሁም የማጣቀሻ ቁጥር ይጨምራል፤ ሆኖም የማንኛውንም ሌላ ግዥ ፈጻሚ ወይም አቅራቢ የውል ቃሎችና ሁኔታዎች አይጨምርም፤ ቢያንስ የሚከተለውን ዝርዝር መረጃ ይይዛል፡-

(ሀ) የማዕቀፍ ስምምነቱን መለያ ቁጥርና የሚቀርቡ ዕቃዎችን ዝርዝር፤

(ለ) የተጠየቀው የዕቃ ማስረከቢያ ቀን፤

(ሐ) በሁለቱ ወገኖች ስምምነት የተደረገበት የመጨረሻ ከፍተኛው ዋጋ፡፡

8.5 የማዕቀፍ ስምምነቱን ማጣቀሻ የያዘ እያንዳንዱ የግዥ ማዘዣ በማዕቀፍ ስምምነቱ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤ የማዕቀፍ ስምምነቱን ቃሎችና ሁኔታዎች በቀጥታ እንደሚያጠቃልል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ማንኛውም የግዥ ማዘዣ ለተወሰነ ዕቃ ግዥ ብቻ ተፈጻሚ የሚሆኑ የውል ማሻሻያዎችን ሊጨምር የሚችል ቢሆንም እነዚህ የውል ማሻሻያዎች የማዕቀፍ ስምምነቱ ማሻሻያ ተደርገው አይወሰዱም፡፡ የማዕቀፍ ስምምነቱን ቃሎችና ሁኔታዎች ማሻሻል የሚቻለው እንዳስፈላጊነቱ ለብቻው ራሱን ችሎ በሚሰጥ የማዕቀፍ ስምምነት ማሻሻያ ብቻ ነው፡፡ ማንኛውም የግዥ ማዘዣ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ሊሻሻል ይችላል፡፡ በግዥ ማዘዣ የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ የሚደረገው በጽሁፍ በሚደረግ ማሻሻያ ይሆናል፡፡

8.6 አቅራቢው የጽሁፍ የግዥ ማዘዣ ከግዥ ፈጻሚው አካል ከመቀበሉ በፊት ማንኛውንም ዕቃ ማስረከብ የለበትም፡፡ የግዥ ማዘዣ ሲሰጥ ለግዥ ማዘዣው አፈጻጸም የተመደበ የግዥ ፈጻሚው አካል የቴክኒክ ተወካይ በርክክቡ ቦታ ላይ የሚቀርበውን ዕቃ ያስተባብራል፣ ፕሮግራም ያወጣል፣ ማንኛውንም የርክክብ ተግባር በኃላፊነት ይቆጣጠራል፡፡ ይህም ሆኖ የስራውን መጠንና አይነት (scope of work) ለመወሰንና የዋጋ ግምት ለማወቅ በግዥ ፈጻሚው አካል የቴክኒክ ተወካይና በአቅራቢው መካከል የሚደረግ ግንኙነትና በማንኛውም ጊዜ በመመካከር መሥራትን አያስቀርም፡፡

## 9. ግንኙነት

9.1 በልዩ የውል ስምምነት መሠረት በማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል የሚፈጸም ጥፋት ወይም ጉድለት በማዕቀፍ ስምምነቱ ተፈጻሚነት ላይ ማንኛውንም ለውጥ አያስከትልም፡፡

9.2 በልዩ የውል ስምምነቱ መሠረት ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት በማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል በሚፈጸም ጥፋት ወይም ጉድለት አቅራቢው በውል ሰጪው ባለስልጣን ላይ የካሳ ጥያቄ ማቅረብ አይችልም፡፡

9.3 በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ ወይም ማሻሻያ

(ሀ) በማንኛውም የውል ስምምነት ቀጣይነት ወይም ተፈጻሚነት፤ወይም

(ለ) በማንኛውም የውል ስምምነት ለውጥ ወይም ማሻሻያ ላይ ለውጥ አያስከትልም፡፡

9.4 በአቅራቢውና በማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል መካከል (ውል ሰጪውን ባለስልጣን ሳይጨምር) ከውል ስምምነት የሚነሳ ማንኛውም ክርክር (በውል ስምምነቱ በተገለጸው የክርክር ትርጓሜ መሠረት) በሚኖርበት ጊዜ አቅራቢው ያለምንም መዘግየት የክርክሩን ባህርይ ማጠቃለያ ለውል ሰጪው ባለስልጣን ማሳወቅ አለበት፡፡

## 10. *በግዥ ፈጻሚ አካላት ላይ ስለሚደረግ ለውጥ*

10.1. በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት አንቀጽ 1 መሠረት የማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል ከግዥ ፈጻሚ አካላት ዝርዝር መሰረዝ በአቅራቢውና በዚሁ ግዥ ፈጻሚው አካል መካከል ባለው የውል ስምምነት ተፈጻሚነት ቀጣይነት ላይ ማንኛውንም ለውጥ ሊያስከትል አይችልም፡፡

10.2 ውል ሰጪው አካል በግዥ ፈጻሚ አካላት ዝርዝር ውስጥ ተጨማሪ ግዥ ፈጻሚ አካል በሚያካትትበት በማንኛውም ጊዜ አዲሱን ግዥ ፈጻሚ አካል በሚመለከት ማንኛውንም ውል ወይም የግንኙነት ነጥብና የክፍያ ሁኔታ ለአቅራቢው በቅድሚያ ያሳውቃል፡፡

## 11. *ልዩ ውል ሲመሰረት ስለሚፈጸም ክፍያ*

11.1 አቅራቢው ልዩ ውል ሲፈጽም በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ለሁሉም (ወይም ለተወሰኑ) ግዥ ፈጻሚ አካላት ላከናወነው ሥራና ላወጣው ወጪ የተጠቃለለ የወጪ ዝርዝር መግለጫ እንዲያቀርብ በውል ሰጪው ባለሥልጣን ሊጠየቅ ይችላል፡፡

## 12. *ልዩ ልዩ*

12.1 የስምምነቱ አፈጻጸም፡- የማዕቀፍ ስምምነቱ ሰነድ ከአንድ በላይ በሆነ አንድ አይነት ቅጂ ሊፈረም ይችላል፤ እያንዳንዱ ቅጂ እንደ ዋና ሰነድ ይቆጠራል፡፡

12.2 ገደብ፡- አቅራቢው በሶስተኛ ወገኖች ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት ውጪ ወይም ተፈጻሚነት ባለው ሌላ የህግ ገደብ በሌላ መንገድ ካልተገለጸ በስተቀር ከዚህ የማዕቀፍ ስምምነት የሚነሳ ወይም የተያያዘ በአቅራቢው በኩል በውል ሰጪው ባለስልጣን ወይም በማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል ላይ የሚወሰድ ማንኛውም እርምጃ ተፈጻሚ የሚሆነው ዕቃዎች ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች በቀረቡ በአንድ (1) አመት ጊዜ እንደሚሆን በሁለቱ ወገኖች መካከል ስምምነት ተደርሷል፡፡ በተጨማሪም ከዚህ የማዕቀፍ ስምምነት በመነጨ በውል ሰጪው ባለሥልጣን በኩል በአቅራቢው ላይ የሚነሳ ማንኛውም የካሳ ጥያቄ ዕቃዎች ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች እስከሚቀርቡበት ቀን ወይም በአቅራቢው ላይ የሚቀርበውን የካሳ ጥያቄ ውል ሰጪው እስከሚያውቅበት ቀን ድረስ እንደሚሆን በሁለቱ ወገኖች መካከል ስምምነት ተደርጓል፡፡

12.3 ማስታወቂያ፡- አቅራቢው በቅድሚያ ከውል ሰጪው ባለስልጣን በጽሁፍ ካላስፈቀደ በስተቀር በዚህ የማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ከቀረበው ዕቃ ጋር በተያያዘ ውል ሰጪውን ባለስልጣን ወይም ማንኛውንም ግዥ ፈጻሚ አካል የሚመለከት ማንኛውንም አይነት ማስታወቂያ ወይም ጋዜጣዊ መግለጫ ወይም ጽሁፍ መስጠት አይፈቀድለትም፡፡

12.4 አጠቃላይ ስምምነት

ይህ የማዕቀፍ ስምምነት በሁለቱ ወገኖች መካከል በቅድሚያ በጽሁፍ ወይም በቃል ከተደረገ ከማንኛውም ስምምነት በላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

ለዚህም ማስረጃ ይሆን ዘንድ ሁለቱ ወገኖች ከላይ በመጀመሪያ ገፅ ላይ በተገለጸው ቀንና ሀላፊነት ፊርማቸውን ከዘህ በታች አኑረዋል።

| ስለግዥ ፈፃሚው አካል | ስለአቅራቢው |
|---|---|
| *[የግዥ ፈፃሚ አካል ስም ይግባ]* | *[የአቅራቢው ስም ይግባ]* |
| ፊርማ፡- *[ፊርማ ይግባ]* | ፊርማ ፡- *[ፊርማ ይግባ]* . |
| ስም፡- *[አግባብ ያለው ተወካይ ስም ይግባ]* | ስም*[አግባብ ያለው ተወካይ ስም ይግባ]* |
| ኃላፊነት፡- *[ኃላፊነት ይግባ]* | ኃላፊነት፡- *[ኃላፊነት ይግባ]* |
| ቀን፡- *[ቀን ይግባ]* | ቀን፡- *[ቀን ይግባ]* . |

ምስክሮች

| | |
|---|---|
| *[የግዥ ፈፃሚ ስም ይግባ]* | *[የአቅራቢው ስም ይግባ]* |
| ፊርማ፡- *[ፊርማ ይግባ]* | ፊርማ ፡- *[ፊርማ ይግባ]* . |
| ስም ፡- *[የምስክር ስም ይግባ]* | ስም *[የምስክር ስም ይግባ]* |
| ኃላፊነት፡- *[ኃላፊነት ይግባ]* | ኃላፊነት፡- *[ኃላፊነት ይግባ]* |
| ቀን፡- *[ቀን ይግባ]* | ቀን፡- *[ቀን ይግባ]* |

**ለ. የውል ማስከበሪያ ዋስትና**

**(የባንክ ዋስትና)**

ቀን:- *[ጨረታው የቀረበበት ቀን(ቀን፣ወር እና አመተ ምህረት)ይግባ]*
የግዥ መለያ ቁጥር:- *[የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ]*

ለ:- *[የግዥ ፈፃሚ አካል ሙሉ ስም ይግባ]*

የአቅራቢው ሙሉ ስም ይግባ (ከዘህ በኋላ ''አቅራቢ'' እየተባለ የሚጠራ) በቀን____ ወር__ *[ቀንና ወር ይግባ]* ዓ.ም. *[ዓ.ም ይግባ]*____ በተፈረመው ውል ቁጥር *[የዉል ቁጥር ይግባ]* ____ (ከሁን በኋላ ''ውል'' እየተባለ የሚጠራው) መሠረት የዕቃዎቹና ተያያዥ አገልግሎቶች ዝርዝር ይገለጽ ለማቅረብ ግዴታ የገቡ ሲሆን፣

በተጠቀሰው ውል ውስጥ እርስዎ አቅራቢው ለገቡበት የውል ግዴታ ይሆንዎ ዘንድ የዋስትና አይነት ይገለጽ ከታወቀ ዋስትና ሰጭ መጠኑ ለተጠቀሰው ገንዘብ የአፈጻጸም ዋስትና እንዲያቀርቡ አጥብቀው የጠየቁ ስለሆነ።

እኛ *[የዋሱ ሙሉ ስም ይግባ]* [ሕጋዊ የመኖሪያ አድራሻው (ሙሉ የዋሱ አድራሻ ይግባ)]፣ የሆንን (ከሁን በኋላ "ዋስ" እየተባለ የምንጠራው) ለአቅራቢው ዋስትና ለመስጠት የተስማማን ስለሆነ፣

ስለዚህ እኛ አቅራቢውን በመወከል እስከ የዋስትናው የመገበያያ የገንዘብ ዓይነትና መጠኑ በአሀዝ እና በፊደል ይግባ ለሚደርስ ዋስትና ተጠያቂ መሆናችንንና አቅራቢው ውሉን መጣሱን በመግለጽ የክፍያ ጥያቄ በጽሑፍ እንደቀረበልን ያላንዳች ማስረጃና ክርክር ክፍያ ለተጠየቀበት ምክንያት እስከ የዋስትናው የመገበያያ ገንዘብ ዓይነትና መጠን በአሀዝና በፊደል ይግባ/ የሚደርስ ለመክፈል ግዴታ እንገባለን፡፡

ይህ ዋስትና የሚፀናው እስከ ቀን [ቀን ይግባ]____ ወር[ወር ይግባ]____ ዓ.ም[ዓ.ም ይግባ] ____ ድረስ ይሆናል፡፡

ይህ ዋስትና በዓለም አቀፍ የንግድ ምክር ቤት እትም ቁ. 458 መሰረት ለደንበኞች በጥያቄ የሚሰጥ አንድ ዓይነት ዋስትና ነው፡፡

ስም፦ [ዋስትናው የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስም ይግባ]
ኃላፊነት፦ [ዋስትናው የሚፈርመው ሰው ኃላፊነት ይግባ]
ፊርማ፦ [እላይ የተጠቀሰው ሀላፊነትና ስም ያለው ሰው ፊርማ ይግባ]
ዋስትናው ለመፈረም ሙሉ ውክልና የተሰጠው አካል [የተጫራቹ ሙሉ ስም ይግባ]
ቀን:ፊርማው የተፈረመበት [ቀን ይግባ] [ወር ይግባ] [እ.ም. ይግባ]

## ሐ. የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና
## (የባንክ ዋስትና)

ቀን:- [ጨረታው የቀረበበት ቀን(ቀን፣ወር እና አመተ ምህረት)ይግባ]
የግዥ መለያ ቁጥር:- [የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ]

ለ:- [የግዥ ፈፃሚ አካል ሙሉ ስም ይግባ]

በውሉ ውስጥ በተጠቀሰው የአከፋፈል ድንጋጌ መሠረት ቅድሚያ ክፍያን በተመለከተ የአቅራቢው ሙሉ ስም ይግባ (ከሁን በኋላ "አቅራቢ" ተብሎ የሚጠራው) በውሉ አንቀጽ የተጣለበትን ግዴታ በአግባቡና በሃቀኝነት ለመፈጸም ግምቱ የዋስትናው ገንዘብ ዓይነትና መጠን በፊደልና በአሃዝ ይግባ የሆነ የዋስትናው ዓይነት ይግባ ከግዥ ፈፃሚው አካል ዘንድ ማስቀመጥ አለበት፡፡

እኛ ፊርማችን ከታች የሚታየውና ሕጋዊ አድራሻችን የዋሱ ሙሉ አድራሻ ይግባ የሆነው የዋሱ የተሟላ ስም ይግባ (ከሁን በኋላ "ዋስ" እየተባለ የምንጠራው) አቅራቢው እንዳዘዘን ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታና ቃላችንን ባለማጠፍ ተራ ዋስ ሳንሆን በማይሻር ዋስትና እንደ መጀመሪያ ተገዳጅ ገዥው በመጀመሪያ እንደጠየቀን ያለምንም ተቃውሞና ክርክር አቅራቢው ሳይጠየቅ እስከ የዋስትናው ገንዘብ ዓይነትና መጠን በፊደልና በአሃዝ ይግባ የሚደርስ ለመክፈል ተስማምተናል፡፡

ይህ ዋስትና የሚጸናው በውሉ መሠረት የቅድሚያ ክፍያ ለአቅራቢው ከተፈጸመበት እለት ጀምሮ እስከ ቀን____ ወር_____ ዓ.ም______ነው፡፡ [ቀንና ወር ይግባ]፣[ዓ.ም ይግባ]

ስም፦ [ዋስትናው የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስም ይግባ]
ኃላፊነት፦ [ዋስትናው የሚፈርመው ሰው ኃላፊነት ይግባ]
ፊርማ፦ [እላይ የተጠቀሰው ሀላፊነትና ስም ያለው ሰው ፊርማ ይግባ]

ጨረታው ለመፈረም ሙሉ ውክልና የተሰጠው አካል *[የተጫራቹ ሙሉ ስም ይግባ*]

ቀን: *[ቀን ይግባ] [ወር ይግባ] [ፊርማው የተፈረመበት አመተ ምህረትይግባ]*